አስገድዶ ከመድፈርም በላይ
ገጽ 11

እንዴት ጠንካራ መሆን ይቻላል?
ገጽ 14

የሀዋሳ ከተማን ገጽታ የሚቀይረው የኮሪደር ልማት
ገጽ 17



# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

83ኛ ዓመት ቁጥር 327 ሐምሌ 27 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## ‹‹የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ዜጎች በሚጠቅም መልኩ ይመራል››

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

ገጽ 4








## ድጋፉና ብድሩ
### ኢኮኖሚው ላይ ምን ለውጥ ያመጣል?

መዓዛ ማሞ

**ዜና ትንታኔ**

ከሰሞኑ ኢትዮጵያ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ማድረጓን ተከትሎ ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት 10 ነጥብ 7 ቢሊዮን ዶላር ገንዘብ ማግኘቷን ብሔራዊ ባንክ አስታውቋል። የተገኘው ድጋፍና ብድር የሀገሪቷን ኢኮኖሚ ዕድገት በዘላቂነት መሠረት የሚጥልና የኅብረ ተሰቡን ተጠቃሚነት

ድጋፉና ብድሩ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የተኪ ምርቶች ኢኮኖሚያዊ ፋይዳዎች

ሳሙኤል ወንደሰን


**ዜና ትንታኔ**

ሀገራት ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ያላቸውን ጥገኝነት ለመቀነስ እና የሀገር ውስጥ ምርትን ለማሳደግ ተኪ ምርቶች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። ተኪ ምርት ለሀገራዊ ምርትና ኢኮኖሚ እድገት ተስፋ የሚሰጥ ቢሆንም አንድምታው ውስብስብ እና ዘርፈ ብዙ ነው።

ኢትዮጵያ ከውጭ የምታስገባው እና ወደ ውጭ የምትልከው ምርት መጠን አሁንም የተመጣጠነ አይደለም። እንደ ሀገር ከውጭ ምርቶችን ለማስገባት 18 ቢሊዮን ዶላር ስናወጣ ወደ ውጭ የምንልከው ምርት ደግሞ ከሁለት እስከ 4 ቢሊዮን ዶላር የምናገኝ መሆኑ የንግድ ሚዛኑ አለመመጣጠን ማሳያ ነው።

ለአብነት ያህል ኢትዮጵያ በ2016 በጀት ዓመት ከውጭ የሚገቡትን ምርቶች ለመተካት በሠራችው ሥራ 2ነጥብ 8 ቢሊዮን ዶላር የሚያወጡ ምርቶች በሀገር ውስጥ ተመርተዋል፡፡ ሆኖም ከውጭ የሚመጣው ጋር ሲነፃፀር አሁንም ዝቅተኛ ነው፡፡

የተኪ ምርቶች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





# በቀጣዩ ወር ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያጋጥም ስለሚችል ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በቀጣዩ የነሐሴ ወር በሁሉም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊከሰት ስለሚችል ከወዲሁ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

አንስትቲዩቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ በቀጣዩ የነሐሴ ወር በሁሉም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች በመጠንም ሆነ በሥርጭት ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ ይጥላል። ዝናቡ በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል ስለሚችል ከወዲሁ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልጋል።

ቀጣዩ የነሐሴ ወር ሁሉም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች በመጠንም ሆነ በስርጭት ከፍተኛ መጠን የሚደርስበት መሆኑን የጠቀሰው መግለጫው፤ ከዚህም ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ለተከታታይ ሰዓትና ቀናት የሚዘንብበት፣ በተጨማሪም በፀሐይ ኃይል ታግዘው ከሚፈጠሩ የደመና ክምችቶች በረዶ የቀላቀለ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የሚስተዋልበት መሆኑን አትቷል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የወንዞች ሙላትና ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊከሰት ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ብሏል።

በቀጣዩ ነሐሴ ወር የክረምት ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን የሚያገኙ ሲሆን በተለይም በአብዛኛው ዓባይ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ ባሮአኮቦ፣ አሞጊቤ፣ አፋር ደናክል፣ የላይኛው እና የመካከለኛው የስምጥ ሸለቆ፣ ዋቢሸበሌ እና የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖራቸው ጠቁሟል።

ይህም ሁኔታ ወደ ግድቦች እና ወደ ተለያዩ የውሃ ማጠራቀሚያዎች የሚገባውን የውሃ መጠን ከመጨመርና የወንዞች ውሃን ሙላት አቅም ከማጎልበት አንጻር ጥሩ አዎንታዊ ሚና ያለው መሆኑን አብራርቷል።

ሆኖም ሊኖር ከሚችለው ከፍተኛ እርጥበት ጋር ተያይዞ የቅጽበታዊ ጎርፍ፣ የወንዝ ዳርቻዎች በውኃ መጥለቅለቅና የግድቦች የውሃ መጠን በከፍተኛ ሁኔታ መጨመር ሊከሰት ይችላል። ወንዞች በመደበኛ ከሚደርሱበት የውኃ ከፍታ በላይ ሊደርሱና ከመጠን በላይ ሊሞሉ ስለሚችሉ የግድቦች የቅርብ ክትትል ሥራን ማጠናከር ያስፈልጋል።

በተጨማሪም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ የከተማም ሆነ የገጠር አካባቢዎች ላይ በሕይወት፣ በንብረትና በመሠረተ ልማት ላይ ጉዳት እንዳያስከትል የጎርፍ ማፋሰሻዎች ማፅዳት ያስፈልጋል። ግድቦች እና የተለያዩ የውሃ ማጠራቀሚያዎች የቅርብ ክትትል በማድረግ ስጋትን አስቀድሞ በመለየት ጉዳትን ለመቀነስ እና ለማስቀረት የሚያስችል ዝግጅት ማድረግ እንደሚገባ ኢንስትዩቱ በላከው መግለጫ አመላክቷል።

በሌላም በኩል በነሐሴ ወር የሚኖረው እርጥበት በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች የውሃ ፍላጎትን ለማሟላት፣ ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሣርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ከማሻሻል አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

በመሆኑም አርሶ አደሮች እና ከፊል አርብቶ አደሮች እንዲሁም የሚመለከታቸው አካላት ሰብሎች በጎርፍ እንዳይጠቁ እና በማሳ ላይ ውሃ እንዳይተኛ የጎርፍ መቀልበሻዎችን ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል ብሏል።

ከማሳ ውስጥ ውሃን ማንጣፈፊያ ቦዮችን ማዘጋጀት እንዲሁም የፀረ-አረም እና የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በወቅቱና የአየር ሁኔታ ምቹነትን ባገናዘበ ሁኔታ ጥቅም ላይ ማዋል ያስፈልጋል ብሏል ኢንስቲትዩቱ በመግለጫው።

# ክልሉ ለሕዝባዊ አጀንዳ ትኩረት በመስጠቱ ውጤታማ መሆኑን ገለጸ

**ዘላለም ግዛው**

ሆሳዕና፡- አመራሩን ከጎጠኝነት፣ ከቡድንተኝነት፣ ከጎሰኝነት አጀንዳ እና አስተሳሰብ ተላቅቆ ሕዝባዊ አጀንዳን እና ኃላፊነትን አንግቦ እንዲሠራ በመደረጉ ስኬት ማስመዝገብ መቻሉን የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ እንዳሻው ጣሰው ገለጹ።

ርዕሰ መስተዳድሩ በጽሕፈት ቤታቸው በሰጡት መግለጫ በ2017 ዓ.ም ሠላምን ለማስፈንና ለማጽናት የሚደረገው ሂደት እንዳይቀለበስ ትኩረት መስጠቱን አመልክተዋል።

የሕዝብ አንድነትን ማጠናከር፣ ያሉ ቁርሾዎችን መፍታት ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ይሠራሉ ብለዋል።

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት 10 ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ገቢ መሰብሰቡንና ካምናው ጋር ሲነጻጸር የሁለት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ልዩነት እንዳለውም ጠቁመዋል።

ለገቢ አሰባሰብ የሚረዱ የፀደቁ ደንቦች፣ አዋጆችና አሠራሮችን ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ በማድረግ ስምንት ቢሊዮን ብር ተጨማሪ ገቢ ለማግኘት መታቀዱንም ተናግረዋል።

በክልሉ ምርታማነትን ለማረጋገጥ እንደሚሠራ፤ በዓመቱ አንድ ሚሊዮን 134 ሺህ ሄክታር መሬት እንደሚለማ እንዲሁም ከተረጂነት ለመውጣት መርሐ ግብር መነደፉንና በመጀመሪያው ትግበራ 65 በመቶ ለመቀነስ እቅድ መያዙንም ጠቁመዋል።

የኅብረተሰቡን ኑሮ ለማረጋጋት በመጪው ዓመት እቅድ መያዙን ያመለከቱት አቶ እንዳሻው፣ ከሰንበት እስከ ሰንበት አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ገበያዎችን ቁጥር በ34 በመጨመር ወደ 138 ለማድረስና የንግድ ሥርዓቱን ለመቆጣጠር መታቀዱን ተናግረዋል።

የሕዝቡን ተጠቃሚነት እያረጋገጥን፣ በክልሉ የሚነሱ ችግሮችን በዕቅዱ በማካተት እየፈታን እንቀጥላለንም ብለዋል።



አቶ እንዳሻው ጣሰው

በግብርና፣ በቱሪዝምና በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተጀመሩ ሥራዎችን ቀጣይነት በማረጋገጥ ለዘርፉ ትኩረት ይሰጣል ሲሉም ተናግረዋል።

የተለያዩ የአደረጃጀትና የማንነት ጥያቄዎች፣ በርካታ የመልካም አስተዳደር ችግሮች፣ አፍራሽ ተልዕኮን በማንገብ በአመራሮች መካከል መከፋፈል የሚፈጥሩ አካላት፣ ሕዝብን ከሕዝብ ለማጋጨትና የተጀመሩ የልማት ሥራዎችን ለማደናቀፍ የሚሠሩ ጽንፍ የወጡ የማኅበራዊ ትስስር ገጾች ለክልሉ ፈተና እንደነበሩም አስታውሰዋል።

በግንዛቤ ፈጠራና ሕጋዊ ርምጃ በመውሰድ ችግሩን ማርገብ መቻሉንም ጠቁመዋል። ምላሽ ያገኙ፣ በውይይትና በጥናት ምላሽ የሚሹ የሕዝብ ጥያቄዎች መኖራቸውንም ገልጸዋል፡፡

በክልሉ በአስተዳደር ብልሽት ምክንያት የመምህራን፣ የጤና እና የግብርና ባለሙያዎችን ደመወዝ በአግባቡ አለመከፈሉም ፈተና እንደነበርና አብዛኛው መፈታቱን ቀሪውም በቀጣይ እንደሚፈታ ተናግረዋል። ለችግሩ መከሰት አመራሩ ለደመወዝ የተመደበውን በጀት ለሌላ በመጠቀም እንደተፈጠረም ጠቁመዋል።

ለአርሶ አደሩ በሚፈለገው መጠን የአፈር ማዳበሪያ ማሰራጨት አለመቻልና የአፈር ማዳበሪያ በሕገ ወጥ ደላሎች ሽያጭ ሌላ ፈተና ነበር ብለዋል።

በንግድ ሥርዓቱ ሕገወጥነት የተስፋፋበት፣ የሸቀጦች የዋጋ ንረት የተባባሰበት ክስተትና የምርት እንቅስቃሴንም የሚገድቡ ኬላዎች እንደነበሩም ተናግረዋል። በተለያዩ አካባቢዎች የፀጥታ ችግር እንዲከሰት የሚጥሩ አካላት ፈተና እንደነበሩም ተናግረዋል።

ከነባሩ ክልል የተላለፈ አምስት ቢሊዮን ብር ዕዳ ውስጥ ከሦስት ቢሊዮን ብር ያላነሰ ክፍያ ተፈጽሟል ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ ክልሉን ከማደራጀት ጎን ለጎን የሕዝብ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉም አመልክተዋል።

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ነሐሴ 13 ቀን 2015 ዓ.ም በይፋ ተመሥርቶ ወደ ሥራ መግባቱ ይታወሳል።

# ከአምስት ሺህ በላይ አዳዲስ ደንበኞች በፀሐይ ኃይል የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ሆኑ

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት ከአምስት ሺህ በላይ አዳዲስ ደንበኞችን በፀሐይ ኃይል የኤሌክትሪክ (በሶላር ኢነርጂ) ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር መላኩ ታዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎትን በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል ተደራሽ ለማድረግ ከዋናው የኤሌክትሪክ ግሪድ በተጨማሪ የተለያዩ የኃይል አማራጮችን ለመጠቀም ጥረት እየተደረገ ይገኛል። በዚህም ባለፈው በጀት ዓመት ከአምስት ሺህ በላይ አዳዲስ ደንበኞች በፀሐይ ኃይል የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

በርካታ የሀገሪቱ ክፍል የሚገኙ ዜጎች ኤሌክትሪክ ኃይል እያገኙ አይደለም ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ዋናውን የኤሌክትሪክ ቋት ተከትሎ የኤሌክትሪክ ተደራሽነት ለማረጋገጥ ረጅም ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ ሌሎች የኃይል አማራጮችን መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል።

ለዚህም አገልግሎቱ የፀሐይ ኃይልን ለዜጎች እንደ አማራጭ ኃይል እያቀረበ እንደሚገኝ አመልክተው፤ በተለይ ከዋናው ግሪድ እርቀው የሚገኙ የገጠር ከተሞችን ተደራሽ ለማድረግ የፀሐይ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች በተለያየ ምዕራፍ እየገነባ እንደሚገኝ አስገንዝበዋል።

በመጀመሪያው ምዕራፍም አስራ ሁለት የገጠር ከተሞችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ፕሮጀክት ተጠናቆ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ከዚህ በተጨማሪም በአሁኑ ጊዜ 25 የገጠር



አቶ መላኩ ታዬ

ከተሞችን ተደራሽ የሚያደርግ ፕሮጀክት እየተሠራ መሆኑና አፈጻጸሙ 64 በመቶ መድረሱን ገልጸዋል። ይህ ፕሮጀክትም በ2017 ዓ.ም ተጠናቆ አገልግሎት ይሰጣል ተብሎ እንደሚጠበቅም አብራርተዋል።

አቶ መላኩ 2016 በጀት 100 አዳዲስ ከተሞች ኤሌክትሪክ ኃይል እንዲያገኙ ታቅዶ የተሠራ ሲሆን ባለፈው በጀት ዓመትም 116 የገጠር መንደሮችና ቀበሌዎች ኤሌክትሪክ ኃይል እንዲገኙ ማድረግ መቻሉን ገልጸዋል።

ከእነዚህ ውስጥ አስራ ሦስት ከተሞች በፀሐይ (ሶላር) ኃይል ኤሌክትሪክ ያገኙ ሲሆን በዚህም ከአምስት ሺህ በላይ የሚሆኑ አዳዲስ ደንበኞች ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን ተናግረዋል።

በቀጣይ 35 በመቶ የሚሆነው የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ከዋናው ግሪድ ውጪ ባሉ ሌሎች የኃይል አማራጮች የሚሸፈን መሆኑን ጠቁመው፤ ከእነዚህ የኃይል አማራጮች የፀሐይ ኃይል አንዱን ነው ብለዋል።

የኤሌክትሪክ ኃይል ተደራሽነትን ማረጋገጥ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ድርሻ ብቻ አይደለም ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በተለይም በፀሐይ ኃይል አማራጭ ላይ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር እንዲሁም የሌሎች የግል ኢነርጂ ቢሮዎች ትብብር እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

# አካዳሚው ከአምስት ሺህ በላይ የሀገር ውስጥና የአፍሪካ ሀገራት አመራሮች ሥልጠና ሰጥቷል



**ወንድዬ ስገሠ (ዶ/ር)**

ታደሠ ብናልፈው

ሱሉልታ፡- በ2016 በጀት ዓመት ከአምስት ሺህ በላይ የሀገር ውስጥና የአፍሪካ ሀገራት አመራሮች ሥልጠና መስጠቱን የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ገለጸ።

የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት ወንድዬ ለገሠ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አካዳሚው በ2016 በጀት ዓመት ከአምስት ሺህ በላይ ለሚሆኑ የሀገር ውስጥና የአፍሪካ ሀገራት ከፍተኛና መካከለኛ አመራሮች ብቁ የሚያደርግ ሥልጠና ሰጥቷል።

ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ አካዳሚው የተለያዩ ለውጦችን አድርጓል ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ በተሠራውም ሥራ አመራሮችን ብቁ የሚያደርግ የሥልጠና ሥርዓተ ትምህርት በማዘጋጀት በአመራር ክህሎት የታነጹ አመራሮችን እያፈራ ይገኛል ብለዋል።

አመራሮችን በአመራር ክህሎትና እውቀት ብቁ ለማድረግ አካዳሚው ከተለያዩ ተቋማት ጋር በጋራ እየተሠራ ነው ያሉት ወንድዬ (ዶ/ር)፤ በአሁኑ ጊዜም በተቋማት ፍላጎት መሠረት ለአመራሮች ስኬታማ የሚያደርግ ሥልጠና እየሰጠ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

አካዳሚው የአፍሪካ አመራሮችን እንዲሁም የሀገር ውስጥ ከፍተኛና መካከለኛ አመራሮችን በየዘርፉ ለማሠልጠን 38 ፕሮግራሞችን እየቀረጸ መሆኑን ጠቁመው፤ የክልል አመራሮችን በማቀራረብ፣ በልምድ ልውውጥና ጥራዝ ነጠቅ ትርክቶችን በማረም ሀገራዊ መግባባት ለመፍጠር እንዲሠሩ በትኩረት እየተሠራ መሆኑንም አብራርተዋል።

አካዳሚው ለአመራሮች የሚሰጠው ሥልጠና ሀገሪቱ የሥራ ኃላፊዎችን ወደ ውጭ ልካ ለማሠልጠን የምታወጣውን ወጪ ማስቀረት ብቻ ሳይሆን ገቢም እንድታገኝ እያደረገ ነው ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ አካዳሚው አሁን እየሰጠ የሚገኘውን የሥልጠና ፕሮግራም ይበልጥ በማስፋፋትና በማዘመን የሀገሪቱን የዶላር እጥረት ለመፍታት የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

አካዳሚው ለአፍሪካ አመራሮች የአመራር ብቃታቸውን ለማሳደግ እየሠራ ያለው ሥራ በአሕጉሪቱ መልካም አስተዳደር እንዲገነባ ትልቅ ሚና እየተጫወተ እንደሆነ ጠቅሰዋል።

ለአብነትም በ2016 በጀት ዓመት በሁለት ዙር ለ110 የደቡብ ሱዳን አመራሮች ሥልጠና መስጠቱን ተናግረዋል።

አካዳሚው በሚሰጠው የአመራሮችን የማብቃት ሥልጠና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን በመገንባት፣ መልካም አስተዳደር በማስፈን ለሀገራዊ፣ ለአካባቢያዊና ለአሕጉራዊ ሁለተናዊ ፋይዳው የጎላ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

አካዳሚው ከሚሰጠው የተለያዩ የአመራርነት ሥልጠናዎችም ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት እንዲሰማሩ የሚያነቃቃ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

አካዳሚው እየሰጠ የሚገኘውን የአመራሮች ሥልጠናም በተሻለ ብቃትና አሠራር አጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ አመላክተዋል።

# "ኢትዮጵያን የሚመጥናት ቁመና ላይ እንድትሆን የሚያደርገው የሥራ ባሕላችን በአግባቡ ሲቃኝ ነው"

## -ኡስታዝ አቡበክር አሕመድ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የፕሬዚዳንቱ ልዩ አማካሪ

አስቴር ኤልያስ



አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያን ስሟን ከፍ ማድረግ የሚቻለውና የሚመጥናት ቁመና ላይ እንድትሆን የሚያደርገው የሥራ ባሕላችን በአግባቡ ሲቃኝ ነው ሲሉ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የፕሬዚዳንቱ ልዩ አማካሪ ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ አስታወቁ፡፡

ኡስታዝ አቡበከር ከአዲስ ዘመን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንዳስታወቁት፤ የኢትዮጵያን ስም ከፍ ማድረግ የሚቻለው የሥራ ባሕላችን በአግባቡ ሲቃኝ ነው፡፡ ጠንካራ የሥራ ባሕል የሚዳብር ከሆነ ኢትዮጵያን እንደ ስሟ በሚመጥናት ቦታ ላይ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

ለዚህ ከፍታ ደግሞ እንደ ሀገር ያለን የሥራ እይታ መቀየር ተገቢ ነው ያሉት ኡስታዝ አቡበከር፣ ኢትዮጵያ ካለችበት ወደ ተሻለ ስፍራ ለማሸጋገር የሥራ ባሕላችን መስተካከል አለበት ሲሉ አፅንዖት ሰጥተዋል፡፡ ሀገሩንና ማኅበረሰቡን ከፍ ማድረግ የሚችልና ያንን ሥርዓት የመለወጥ ኃላፊነት ደግሞ የሁሉም ዜጋ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

እንደ ኡስታዝ አቡበከር ገለጻ፤ የዛሬው ትውልድ ሀገሬ ኢትዮጵያ ሁልጊዜ በርዳታና በድጋፍ መኖር የለባትም ብሎ መወሰን አለበት፡፡ ምክንያቱም ሁሌ በድጋፍና በርዳታ የምትኖር ሀገር ካለችን ውርደቱ የእርሱም ጭምር ነው፡፡ ትውልዱ የሥራ ባሕሉን ማስተካከል ካልቻለ ከከፍታ ይልቅ ውርደትን መርጧልና ቆም ብሎ ሊያስብ ይገባዋል፡፡ ከላይ ከመንግሥት ተቋማት ጀምሮ እስከታች ያለው ማኅበረሰብ፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የማኅበረሰብ መሪዎች ጭምር የሥራ ባሕሉን ማሳደግና ሀገሩን መውደድ መቻል አለበት፡፡

ሰው ዛሬን ብቻ ኖሮ የሚያልፍ ፍጥረት መሆን የለበትም፤ ሰው ማለት ለነገ የሚተርፍ እና ለሌሎች ተስፋ መሆን የሚችል ነው ያሉት ኡስታዝ አቡበከር፣ ከዚህ አኳያ ቤተ እምነቶች ትውልዱን የማንቃት ትልቁን ድርሻ ይይዛሉ ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የሃይማኖት መሪዎችና አባቶች፤ ሊሠሩ የማይወዱ እጆች መኖር እንደማይገባቸው ትውልዱን በማስተማር በኩል ትልቁን ሥራ የመሥራት ኃላፊነት እንዳለባቸውም አስረድተዋል፡፡ ይህ ደግሞ የእምነቱም ግዴታ ነው ብለው እንደሚያምኑ ተናግረዋል፡፡

ኡስታዝ አቡበከር፣ "ነብዩ መሐመድ (ሰዐወ) የማይሠሩ እጆችንና የሚለምኑ እጆችን የሚያወግዟቸው መሆኑን ገልጸው፤ አላህ ዘንድ ተወዳጅ ባሪያ ማለት በሥራ የደከመ ባሪያ ነው" ሲሉ አመልክተዋል፡፡

"ትውልዱ መሥራት ካልወደደ ሃገራችን በርዳታና በጥገኝነት እንድትኖር፣ ዜጋውም የራሱ የሆነ ማንነት እንዳይኖረውና የሌሎችን የፖለቲካ ሐሳብና ፍላጎት የምታስፈጽም ሀገር እንዲኖረው መርጧልና የሚጠብቀው ክብር ሳይሆን ውርደት ይሆናል ማለት ነው ብለዋል፡፡ ነገር ግን ትውልዱ ከፍታን ከመረጠና ከዚያ ከፍታ ላለመውረድ የሚሠራ ከሆነ የሚሰለፈው ከታላላቅ ሀገራት ጋር መሆኑን አስታውሰዋል፡፡ ለዚያ ለከፍታ የሚሆን ሥራ እንደዜጋ፣ እንደ ማኅበረሰብ ኃላፊነታችንን መወጣት እንዳለብን ገልጸዋል፡፡


ኡስታዝ አቡበከር እንዳሉት፤ ያንን ከፍታ ማምጣት የምንችለው በመሥራት እንጂ በማውራት እና በትናንት ታሪክ በመጣላት አይደለም፡፡ እኛ ባልኖርንበትና የታሪክ አካል ባልሆንበት ጉዳይ ላይ እየተጨቃጨቅንና እየተገፋፋን መቀጠል አይኖርብንም፡፡ እየሠራን፤ እየተለወጥን፤ ለሀገርና ለማኅበረሰብ ከፍታ መትጋት አለብን፡፡

እየፈጠርን ያለነው ምን አይነት ትውልድ ነው የሚለውን ማጤን ተገቢ ነው ሲሉ ጠቅሰው፤ መለመንን፣ ውርደትን፣ የበታችነትን፣ መስረቅን ወይም ደግሞ ጉቦን የሚጠየፍ ትውልድ ካልፈጠርን መከራው የሁሉም እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

ይህ ችግር እንዳይቀጥልም መሠራት የግድ መሆኑን አመልክተው፤ የሥራ ልምምዱም ሆነ ትምህርቱ ከታች ከቤተሰብ እና ከትምህርት ቤት እንዲሁም ከሃይማኖት ተቋማት የሚጠበቅ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

# የኢትዮጵያ መንግሥት ከታይላንድና ከማይናማር ጋር ያደረገው የሥራ ስምሪት ስምምነት የለም

ሞገስ ፀጋዬ



**አምባሳደር ነብዩ ተድላ፤**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መንግሥት ከታይላንድና ከማይናማር ጋር ያደረገው የሥራ ስምሪት ስምምነት አለመኖሩን ኅብረተሰቡ በመገንዘብ ከሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪ አደጋ ራሱን መጠበቅ እንዳለበት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር መገናኛ ብዙኃን ትናንት መደበኛ ሳምንታዊ መግለጫ ሰጥቷል። መግለጫውን የሰጡት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር ነብዩ ተድላ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት የሥራ ስምሪት ስምምነት ባልፈጸመባቸው ሀገሮች በሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች መሠረት ወደ ታይላንድና ማይናማር የሚሄዱ ኢትዮጵያውን መኖራቸውን ገልጸዋል።

እንደ አምባሳደሩ ገለጻ፤ አሁንም ወደ ታይላንድና ማይናማር የሚሄዱ ዜጎች ስለመኖራቸው መረጃዎች እየደረሱን ነው። መንግሥትም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይህን ሕገወጥ ድርጊት ለማስቆም ጥረት እያደረገ ነው።

ማንኛውም ዜጋ የኢትዮጵያ መንግሥት ከታይላንድና ከማይናማር ጋር የተደረገው አንዳችም የሥራ ስምሪት ስምምነት አለመኖሩን ተገንዝቦ ራሱን ከሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች አደጋ መጠበቅ አለበት ሲሉ አሳስበዋል።

ወደ እስያ በተለይ ታይላንድና ማይናማር የሚደረጉ ሕገወጥ ጉዞዎች አሉ ያሉት ቃል አቀባዩ፤ በሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች ተታለው የሚሄዱ ኢትዮጵያውያን ለችግር እየተጋለጡ መሆኑን ገልጸዋል።

በአሁኑ ጊዜ ታይላንድና ማይናማርን የሚሸፈኑት በጃፓንና በሕንድ በሚገኙ የኢትዮጵያ ሚሲዮኖች መሆናቸውን አመልክተው፤ ችግሩን ለመፍታት ክትትል እያደረጉ ነው። ወደ ታይላንድና ማይናማር በሕገወጥ መንገድ የተጓዙ ዜጎችን ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ሥራዎች ተሠርተዋል፤ በተለይ ወደ ታይላንድ በሕገወጥ መንገድ ገብተው ወደ ማይናማር ሊሻገሩ የነበሩ ኢትዮጵያኖችንም የመመለስ ሥራ መከናወኑ ጠቅሰዋል።

እንደ አምባሳደር ነብዩ ማብራሪያ፤ ወደ ታይላንድ የሚደረጉ ጉዞዎች የሆቴልና ትኬት ጉዳዮች ብቻ ከተመቻቹ በቀላሉ መሄድ ይቻላል። ይህን ምቹ ሁኔታ ሕገወጥ አዘዋዋሪዎች በመጠቀም ኢትዮጵያውያን ሥራ እናስቀጥራችኋለን በሚል ወደ ታይላንድና ማይናማር የማሻገር ሁኔታዎች አሉ። ይህን ሕገወጥ ስምሪት ኅብረተሰቡ ሊገነዘበውና ከመታለል ሊጠነቀቅ ይገባል። ችግሩ እንዳይሰፋ በመንግሥት በኩል ሥራዎች እየተሠሩ ነው።

‹‹ሕጋዊ የሥራ ስምሪት በሌለበት ሁኔታ ወደ ታይላንድና ማይናማር የሚደረጉ ጉዞዎችን ተገቢ አለመሆናቸውን ቀደም ብለን አስገንዝበናል››። ዜጎች ያጋጠማቸውን ችግር ተከትሎ ታይላንድንና ማይናማርን የሚሸፍኑ የኢትዮጵያ ሚሲዮኖች ከየሀገራቱ መንግሥታት ጋር እየሠሩበት እንደሚገኙ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

ወደ ማይናማር የሚደረጉ ጉዞዎች ቦታው አስቸጋሪ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ጊዜ ሊወስድ ይችላል፤ ይሁንና ማንኛውም ዜጋ በሕገወጥ የሥራ ስምሪት ውስጥ ሕዝቡ መሳተፍ የለበትም ሲሉ ቃል አቀባዩ አሳስበዋል።

በነገው ዕለት የተርከዩ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተመራ የልዑካን ቡድን ወደ አዲስ አበባ ይገባል። ልዑካን ቡድኑ በቀጣይ በሁለቱ ሀገራት ግንኙነትና በሌሎች የሁለቱ ሀገራት የዲፕሎማሲ ሁነቶች ላይ የሚሳተፍ ይሆናል ብለዋል አምባሳደር ነብዩ።

# «የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ዜጎች በሚጠቅም መልኩ ይመራል»

## - ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎችን በሚጠቅም መልኩ እንደሚመራ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲው ላይ በሰጡት ማብራሪያ፤ ደሃ ተኮር ስለሆን ደሃን የሚጎዳ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ አናደርግም፤ ማሻሻያው ደሃን በሚጠቅም መንገድ እንመራዋለን ብለዋል፡፡

የኢንቨስትመንት በሚፈለገው ደረጃ አለማደግ፣ በቂ መሠረተ ልማት አለመኖር፣ የተቋማት ተልዕኮ የመፈጸም ውስንነት እንዲሁም ሀገራዊ ዕዳ ጫና የሚፈለገውን ሀገራዊ እድገት ማምጣት እንዳይቻል ካደረጉ ምክንያቶች መካከል መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ማሻሻያው እንደ ኮሶ መራራ ነገር ግን በሂደት የሀገርን እድገት ማረጋገጥ የሚያስችል ፍቱን መድኃኒት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የመንግሥት ሠራተኞች፣ አርሶ አደሮችና ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ በሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ ጫና እንዳያሳድር በትኩረት ይሠራል ብለዋል፡፡

በዚህም ለመንግሥት ሠራተኛው ለሚደረግ ደመወዝ ማሻሻያ ከ90 ቢሊዮን ብር በላይ ሀብት መጠየቁን ገልጸው፤ በዚህም ታችኛው እርከን ላይ ለሚገኘው ሠራተኛ ከፍተኛ የደመወዝ ጭማሪ ተደርጓል፡፡ ከ25 ሺህ ብር በላይ የሚከፈላቸው ደግሞ ባሉበት እንዲቆዩ ተደርጓል ነው ያሉት፡፡

ይህ ማለት ግን ይበቃቸዋል ማለት ሳይሆን ለጊዜውም ቢሆን ጫናውን መሸከም ስለሚችሉ ታግሰው ይቆዩ በሚል የተወሰነ ነው ብለዋል፡፡

በከተማ ለሚኖሩ ዝቅተኛ ኢኮኖሚ ያላቸው ዜጎችም በሴፍትኔት የሚደገፉበት በቂ ፕሮግራም ተዘጋጅቷል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በማዳበሪያ ዋጋ ጭማሪ ምክንያት አርሶ አደሩ ላይ ጫና እንዳይደርስ መንግሥት ድጎማ ማድረጉን ይቀጥላል፡፡ ለዚህም በርካታ ቢሊዮን ብር ወጪ ይደረጋል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ነዳጅም ማኅበረሰቡ ሕይወት ላይ ጫና እንዳያደርስም መንግሥት ለድጎማ 100 ቢሊዮን ብር የሚያወጣ ይሆናል ብለዋል፡፡

ኢኮኖሚው ክፍት ለማድረግ የተወሰነው ዛሬ ሳይሆን ለውጡ በመጣ ጥቂት ወራት ውስጥ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በዚህም ተዘግቶ የነበረውን ኢኮኖሚ በመክፈት ዓለምን ተቀላቀልን እንጂ ሌላ የተፈጠረ ተዓምር የለም ሲሉ አስገንዝበዋል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ከነዳጅና ማዳበሪያ ውጭ ሁሉም ሥራ ሲሠራ የቆየው በጥቁር ገበያ እንደነበር አስታውሰው፤ ዋናው ዓላማውም በሕጋዊ ምንዛሪና በጥቁር ገበያ መካከል ያለው ልዩነት ማጥበብና ሕገወጥትን ማስቀረት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ማሻሻያው እንዲሳካም እንዳይሳካም ማድረግ የምንችለው እኛ ነን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፤ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ ወጪ ምርትን መጨመርና ከምናገኘው ገቢ ላይ ተገቢውን ግብር መክፈል ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይገባል ብለዋል፡፡

መንግሥትም የሰበሰበውን ገቢ በአግባቡ ማስተዳደርና የተቀላጠፈ አገልግሎት መስጠት ላይ ቁርጠኛ መሆን ይጠበቅበታል ነው ያሉት፡፡

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ማሻሻያውን በትብብር ከመራነው በሚቀጥሉት 10 ዓመታት ትልቅ ሀገራዊ እድገት ይመዘገባል፡፡ በዚህም አገልግሎት ሰጪና አምራች ዘርፉ ከፍተኛ እድገት ያሳያል፡፡ ግብርና በራሱ የሚኖረው እድገት እንደተጠበቀ ሆኖ አሁን ኢኮኖሚው ላይ ያለው የአንድ ሦስተኛ ድርሻ ከአስር በመቶ በታች ይሆናል፡፡ ሀገራዊ ዕዳም ከ8 እስከ 10 በመቶ ዝቅ ይላል፡ ፡ ከወጪ ንግድ ከሚገኘው ገቢም ላይም 10 በመቶ ብቻ ለዕዳ ክፍያ ይውላል፡፡

ይህ ውጤት በቀላሉ የሚመዘገብ ሳይሆን በተለይ በመጀመሪያው ዓመት ላይ ብዙ ትግል የሚፈልግ መሆኑን ጠቁመው፤ መንግሥት፣ የግሉ ዘርፍና ሕዝቡ በትብብር መሥራት ይጠበቅበታል ብለዋል፡፡

የማክሮ ኢኮኖሚውን ማሻሻያ ምክንያት በማድረግ አግባብነት የሌለው የዋጋ ጭማሪ የሚያደርጉ ነጋዴዎች መኖራቸውን አስታውሰው፤ ይህን የሚከታተልና የሚቆጣጠር ግብረ ኃይል ተቋቁሟል፤ ጠንካራ ርምጃም እንደሚወሰድ አመልክተዋል፡፡

የሚኖሩ ጭማሪዎች በተጠና መልኩ እንጂ በዘፈቀደ በሕዝቡ ላይ የሚደረግ ዘረፋና ቅሚያ ግን ተቀባይነት የለውም፤ ሕዝቡን ከሕግ አስከባሪ አካላት ጋር በማቀናጀት ጠንካራ ቁጥጥር እንደሚደረግና ርምጃ እንደሚወሰድ ጠቁመዋል፡፡

# የተኪ ምርቶች...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ይህን ያጋደለ የንግድ ሚዛን የሚታየው ደግሞ ምርትና ምርታማነት በሚጠበቀው ደረጃ አለማደጉ፣ እሴት ያልተጨመረባቸው ምርቶችን ወደ ውጭ መላክና ሌሎች ችግሮችም በመንስኤነት ይጠቀሳሉ።

ኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ዘርፉን ለማጠናከር እና ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ያላትን ጥገኝነት ለመቀነስ "የተኪ ምርት ስትራቴጂ" ቀርፃ ተግባራዊ እያደረገች መሆኑን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ታረቀኝ ቡሉልታ ይገልጻሉ።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ኃይለመስቀል ጋዙ በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ መሠረተ ልማት ማለትም የኤሌክትሪክ ኃይል፣ ትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስን ጨምሮ ለተኪ ምርቶች ልማትና ስርጭት ትልቅ ማነቆ ነው። የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረት በተለይም በቴክኒክና በአስተዳደር ሚናዎች በኩል ያለው ክፍተት ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን እና ተወዳዳሪ ተኪ ምርቶችን የማምረት አቅምን ያደናቅፋል ይላሉ።

ለንግድ ድርጅቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ያለው የፋይናንስ አቅርቦት ውስን መሆን በምርምር፣ ልማት እና ምርት ላይ ኢንቨስት ማድረግን ያግዳል ያሉት አቶ ኃይለመስቀል፤ ከዓለም አቀፍ ብራንዶች እና ዝቅተኛ ዋጋ አምራቾች ጋር መወዳደር ለኢትዮጵያ ተኪ ምርቶች ከባድ ፈተና መሆኑን ነው አስተያየታቸውን የሰጡት።

እነዚህ መሰናክሎች ቢኖሩም ኢትዮጵያ ለተኪ ምርቶች እምቅ አቅም አላት። እያደገ ያለው የሀገሪቱ የሕዝብ ብዛት ለሀገር ውስጥ ምርቶች ትልቅ የገበያ ዕድል ይፈጥራል። የኢትዮጵያ የግብርና ዘርፍ እሴት ለተኪ ምርቶች መሠረት ሆኖ ሊያገለግልም ይችላል ያሉት አቶ ኃይለመስቀል፤ መንግሥት ለኢንዱስትሪ የሰጠው ትኩረት ለተኪ ምርት ልማት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ነው ያብራሩት።

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታው አቶ ታረቀኝ ቡሉልታ እንደገለጹት፤ መንግሥት የተኪ ምርት ስትራቴጂ ቀርጾ ወደ ሥራ ከገባ በኋላ ለዜጎች ተጨማሪ የሥራ ዕድል ከመፍጠር በተጨማሪ አምራች ኢንዱስትሪዎች አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀሙ በር መክፈቱን አብራርተዋል።

ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች ለመተካት ባለው ሂደት አምራች ኢንዱስትሪዎች ከዚህ በፊት ያልተጠቀሙባቸውን አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እንዲጠቀሙ አድርጓል ያሉት አቶ ታረቀኝ፤ የፀጥታ ኃይል እና የተማሪዎች የደንብ አልባሳት፣ የቢራ ብቅልና ስማርት ፖል ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ ተመርተው ለውስጥ ፍጆታ እየዋሉ መሆኑን በአብነት ይጠቅሳሉ።

እንደ ምጣኔ ኃብት ባለሙያው አቶ ኃይለመስቀል ጋዙ ገለፃ፤ የተኪ ምርቶችን ማምረት በተለይ በማኑፋክቸሪንግ እና ተዛማጅ ዘርፎች የሥራ ዕድል ከመፍጠሩም በላይ ፈጠራን እና የቴክኖሎጂ እድገትን ሊያነቃቃ ይችላል። ይህም በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ሸቀጦች በስፋት እንዲመረቱ ያደርጋል ይላሉ።

ይህም የተኪ ምርቶች ለኢኮኖሚ ብዝኃነት የሚያደርጉትን አስተዋፅዖ ያጠናክራል ያሉት አቶ ኃይለመስቀል፤ የተኪ ምርት ስትራቴጂዎችን በተሳካ ሁኔታ መተግበሩ በውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ያለውን ጥገኝነት እንደሚቀንስ ያስረዳሉ።

የኢትዮጵያ መንግሥት የሚከተሉት ጉዳዮች ላይ በትኩረት ሊሠራ ይገባል። መንግሥት ባለሃብቶች በተኪ ምርት ላይ ኢንቨስት እንዲያደርጉ የታክስ እፎይታና ድጎማዎችን መስጠትና ሌሎች ማበረታቻዎችን ተግባራዊ ማድረግ አለበት ያሉት አቶ ኃይለመስቀል፤ መንግሥት የሠለጠነ የሰው ኃይል ለመገንባት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ ኢንቨስት ማድረግ አለበት የሚል ሀሳብም ሰንዝረዋል።

በተለይ ተግባር ተኮር ሙያዊ ሥልጠናዎች ላይ ልዩ ትኩረት ሊያደርግ ይገባል። ከዚህም ባለፈ የትራንስፖርት፣ የኢነርጂ እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሠረተ ልማትን ሊያሻሽል ይገባል ያሉት አቶ ኃይለመስቀል፤ የመንግሥት የንግድ ፖሊሲዎች ለሀገር ውስጥ ምርቶች ከለላ የሚያደርጉ መሆን እንዳለባቸውም ተናግረዋል።

እነዚህንም የጥበቃ እርምጃዎችን፣ ውድድርና ፈጠራን ከሚያበረታቱ ፖሊሲዎች ጋር ማመጣጠን ያስፈልጋል ያሉት አቶ ኃይለመስቀል፤ በሂደት የሚያ ጋጥሙ ተግዳሮቶች በመፍታትና አጋዥ ፖሊሲዎችን በመተግበር ኢትዮጵያ ተኪ ምርቶችን የማምረት አቅሟን በማሳደግ ሀገራዊ ምርትና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ማስመዝገብ ትችላለች ነው ያሉት።

በርካታ ሀገሮች ከውጭ የሚያስገቡትን ምርት በሀገር ውስጥ ለመተካት የሚያስችሉ ፖሊሲዎች አሏቸው። ለአብነት ቻይና ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ ትታወቃለች። ነገር ግን አሁንም ቢሆን ከውጭ የሚገቡ ምርቶች ላይ ያላትን ጥገኝነት ለመቀነስ እየሠራች ነው።

ሕንድንም ብንመለከት ከውጭ የሚገቡ የፋርማሲ ዩቲካል እና የግብርና ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት የሚያስችል ፖሊሲ ያላት ሀገር ነች። ይህ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች የመተካት ተግባር የተለያዩ ሀገራት የፖሊሲ አካሄድ መሆኑን ያሳያል።

ኢትዮጵያም አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያጋጥ ሟቸውን ችግሮች መፍታት ከቻለች በአጭር ጊዜ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች በመተካት የውጭ ምንዛሪ እጥረትን ከመፍታት ባሻገር ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ትችላለች። በዚህም የኢኮኖሚ ዕድገቷ ማስቀጠል የምትችል ይሆናል።

# ድጋፉና ብድሩ ኢኮኖሚው ላይ ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የሚያረጋግጥ መሆኑም ተገልጿል።

በድጋፍ እና በብድር የተገኘው ገንዘብ አሁን ላይ በሀገሪቱ እየታየ ያለውን የውጭ ምንዛሪ እጥረት በመቅረፍ እና የኑሮ ውድነቱን በማረጋጋት ለኢኮኖሚ ዕድገቱ ትልቅ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ይናገራሉ። የተገኘው ገንዘብ ኢኮኖሚው ላይ ተጨባጭ ለውጥ እንደሚያመጣ እሙን ቢሆንም ገንዘቡ ለታለመለት ዓላማ በአግባቡ ካልዋለ ችግሮች ሊያስከትል እንደሚችልም ባለሙያዎቹ ስጋታቸውን ይገልጻሉ።

በሀረማያ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍል መምህር ሀብታሙ ለገሠ፤ የተገኘው የገንዘብ ድጋፍ እና ርዳታ በአግባቡ ጥቅም ላይ ከዋለ የኑሮ ውድነት መቀነስ፣ የዕዳ ጫና ማቅለል፣ የሥራ ዕድል መፍጠር፣ የመንግሥትን ገቢ ማሳደግ እና የኢኮኖሚ እድገት ማምጣት እንደሚችል ይናገራሉ። ብድር ተሠርቶ ትርፍ ተገኝቶበት በተባለለት ጊዜ መከፈል ያለበት በመሆኑ ገንዘቡን በአግባቡ ለታለመለት ዓላማ ማዋል የግድ እንደሚልም ያስረዳሉ።

አቶ ሀብታሙ እንደሚሉት፤ መንግሥት በብድር እና በድጋፍ ካገኘው የውጭ ምንዛሪ ላይ የተወሰነውን ኢትዮጵያ ውስጥ እየሠሩ ላሉ ባንኮች ማከፋፈል አለበት። ከዚህ በፊት ባንኮች አስመጪዎች በሚፈልጉት መጠን የውጭ ምንዛሪ ማቅረብ ስለማይችሉ ጥቂት የማይባሉ አስመጪዎች የውጭ ምንዛሪ ከጥቁር ገበያ ይገዛሉ። ባንኮች በየዕለቱ በሚተመነው የውጭ ምንዛሪ ዋጋ መሠረት አስመጪዎች በሚፈልጉት መጠን የውጭ ምንዛሪ ማቅረብ ከቻሉ የተገኘው ገንዘብ የኑሮ ውድነቱን በማረጋጋት ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል።

መንግሥት የተገኘውን ገንዘብ ተጠቅሞ ኢትዮጵያ ውስጥ የግሉ ዘርፍ በሚፈለገው መጠን ባልተሰማራባቸው ዘርፎች ላይ ኢንቨስት ማድረግ እንዳለበት በመጥቀስ፤ ኅብረተሰቡ በሚፈልጋቸው እንደ ምግብ ዘይት ያሉ ፋብሪካዎችን በመገንባትና ከውጭ የሚገባውን ምርት በመቀነስ የዋጋ ንረቱን ማረጋጋት እንደሚቻልም ይመ ክራሉ።

ከውጭ ሀገራት እየገቡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ዋጋቸው እየጨመረ የመጡ የኅብረተሰቡ የእለት ተእለት መጠቀ ሚያዎችን መንግሥት ቢያመርት እጥረቱን መቅረፍ እንደሚቻል ያመለክታሉ። የግሉ ዘርፍ በዘርፉ ለመሰማራት ፍላጎት ሲያሳይ መንግሥት ፋብሪካዎቹን መልሶ በውጭ ምንዛሪ በመሸጥ ዕዳውን መክፈል እንደሚችልም ያብራራሉ። ምርት በመጨመር እና የሥራ ዕድል በመፍጠር እንዲሁም ከሀገር ውጭ የሚገቡ ምርቶችን በመቀነስ የውጭ ምንዛሪ መቆጠብ እንደሚቻልም ይጠቅሳሉ።

መንግሥት ከሚያገኘው ድጋፍ እና ብድር ላይ ለነዳጅ ድጎማ በማዋል የማኅበረሰቡን ጫና መቀነስ ላይ መሥራት እንዳለበት የሚገልጹት ምሁሩ፤ መንግሥት በውጭ ምንዛሪ የሚያደርገው አነስተኛ ድጎማ የማኅበረሰቡን ኑሮ በእጅጉ እንደሚያግዝም ያብራራሉ።

መንግሥት የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶችን ጨምሮ ሀገር ውስጥ በቀላሉ ሊመረቱ የሚችሉ ቁሳቁሶችን ማስመጣት ማቆም እንደሚኖርበት ተናግረው፤ ካልሆነ የተገኘውን የውጭ ምንዛሪ ያለአግባብ ተጠቅሞ ዕዳ ማትረፍ እንደሚሆን ስጋታቸውን ይገልጻሉ።

ለአምራቾች የሚያስፈልጋቸውን የውጭ ምንዛሪ በመስጠት ጥሬ እቃዎች፣ መለዋወጫ እና ማሽነሪ እንዲያስገቡ በማድረግ አምራች ተቋማቱ ለሀገር ውስጥ ምርት እና ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡት ምርት እንዲጨምር ቢያደርግ መልካም መሆኑን አቶ ሀብታሙ ይመክራሉ። ይህ ከሆነ ሌሎችም እነሱን በመመልከት ወደ አምራች ኢንዱስትሪው እንዲመጡ ዕድል እንደሚፈጥር ያስረዳሉ። በአጠቃላይ የተገኘው ብድር ምርትና ምርታማነትን የሚጨምሩ ተግባራት ላይ መዋል እንዳለበት ይጠቁማሉ።

ብዙ የአፍሪካ ሀገራት ከዓለም አቀፍ አበዳሪ ድርጅቶች የተበደሩት ብድር በመዝባሪዎች ተመዝብሮ ተመልሶ ወደ ውጭ ሀገራት እንደሚወጣ ጠቁመው፤ አሁንም መንግሥት የተገኘውን የውጭ ምንዛሪ በአግባቡ ጥቅም ላይ ውሎ ኢኮኖሚው ላይ አዎንታዊ ለውጥ እንዲያመጣ ሙስናን መከላከል ላይ አተኩሮ መሥራት እንዳለበት ይናገራሉ። በድጋፍ እና በብድር የተገኘው የውጭ ምንዛሪ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን የሚከታተል እና ኦዲት የሚደርግ ግብረ ኃይል ማቋቋምም እንደሚያስፈልግ ይጠቁማሉ።

እንደ አቶ ሀብታሙ አባባል፤ የተገኘው ድጋፍ እና ብድር በአግባቡ ጥቅም ላይ ከዋለ የዋጋ ግሽበትን ያረጋጋል። የተገኘው ድጋፍ እና ብድር ለታለመለት ዓላማ ካልዋለ እና በአግባቡ ካልተተገበረ የብር የመግዛት አቅም የሚያሽቆለቁል በመሆኑ የኑሮ ውድነቱን በእጅጉ ያባብሰዋል።

እንደ አርጀንቲና እና ብራዚል ያሉ ሀገራት ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ገንዘብ ከተበደሩ በኋላ በአግባቡ ማስተዳደር ባለመቻላቸው በሀገራቱ ያለው የዋጋ ግሽበት እንዲጨምር አድርጓል። መንግሥት ኢኮኖሚው ላይ እያደረገ ያለው ማሻሻያ ውጤታማ እንዲሆንም የሀገሪቷን የውስጥ ሠላም ማስጠበቅ ላይ አተኩሮ መሥራት አለበት ነው ያሉት።

በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የገበያ አስተዳደር መምህር እና ተመራማሪ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ቡርጂ በበኩላቸው፤ የተገኘው ድጋፍ እና ብድር የሥራ ዕድል በመፍጠር እና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በመሳብ ኢኮኖሚው ላይ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል እንደሆነ ይገልጻሉ።

ገንዘቡ ገበያው ላይ በሚገባ እንዲንቀሳቀስ ሠላም ወሳኝ መሆኑን የሚናገሩት ፕሮፌሰሩ፤ መንግሥት የውስጥ ሠላም ላይ በሚገባ በመሥራት ገበያውን ማረጋጋት አለበት ይላሉ።

በድጋፍ እና በብድር የተገኘውን የውጭ ምንዛሪ መንግሥት ለባንኮች እንዲያከፋፍል አቅም ስለሚሰጠው ጥቁር ገበያን ለመቆጣጠር እንደሚያስችልም ያስረዳሉ። መንግሥት የውጭ ምንዛሪ ለባንኮች ሳያከፋፍል አሁን ላይ ባንኮቹ በቂ ምንዛሪ ሳይኖራቸው እለታዊ የውጭ ምንዛሪ መግዣ እና መሸጫ ዋጋቸውን መጨመራቸው ገበያው ላይ አለመረጋጋት እንደሚፈጥር ይጠቅሳሉ።ባንኮቹ መንግሥት የሚሰጣቸውን የውጭ ምንዛሪ መጠን አውቀው ዋጋ ማውጣት እንዳለባቸው ያስረዳሉ።

በጥረት የተገኘው ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሪ በአግባቡ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል መንግሥት ብልሹ አሠራሮችን ማሻሻል አለበት የሚሉ ፕሮፌሰር ብርሃኑ፤ መንግሥት ገንዘቡ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል እና በግለሰቦች እንዳይመዘበር ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ እንዳለበት ይናገራሉ። መንግሥት ገንዘቡን በአጫጭር እና ትርፋማ ፕሮጀክቶች ላይ እንዲያተኩርም ይመክራሉ። ይህን ሲያደርግ የታሰበውን የኢኮኖሚ ለውጥ በአጭር ጊዜ ማሳካት እንደሚቻልም ነው የገለጹት።

ምሁራኑ ብድሩና ድጋፉ በመጪዎቹ ዓመታት የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ ዕድገት ከማስቀጠል ባለፈ የውጭ ምንዛሪ እጥረትን በዘላቂነት በመፍታት የተረጋጋ ኢኮኖሚ ያሰፍናል ሲሉ ሀሳባቸውን ቋጭተዋል።

# አገልግል

## የቅዳሜ መጽሔት

የውስጥ ገጾች

“ልመናን፣ ተመጽዋችነትንና የበታችነትን የሚጠየፍ ትውልድ መፍጠር የጋራ ኃላፊነት ነው”

-ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ
የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የፕሬዚዳንቱ ልዩ አማካሪ



ገጽ 7



በእንጨት ሥራ የተካነው የጅማ ነዋሪው ወጣት

ገጽ 10



እዮስያስ ልበ-ሙሉ ብሳቴና ...

ገጽ 16

# ነፃ ሃሳብ

# የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ትግበራው ከውዥንብር የጠራ እንዲሆን

ሰው መሆን

ባለፉት አምስትና ስድስት ዓመታት ውስጥ መንግሥት ትልልቅ ሀገራዊ ውሳኔዎችን ሲወስንና የፖሊሲ ማሻሻያዎችን ሲያደርግ ቆይቷል። በተለይ የሀገሪቱን ምጣኔ ሀብት በማሻሻል «ዜጎችን ከድህነት ሀገርንም ከኋላቀርነት ይታደጋሉ» ተብሎ የሚታመንባቸው የግብርና፣ የትምህርት፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እንዲሁም የማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች ላይ ስር ነቀል ሊባል የሚችሉ መዋቅራዊ ማሻሻያዎች ተደርጓል።

እነዚህ ግዙፍ ውሳኔዎች ጨከን ያሉ የአመራር እርምጃዎችን የጠየቁ፣ ቆየት ያሉ አስተሳሰቦችና ልማዶችን ለመቀየር ትግል የገጠማቸው ይሁኑ እንጂ የረጅም ጊዜ ውጤታቸውና ፍሬያማነታቸው የዛሬ ውሳኔያችንን እንድናመሰግን የሚያደርጉ መሆናቸው አያጠራጥርም።

የኢትዮጵያን መፃኢ እድል የሚወስኑ፤ ድፍረት እና ሰከን ያለ የአመራር ውሳኔ የሚሹ ውሳኔዎች አሁንም ከፊታችን ተደቅነዋል። የሀገሪቱ መንግሥትም ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ ለእነዚህ መሰል እርምጃዎች ቁርጠኛ አመራር እየሰጠ መሆኑንም እየተመለከትን ነው። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን የሰሞኑ የማክሮ ኢኮኖሚ መዋቅራዊ የፖሊሲ ማሻሻያ ነው።

በመግቢያዬ ላይ ላነሳኋቸው የኢኮኖሚ ምሰሶዎች ይህ የመንግሥት እርምጃ በርካታ እድሎችን ይዞ መምጣቱን የዘርፉ የኢኮኖሚ ምሁራን ውሳኔውን ተከትሎ በሰጡት ምክረ ሃሳቦች ላይ በስፋት ሲነሳ አድምጠናል። በዋናነት ግን መዋቅራዊ ለውጡን፣ የሕግና የፖሊሲ ማሻሻያ ውሳኔዎቹን ተከትሎ በማህበረሰቡ ዘንድ ብዥታ እንዳይፈጥር፣ የዋጋ ግሽበት እንዳይባባስ፣ ወደ አዲስ የንግድና ግብይት ሥርዓት ሲገባ በሚኖር አለመረጋጋት በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ዜጎች ቀጥተኛ ተጎጂ እንዳይሆኑ ከፍተኛ የጥንቃቄ እርምጃዎች መውሰድ እንደሚገባ ነው። ይህ ቁልፍ ጉዳይ የራሱ የፖሊሲ አውጪው አካል ቀዳሚ አጀንዳ መሆኑንም ውሳኔው ይፋ በተደረገበት ወቅት በተሰጠ ዝርዝር መግለጫ ላይ በግልፅ ተቀምጦ ተመልክቻለሁ።

ኢትዮጵያ ረዘም ላሉ ዓመታት ቅድመ ዝግጅት ስታደርግበት የቆየችውና ከሰሞኑ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ይፋ የተደረገው የማክሮ ኢኮኖሚ መዋቅራዊ የፖሊሲ ማሻሻያ (በተለይ የወቅቱን ገበያ ባገናዘበ በውጭ ምንዛሬ ተመን floating exchange rate እንዲመራ መወሰኑ) የሀገሪቱንና የዜጎችን ጥቅም ከማስጠበቅ አኳያ ዘላቂና አዎንታዊ ለውጥ እንደሚያመጣ ይጠበቃል።

ይሁን እንጂ «የደፈረሰው እስኪጠራ» በፖሊሲው ላይ ሁለንተናዊ ግንዛቤ እስኪፈጠር ድረስ እዚህም እዚያም የሚፈጠሩ መደናገሮች እንደሚያጋጥም የሚታመን ነው። በዛሬው ርእስ ጉዳይ ላይ በስፋት ላነሳው የወደድኩት ይህንኑ ጉዳይ ሲሆን ከዚህ እንደሚከተለው ዝርዝር ጉዳዮችን እዳስሳለሁ።

መንግሥት ይንን ታሪካዊ ውሳኔ ሲያስተላልፍ እንደገለጸው የማክሮ ኢኮኖሚ የፖሊሲ ማሻሻያው ብሄራዊ ጥቅምን ያገናዘበና ቀጣይ የሀገሪቱን የእድገት አቅጣጫ የሚወስን ነው። እንደሚታወቀው ማንኛውም አይነት ፖሊሲም ይሁን ሕግ ሲደነገግ ቅድሚያ የሚሰጠው ብሄራዊ ጥቅም ነው። ይህ ደግሞ በቀጥታ ከዜጎች በተለይ ደግሞ የሀገር ባለቤት ከሆኑት ብዙኃን ጥቅም ጋር የተሳሰረ መሆኑ እሙን ነው።

የምንዛሬ ተመን በገበያው እንዲወሰን ሲደነገግ የዋጋ ንረትን ለማስተካከል እና ጤናማ የግብይት ሥርዓትን ለማስፈን እንደሚያስችል የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ይናገራሉ። ሆኖም ግን የመጫወቻ ሜዳው ጤናማ እንዲሆን የተረጋጋና ህግን የተከተለ ውድድር እንዲሰፍን መንግሥት በተቋሞቹ ጠንካራ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል።

የፖሊሲ ማሻሻያውን ይፋ ያደረገው መንግሥት የዜጎችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ክትትል እንደሚያደርግ ነግሮናል። ይህ እቅድ ከወረቀት ላይ አልፎ ተግባራዊ እርምጃዎችን የሚጠይቅ ነው። ፖሊሲው ተግባራዊ ከተደረገበት እለት አንስቶም ተቋማቱ አፈፃፀሙንና ተግባራዊነቱን መከታተል መጀመር አለባቸው።

ብዙውን ጊዜ ፖሊሲዎች መሬት ላይ መውረድ የሚሳናቸውና ኅብረተሰቡ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የሚፈጥሩት በክትትልና ቁጥጥር ማነስ እንደሆነ ይነገራል። ብልሹ አሰራርና ሙሰኝነት ሲታከልበት ደግሞ ከድጡ ወደ ማጡ ነው። በመሆኑም ሀገርን መፃኢ እድል የሚወስን እና ከፍተኛ ጥንቃቄን የሚሻ ይህን መሰል የፖሊሲ ትግበራ በተቀናጀ ተቋማዊ አሰራርና በጠንካራ አመራር ሰጪነት ሊደገፍ ይገባል።

መንግሥት ለማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያ ትግበራ ቀጥተኛ ሚና ይኖራቸዋል ያላቸውን ተቋማት ለይቶ ማስቀመጡን ውሳኔውን ባሳለፈ ማግስት ነግሮናል። ከተቋማቶቹ ውስጥ ብሄራዊ ባንክ፣ የገንዘብ ሚኒስቴር እና የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ናቸው። ፖሊሲውን በማውጣትና በማስተግበር ሂደት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎና ድርሻም መለየቱን ሰምተናል። ይሁን እንጂ ተቋማቱ ከመንግሥት ጋር ከሚኖራቸው ቀጥተኛ ግንኙነት ባሻገር የሕዝብ ግንኙነት መረባቸው የተሰናሰለና ውጤታማ መሆን አለበት።

ምክንያቱም አብዛኛው ማህበረሰብ ጓዳ ድረስ የሚገባ ይህ ውሳኔ «ምን በጎና አሉታዊ» ተፅእኖ እንደሚኖረው በተከታታይ መረጃ በመስጠት ኅብረተሰቡን ማንቃትና ማስተማር ይኖርባቸዋል። የነፃ ገበያ ሥርዓቱ የሚመራበትን ሕግና ሥርዓት ሁሉም ዜጎች ጠንቅቀው እንዲረዱት ለማስቻል ተቋማቱ በተናጠልና በቅንጅት መስራት ይጠበቅባቸዋል። ሁሉም ዜጎች በንግድ ሥርዓቱ እኩል ተጠቃሚና ተወዳዳሪ የሚሆኑበትን ሀብትና ንብረት የሚያፈሩበት መደላደል መዘርጋቱን በክትትልና ቁጥጥር የማረጋገጥ ኃላፊነትም አለባቸው።

አባቶቻችን «እንቅልፍ ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም» የሚል ብሂል አላቸው። ተወደደም ተጠላም በዓለም አቀፍ ውድድር ውስጥ መሆናችንን መዘንጋት የለብንም። በዚህ ሉዓላዊ ዓለም ላይ ጠንካራ፣ ሉዓላዊና ያደገች ሀገር መገንባት ካሻን የኢኮኖሚ ፖሊሲዎቻችንን ማሻሻል የግድ ይለናል። አሁን ያለው መጫወቻ ካርድ ደግሞ የሚያመለክተን የነፃ ገበያ መርህን የሚከተል፣ በተለይ ደግሞ የውጭ ምንዛሪ ተመንን የወቅቱን ገበያ መሠረት ያደረገ ነው። ለዚህ ደግሞ መንግሥት ወቅቱን አገናዝቦ ማሻሻያ እና ውሳኔ አሳልፏ። በመሆኑም ውሳኔውን በበጎና አዎንታዊ ልቦና ተቀብሎ ለአፈፃፀሙ ስኬታማነት መስራት የተሻለው አካሄድ ይሆናል።

በእርግጥ ከላይ በዝርዝር ለማስቀመጥ እንደሞከርኩት በውሳኔው እና በፖሊሲና ሕግ ማሻሻያው ተጋላጭ የሚሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች መኖራቸው የማይካድ ነው። ለእነዚህ ዜጎች ግን መንግሥት ከለላ ለማድረግ ከወዲሁ ዝግጅት ማድረጉን ነግሮናል። ይህንን እንደ በጎ ጅምር መውሰድ ይኖርብናል። ካለፉት ጊዜያት ተሞክሮዎች ለመረዳት እንደምንችለው በተለያዩ ጊዜዎች የሚወጡ ሕጎችን ተከትለው የማህበረሰቡን ጥቅም የሚጎዱ እንዲሁም ብልሹ አሰራርን በመዘርጋት ሕግና ሥርዓትን ለመጠምዘዝ የሚጥሩ ሕገወጦች መኖራቸውን ነው። እነዚህን አካላት በየጊዜው ተከታትሎ እርምጃ መውሰድ ደግሞ የመንግሥት ተቋማት ድርሻ ነው።

ከሕገ ወጦች ባሻገር በራሱ በፖሊሲው ለውጥ ምክንያት የሚፈጠርን ክፍተት ለማረቅና የዜጎችን ተጋላጭነት ለመቀነስ የሚያስችሉ ተግባራት መሬት እንዲነኩ ለማስቻል መንግሥት የወሰደው ቁርጠኝነት መልካም ነው። ይህ ውሳኔም ከወረቀትና እቅድ ባሻገር መሬት መንካት ይኖርበታል። በተለይ የማኅበራዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራሞች ድጎማ የማድረግ ሃሳቡ ከወዲሁ በተቀናጀ መንገድ መሬት መንካት ይኖርበታል።

መንግሥት «የማክሮ ኢኮኖሚ መዋቅራዊ የፖሊሲ ማሻሻያውን ተከትሎ ለዝቅተኛ ደመወዝ ተከፋይ የመንግሥት ሰራተኞች የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያዎቹ ሊያስከትሉ ከሚችሉት የአጭር ጊዜ አሉታዊ ተጽዕኖዎች ለመጠበቅ አስፈላጊ የደሞዝ ድጎማና ማሻሻያዎች ለተወሰኑ ጊዜያት ይደረጋሉ» የሚል ቃል ውሳኔውን ባስተላለፈበት እለት አያይዞ ነግሮናል። ይህ ውሳኔ ለማህበረሰቡ እፎይታን የሚሰጥ ነው።

ብዥታውን አጥርቶ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም ባስከበረ መልኩ ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግም እንደ አንድ መንደርደሪያም ይሆናል። በመሆኑም ከቃል ያለፈ ፈጣን ውሳኔ ማሳለፍ አስፈላጊ ነው። ይህ ወሳኔ ተግባራዊ በሚደረግበት ወቅት የዋጋ ግሽበት እንዳይፈጠር ገበያው የተረጋጋ እንዲሆን መስራትም ተገቢ ይሆናል። በተለይ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪውን መንግሥት በከፊል የሚደጉም መሆኑን ማሳወቁ ገበያው ላይ በፍጥነት ያልተጠበቀ ማሻቀብ እንዳይኖርና የኢኮኖሚ ስብራት እንዳያጋጥም አጋዥ ይሆናል። ይህን መሰል የተመረጠ ስልታዊ እርምጃዎችን መውሰድ የታለመውን ግብ ለመምታት ያግዛል።

**መንግሥት ይንን ታሪካዊ ውሳኔ ሲያስተላልፍ እንደገለጸው የማክሮ ኢኮኖሚ የፖሊሲ ማሻሻያው ብሄራዊ ጥቅምን ያገናዘበና ቀጣይ የሀገሪቱን የእድገት አቅጣጫ የሚወስን ነው**

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ሂደት ቀጣይነት ያለው ግምገማ እንደሚደረግበት መንግሥት አስታውቋል። ይህ ውሳኔም ያልተጠበቁ ክስተቶች በሚኖርበት አጋጣሚ ማስተካከያዎችን ለማድረግ የሚረዳ ነው። ይህም ማለት አንዴ የወጣ ሕግ አሊያም የፖሊሲ ማሻሻያ የማይቀየር አሊያም የማይሻሻል እንዳልሆነ ያስገነዝበናል። በመሆኑም የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም የሚጎዳ ከሆነ ከነባራዊው ሁኔታ ጋር ተገናዝቦ ማሻሻያ እንዲደረግበት መንግሥት ያለውን ቁርጠኝነት ማሳየቱ በበጎ መልኩ ልንወስደው ይገባል።

በመጨረሻ ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ ምቹ አጋጣሚን ተጠቅመው የግል ፍላጎታቸውን ለመፈፀም ከላይ እታች የሚሯሯጡ ሕገወጦችን በተቋማዊ ቅንጅት መከላከል ነው። እነዚህ አካላት ማንኛውንም የመንግሥት ውሳኔ በሚተላለፍበት፣ ሕግና ፖሊሲ ተግባራዊ በሚሆንበት ወቅት ሕገወጥ አካሄዶችን ለመከተል ማድባታቸው አይቀርም።

በእርግጥ በዚህም ረገድ መንግሥት የራሱን ዝግጅት ማድረጉንና «የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያውን ሂደት ተከትሎ በኢኮኖሚው ውስጥ ሊከሰት የሚችለውን የመልካም አስተዳደር ብልሹነት እና ሕገ ወጥነት ለመከላከል የነቃ ቁጥጥር በማድረግ ርምጃ ይወስዳል» በማለት ለበሽታው ማርከሻ ማዘጋጀቱን ነግሮናል። ይህ የጥንቃቄ ዝግጅት ግን ከኅብረተሰቡ ሙሉ ለሙሉ ድጋፍን የሚሻ ነው።

እንደሚታወቀው ሕገ ወጥነትን በመንግሥት መዋቅር ብቻ መቆጣጠር አይቻልም። በዚህ ድርጊት ላይ የመንግሥትን ስልጣን አላግባብ የሚጠቀሙ ሙሰኞች ሲታከሉበት ደግሞ ውጤቱ የከፋ ይሆናል። በመሆኑም የመንግሥትና የኅብረተሰቡ ቅንጅት በእጅጉ አስፈላጊ ይሆናል። እያንዳንዱ ዜጋ የማክሮ ኢኮኖሚው ትግበራ ጓዳው ድረስ ተፅእኖ እንደሚኖረው አውቆ በሕገወጥ መልኩ ሂደቱ እንደይሳካ የሚያስተጓጉሉ ደላሎች፣ ነጋዴዎችና ሙሰኛ ባለስልጣናትን የማጋለጥ፤ ሕግና ሥርዓት እንዲሰፍን ተባባሪ መሆን ይጠበቅበታል። ከሁሉም በላይ ግን የፖሊሲ ትግበራው ውጤታማነት እያደር የሚታይና በአንድ አዳር በጎ ለውጥን እንደማያመጣ ተረድቶ በትእግስት መጠበቅ የዜጎች ኃላፊነት ይሆናል።

**ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች**

# የዘመን እንግዳ

## “ልመናን፣ ተመጽዋችነትንና የበታችነትን የሚጠየፍ ትውልድ መፍጠር የጋራ ኃላፊነት ነው”



-ኡስታዝ አቡበክር አሕመድ

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የፕሬዚዳንቱ ልዩ አማካሪ

አስቴር ኤልያስ

የትውልድ ስፍራቸው ደሴ ከተማ መሃል ፒያሳ ነው፡፡ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የፕሬዚዳንቱ ልዩ አማካሪ ናቸው፡፡ ገና ከልጅነት ጊዜያቸው ጀምሮ የተለያዩ መፍትሔ የሚሹ ጉዳዮች ላይ ኃላፊነት በመውሰድ ውጤታማ ሥራ በመሥራት ዛሬ ላይ ደርሰዋል፡፡ ከልጅነታቸው ጀምሮም ተሰሚነት ያላቸው በመሆናቸው በብዙ ቦታዎች ላይ ግንባር ቀደም ሆነው የሚገኙ ናቸው - የዛሬው እንግዳችን ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ፡፡

እንግዳችን፣ ከወጣትነታቸውም ጀምሮ ችግር ባለበት ጊዜ ሁሉ በመገኘት ሰላም እንዲሰፍን ትልቅ ሚና ሲጫወቱ ኖረዋል፡፡ በሙስሊሙ ማኅበረሰብ በሚኖሩ የመብት ጥያቄዎች በመሳተፍ ረገድ ፊተኛው መስመር ላይ የሚገኙ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ለዓላማቸውና ለነጻነት እስከመታሰር ድረስ መስዋዕትነት ከፍለዋል፡፡

በተለያዩ ኢስላማዊ ድርጅቶች ውስጥ በመስራችነትና በቦርድ አባልነትም ይታወቃሉ፡፡ ለዚህ ሁሉ መልካም እንቅስቃሴያቸውና በሕይወታቸው ሕልም እንዲኖራቸው ያደረጓቸው አባታቸው ሲሆኑ፤ በሚያከናውኑት የተለያዩ ተግባራት ውስጥ ትልቅ ሚና አላቸው፡፡ የዛሬው እንግዳችን፣ ከልጅነታቸው ጀምሮ ከእውነተኛነትና ከታማኝነት ፈቀቅ ብለው አያውቁም፡፡ በሀገራቸው ላይ ያላቸው አቋምም ቀጥተኛና ግልጽ በመሆኑ አዲስ ዘመን በኢትዮጵያ ጉዳይ የዛሬው እንግዳ አድርጎ አቅርቧቸዋል፡፡ መልካም ንባብ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ አንገቷን ቀና የምታደርግባቸው በርካታ ታሪኮች አሏት፤ ከዚህ ውስጥ ዓድዋ ተጠቃሽ ነው፤ በአንጻሩ ደግሞ አንገቷን የሚያስደፉት እንደርዳታ መጠበቅና ልመና አይነት ታሪክ አላት::እነዚህን ሁለት ጉዳዮች እንዴት ያይዋቸዋል ?**

**ኡስታዝ አቡበከር፡-** እንደ ሀገር በተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ አልፈናል:: ዓድዋ የአንድነት፣ የከፍታና የድል ታሪካችን ነው:: ታሪክ በራሱ የከፍታም የዝቅታም ሊሆን ይችላል:: እንዲያ ሲባል ታሪክ በዘመናት ውስጥ የሚያልፉ ትውልዶች መገለጫ ነው ማለት ይቻላል:: ትውልድ በሚሰራው ሥራ ልክ ከፍታን እንደሚያገኝ ሁሉ ከዚያ ተቃራኒ በሆነው ዝቅታ ውስጥም ይኖራሉ::

ዓድዋ የድል እና የከፍታ ታሪክ ነው:: እንደማኅበረሰብ ደግሞ የጥንካሬና ብዙ ነገር ያለን መሆኑ ማሳያ ታሪካችን ነው:: ትናንት ለነገአችን የተሻለ እንዲሆን ትልቅ ማሳያ እና መስታወትም ነው:: እኛ ደግሞ የበለጠ አሳምረነው ልናስቀጥልና እኛነታችንን ልንገልጽበት የምንችልበት ነው ብዬ አምናለሁ::

እኔ እንደ አንድ ሙስሊም መምህር የእስልምና አስተምህሮ ውስጥ ኢትዮጵያ ትልቅ ድርሻ አላቸው ከሚባሉ ሀገራት ውስጥ ናት:: እስልምና በፈተናዎች ውስጥ በወደቀ ጊዜ ነብዩ መሐመድ (ሰዐወ) ቅርብ የሚባሉ ቤተሰቦቻቸውንና ወሳኝ የሚባሉ ባልደረቦቻቸውን ወደኢትዮጵያ ምድር ልከዋል:: በዘመኑ ኃያል ከነበሩ ሀገራት መካከል መርጠው ኢትዮጵያ ላይ ባልደረቦቻቸውን ሲልኩ ኢትዮጵያን የመምረጣቸው ምክንያት አንዱ ጠንካራ የፋይናንስ ሥርዓትና ጠንካራ የኢኮኖሚ አቅም የነበራት ሀገር በመሆኗ ጭምር ነው::

ነብዩ መሐመድና ባልደረቦቻቸውን ከዚህ ሀገር ለመውሰድ እጅ መንሻ ይዘው የመጡት እስልምናን የሚቃወሙት የቁሬይሽ አባላት ነበሩ:: ለመጀመሪያ ጊዜ እጅ መንሻን ያልተቀበሉ፤ ጉቦን የተጠየፉ፤ ሰውን በእምነት ነጻነቱና በሃሳብ ነጻነቱ መከበር አለበት ብለው የሚያምኑ መሪ ያለበት ሀገር ነበረችና እንግዶችን ተቀብላ አስተናግዳለች::

ኢትዮጵያ ሰላሟ የተረጋጋ ሀገር ናት:: በኢኮኖሚም ጠንካራናት::ተመጽዋችም የሌላውን ፈላጊም አልነበረችም:: ይህ ደግሞ እንድትመረጥ ያደረጋት መገለጫዋ ነበር:: እሱ እንደ ታሪክና ማንነት ዛሬም ልንኖረውና ልንተገብረው የተገባው:: ይህ ታሪክ በዚህች ምድር ላይ የተተገበረው ከአንድ ሺ 400 ዓመት በፊት ነው:: ትናንት በዚህ መልኩ የከፍታ ታሪክ ያለን ሕዝቦች፤ ዛሬ በእኛ ዘመን፤ ምን ጉዳይ ላይ ነው ያለነው የሚለው ነገር የመጀመሪያው ሃሳቤ ነው::

ስለዚህ ይህ የትናንት የእኛነታችን መገለጫ ነው፡፡፡ ዛሬ ደግሞ የተሻለ ሆኖ መገኘት አሊያም ያንኑ መድገም አለብን:: መልካም ልጅ ማለት የአባቶቹን ስራ የሚደግም ከእነርሱ የተሻለ ሆኖ የሚገኝ ነው:: ከእዛ በታች ከሆነ ልጅነቱም አደጋ ላይ ነው ማለት ይቻላል:: በዚህ መልኩ ያንን ማምጣት የምንችለው በመሥራት እንጂ በማውራት እና በትናንት ታሪክ በመጣላት አይደለም:: እኛ ባልኖርንበትና የታሪክ አካል ባልሆንበት ጉዳይ ላይ እየተጨቃጨቅንና እየተገፋፋን መቀጠል አይኖርብንም:: እየሰራን፤ እየተለወጥን፤ ለሀገርና ለማኅበረሰብ ከፍታ መትጋት አለብን::

ኢትዮጵያን ስሟን ከፍ ማድረግ የሚቻለውና የሚመጥናት ቁመና ላይ እንድትሆን የሚያደርገው በተግባር መንቀሳቀስ ሲቻል ነው:: የሥራ ባህላችን ሊቃኝ የሚገባው ነው:: እንደ ሀገር ያለን እይታችንና ሀገርን ካለችበት ወደተሻለ ስፍራ ለማሸጋገር የምንሰራበት መስመር መስተካከል አለበት የሚል ሃሳብ አለኝ::

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ ከመናቅ የተነሳ ሥራ የለም የሚል አተያይ እንዳላቸው ይነገራል፤ እርስዎ ከዚህ አንጻር የትውልዱን የሥራ ባህል እንዴት ይገልጹታል? ጠንካራ የሥራ ባህል እንዲኖረንስ ምን መደረግ አለበት ይላሉ?**

**ኡስታዝ አቡበከር፡-** መጀመሪያ ከሥራ ባህላችንም በፊት እንደ አንድ ማኅበረሰብ መሥራት መቻል አለብን ብለን ማመን ይገባናል:: ምክንያቱም ለውጥ ማምጣት የምንችለው በጋራ መሥራት ስንችል ነው:: በእስልምና አስተምህሮ ውስጥ በጣም ትኩረት አድርጎ ከሚጠቅሳቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ ከተረጂነት አመለካከት የወጣና የሚሠራ ጠንካራ የሆነ ማንነት ያለውን ሲሆን፤ አስተምሮው፣ ሥራን ወዶ የሠራ ዋጋው ከፍተኛ እንደሆነና እንዲሁም ከፍታ እንደሚኖረው ይገልጸዋል:: ስለዚህም በዚህ መልክ ሥራን ያበረታታል:: ሰዎችን ለሥራ ይገፋል::

በየትኛውም የእስልምና አስተምህሮ ውስጥ ማስተዋል ከተቻለ በምድር ላይ የተላኩ ነብያት ወደ ምድር የሚመጡት የፈጣሪን መመሪያና ኃላፊነት ይዘው ሕዝብን ከፈጣሪ ጋር ለማገናኘት ሲሆን፤ የሚመጡትም በአንድ የሙያ ዘርፍ ብቁ ሆነው ነው:: ለአብነት ያህል ነብያቱ፣ ወይ ነጋዴ ናቸው፤ አሊያም አናጺ፤ ወይም ደግሞ ብረት አቅላጭ ናቸው:: አንድ የሙያ አይነት ያልነበረው ነብይ ምድር ላይ አልተላከም ማለት ይቻላል:: በአንድ ነገር ላይ ስልጡን ያልሆነ ነብይ የለም ማለት ይቻላል:: አብዛኞቹ ነብያት እረኞች ነበሩ:: ሌሎች የሚታወቁበት ፕሮፌሽናል ሥራ እንዳለ ሆኖ ማለት ነው:: እሱ ማለት የሚያሳየው ነገር በሕይወታቸው ውስጥ ውጣ ውረድን መልመድ፣ በተለያዩ ፈታኝ በሆኑ ነገሮች ውስጥ ማለፍ፣ በራስ መተማመን እንዲኖር ማድረግ፣ የሰውን እጅ ጠባቂ እንዳይኖር ማድረግና በራስ ሰርቶ የማደር ስሜት እንዲፈጠርባቸው ማድረግ ነው::

እንደ አማኝ ማኅበረሰብ የመጀመሪያው ነገር መሥራት አለብን የሚለውን ነገር ማመን ነው:: መሥራት አለብን ብለን ካመንን ብዙ ነገር መለወጥ ይቻላል:: ዛሬ ኢትዮጵያ ለማደግ እየተፍጨረጨረች ነው::ስለዚህም ዜጎቿ አብረው ለሥራ መፍጨርጨር አለባቸው::ምክንያቱም ተከፍሏቸው የሚኖሩ እንደስካንዲቪያ ሀገራት ያሉ ዜጎች እንኳ ቢሆን ሰው ሥራ ይሠራል:: ሥራ የሚሠራ ትውልድ ደግሞ የነቃ፣ ተጠያቂነት ያለው፣ ከራሱ አልፎ ለሌላው መኖር የሚችል መሆን ነው:: ሥራ ስንሠራ እኛነታችንን ብቻ አስበን መሥራት የለብንም:: ነገን፣ ትውልድን፣ ማኅበረሰብንና ሀገርን አስበን መሆን አለበት::

ሁሉም ሰው የተለየ የሙያ ዘርፍ ይኖረዋል::በመረጠው ሙያ እንዲሠራ ታዝዟል፤ መሥራትም አለበት:: ምክንያቱም ያለሥራ የሚመጣ ውጤት የለም:: መሥራት አለብን ብለን ካመንን ደግሞ ሥራ እኛ ዘንድ ይጠፋል ብለን አናስብም:: ምክንያቱም በሀገራችን የተጀመሩ እንጂ ያልተጠናቀቁ ሥራዎች ባለበት ሀገር ውስጥ ሥራ የለም ማለት አይቻልም፤ ዛሬ ዛሬ ከሀገር ተሰድደው ሔደው ሥራ የሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ወደ ውጭ ሀገር ሔደው የሚሰሩት ሥራ ኢትዮጵያ እያሉ የናቁት ሥራን ነው:: ለውጡ ምንድን ከተባለ ምናልባት እዛ ክፍያው ከፍ ሊል ይችላል:: ነገር ግን ከታች ተነስቶ ትልቅ ደረጃ መድረስ ይችላል:: ያውም ሰው ሀገር ላይ ሳይዋረዱ፣ በማንነታቸው ሳይሸማቀቁና ሳይገፉ በሀገር ላይ ክብርን አግኝተው መኖር ይቻላል:: የብዙ ሰዎች ሕይወት በዚህ መልኩ እንዳለፈ እናውቃለን፡፡ የሠሩ ሰዎች ውጤት ያገኛሉ::

በሀገራችን የሥራ እድሎች አሉ፤ እንዲያውም ያልተሰራ የሥራ እድል ያለው እኛ ሀገር ነው:: ሌላው ዓለም ላይ ሥራው እያለቀ ነው ማለት ይቻላል:: ታላላቅ ናቸው የተባሉ ሀገራት ላይ ብዙ ነገር ላይ የደረሱ ናቸው፡፡ እኛ ሀገር ላይ ሁሉ ነገር ገና ጅምር ላይ ነው:: ያልተነካ ነው::

እኔ፣ የሃይማኖት መምህር ብሆንም ነጋዴ ነኝ:: ንግዴን እንዴት አድርጌ ላሳድገው? ላስፋው እላለሁ:: ምክንያቱም ዘርፉ ገና ነው፤ ፍላጎቱ ብዙ ነው:: ሀገር ገና እየተገነባ ነው ያለው:: ማኅበረሰብም ገና እያደገ ነው:: ስለዚህ ሥራ የመሥራት ፍላጎት ያለው ከትንሽ ተነስቶ ትልቅ ደረጃ ላይ መድረስ ይችላል:: ከመቀጠር ተነስቶ ትልቅ ቦታ ላይ መድረስ ይችላል:: ነገር ግን ይህ የሚሆነው እኔ የሰው እጅ ማየት የለብኝም፤ መሥራት አለብኝ ብሎ ሲያምን ነው::

ሁልጊዜ ከላይ ያለች እጅ ከታች ካለችው እጅ በላይ በላጭ ናት፤ የሚሰጥ እጅ ከላይ ሲሆን፣ የሚቀበል እጅ ከታች ናት:: ተቀባይነትን የሚጸየፍና የሚጠላ፤ ነገር ግን መሥራት አለብኝ ብሎ ለሌላው የሚተርፍ ማንነት ያለው አስተሳሰብን ካዳበርን ሥራ አልጠፋም::

እንደ ሀገር የከሰርነውና ዛሬም ፈተና ውስጥ የወደቅነው ወጣቱ ለብዙ ችግር ተጋላጭ ሆኖ ነው:: አሁን አሁን የምናስተውለው ሽማግሌ የሆኑ ወጣቶችን ናቸው:: እድሜያቸው የገፉ አባቶች ሲታገሉ እናያቸዋለን:: በወጣትነቱ ደግሞ የሚተኛ፣ በሱስና በተለያየ ነገር ተጠምዶ ተረጂ የሆነ ወጣት ነው:: በዚህች ሀገር ላይ ያለው የሚጦር ወጣት ነው:: አካሉ የወጣት ነው፤ አቅሙ ግን የሽማግሌ ነው:: የተሰጠንን የወጣትነት አቅም በአግባቡ ለጠቀም ከወሰንን ሥራ አልጠፋም፤ እንዲያውም በተቃራኒው ሥራ በጣም ሞልቷል:: እኛ ውስጥ የጠፋው የመሥራት አቅምና ሃሳቡ ነው:: ያንን ማድረግ ካልቻልን ደግሞ ራሳችንን፣ ማኅበረሰባችንንና ሀገራችንን አይለወጥም:: ስለዚህ ሁልጊዜ ተመጽዋች፣ ሁልጊዜ ተረጂ፣ ሁልጊዜ ጡረተኛ ሆኖ የሚኖር ሰው ወጣት የሆነ ሽማግሌ ነው፤ ከክብር ውርደትን መርጧል ማለት ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ብዙ ሀብት ቢኖራትም ኢትዮጵያ ግን ርዳታ በጠበቅም በመለመንም ላይ ናት ፤ በዚህ የምትቀጥል ከሆነ የሚያጋጥመው ነገር ምንድን ነው? መፍትሔውስ?**

**ኡስታዝ አቡበከር፡-** እንደ አንድ ሀገር ሀገራችን ያለችበትን ወቅት መረዳት ተገቢ ነው:: ታሪክ ያለን ሀገር ነን፤ በትናንት ታሪክ ግን አንቆምም:: ትናንት የነበሩ የእኛነታችን መገለጫና ማሳያ የነበሩ ዛሬ ካላደጉ የትንናት ታሪክ ለእኛ ለትውልዱ ዛሬ ላይ ታሪክ አይሆኑም:: ታሪክ የሚሆነው ተምረንበት የተሻለ ነገር ለመሥራት ስንዘጋጅ ነው:: ስለዚህ ከተረጂነት የወጣች ሀገር እንድትኖረን ካስፈለገ እንደ ሀገር ትልቅ ነገር ለመሥራት መዘጋጀት አለብን::

ሁልጊዜ መረዳት ካለ መረገጥ አለ:: ምክንያቱም ረጂ ሀገራት ሁሌም ቢሆን የየራሳቸው ፍላጎት አላቸው:: የሚረዱ ሀገራት የየራሳቸው ሃሳብ አላቸው:: የሚፈልጉትን ነገር ማድረግ፣ ማውጣትና ማውረድ ይፈልጋሉ:: በዚህች ሀገር ላይ ጫና መፍጠር ይሻሉ:: እሱ ነገር እንዳይደርስብን ከፈለገን እኛ ማድረግ ያለብን መሥራት ነው:: ሀገር የምትገለጸው በልጆቿ ነው:: ሀገር የምትገለጸው በዜጎቿ ነው:: ያ ዜጋ በዚህ ስሜት መፈጠር አለበት ብዬ የማምነው የሀገር ፍቅር ሲኖር ነው:: ይህ የሀገር ፍቅር የሚባለው ስሜት ግን አሁን አሁን እየጠፋ የመጣ ይመስለኛል::

በመነሻችን ላይ ዓድዋን እንዳነሳነው በወቅቱ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ከሁሉም የሀገራችን ክፍል ከጫፍ እስከ ጫፍ ተጠራርተው ወደስፍራው አቆራርጠው የደረሱት በእግራቸው ነው:: ያንን ታሪካዊ የሆነ ድል መቀዳጀት የቻሉትም የሀገር ፍቅር ስሜት ስላላቸው ነው:: ዜጋው፣ ሀገር ስትነካ መተኛት ስላቃተውና ጥሪ አለብኝ ብሎ መንቀሳቀስ ስለቻለ ታሪክ መሥራት ቻለ::

የዛሬው ትውልድ ሀገራችን ሁልጊዜ በርዳታና በድጋፍ መኖር የለባትም ብሎ መወሰን አለበት:: ምክንያቱም ሁሌ በድጋፍና በርዳታ የምትኖር ሀገር ካለችን ውርደት እሱ ነው:: እንዲያ የምናደርግ ከሆንን ከከፍታ ውርደትን መርጠናል ማለት ነው፡፡

ሀገር ስትራቴጂ የሚቀረጽለት፣ ሃሳብ የሚወጣለት፣ ወደፊት የሚቀጥልበት ብዙ ስራዎች ይፈልጋል:: ከላይ ከመንግሥት ተቋማት ጀምሮ እስከታች ያለው ማኅበረሰብ፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የማኅበረሰብ መሪዎች፣ ትውልዱም ጭምር የሥራ ባህሉን ማሳደግና ሀገሩን መውደድ መቻል አለበት:: ዜጋው፣ ስለ ሀገሩ፣ ስለትውልዱ፣ ስለነገው

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## “ልመናን፣ ተመጽዋችነትንና የበታችነትን የሚጠየፍ. . .

**ከ7ኛው ገጽ የዞረ**

እንዲኖር ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

ሰው ዛሬን ብቻ ኖሮ የሚያልፍ ፍጥረት መሆን የለበትም፤ ሰው ማለት ለነገ የሚተርፍ እና ለሌሎች ተስፋ መሆን የሚችል ነው፡፡ ሀገሩንና ማኅበረሰቡን ከፍ ማድረግ የሚችልና ያንን ሥርዓት የመለወጥ ኃላፊነት ደግሞ የሁላችንም ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ቤተ እምነቶች ትውልዱን የማንቃት ትልቁን ድርሻ ይይዛሉ፡፡ የሃይማኖት መሪዎችና አባቶች ትልቁን ሥራ የመሥራት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ሊሠሩ የማይወዱ እጆች መኖር እንደማይገባቸው ማስተማር አለባቸው፡፡ ይህ ደግሞ የእምነቱም ግዴታ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

ነብዩ መሐመድ (ሰዐወ) የማይሰሩ እጆችን፣ የሚለምኑ እጆችን የሚያወግዟቸው በዚያ መልኩ ነበር፡፡ እርሳቸው፤ “አላህ ዘንድ ተወዳጅ ባሪያ ማለት በሥራ የደከመ ባሪያ ነው” ይላሉ፡፡ የደከመና የተሰነጣጠቀ እጅ ተመልክተው “የምወዳት እጅ፣ በሥራ የደከመች እጅ” እያሉ ነበር ሰዎችን ያበረታቱ የነበረው፡፡ ሲለምን የመጣን ሰው “እዚህ ለልመና መስጂድ ላይ ከምትቆም በአጥንትህ ወይም በአጽምህ ሰው ፊት ብትቆም ይሻልህ ነበር፡፡” ይላሉ፡፡ ምክንያቱም ይህን የሚሉት ልመና ውርደት እንጂ ክብር እንዳልሆነ ለመግለጽ ነው፡፡

እኛም መሥራት የማንፈልገው ሀገር በዚያ ልክ እንድትዋረድ እና በዚያ ልክ ዝቅ እንድትል ከፈለግን ነው፡፡ ሥራ መሥራት የምንጠላ ከሆነ ደግሞ ውጭ ሀገር ብንሆንም ተከብረን መኖር አንችልም፡፡ የትም ስፍራ ብንኖር ካልሰራን ክብር አይኖረንም፡፡ ሀገራችን በእርዳታ እና በጥገኝነት እንድትኖር ከመረጥን ዜጋው የራሱ የሆነ ማንነት የሌለው፣ የሌሎችን የፖለቲካ ሐሳብና ፍላጎት የሚያስፈጽም አገር እንዲኖረን መርጠናልና አማራጭ የለንም፡፡ መምረጥ ያለብን ከሁለት አንዱን ነው፡፡ ከፍታን ከመረጥን ለዚያ ለከፍታ የሚሆን ሥራ እንደዜጋ፣ እንደ ማኅበረሰብ ኃላፊነታችንን መወጣት ነው፡፡ ውርደቱን ከመረጥን ደግሞ ምርጫችንን የመረጥነው እኛው ራሳችን ስለሆንን ምንም የምንወቅሰውና የምንተቸው አካል መኖር የለበትም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ከውርደትም ከዝቅተኝነትም ስፍራ መውጣት እንድትችል ዜጎቿ ምን ማድረግ አለባቸው? ትውልዱ ልመናን እንዲጸየፍስ ምን ይመክራሉ?**

**ሡስታዝ አቡበከር፡-** እኔ በመጀመሪያ ሁላችንም የድርሻችንን መወጣት አለብን እላለሁ፡፡ እኔ፣ ሀገሬ እንድትኖር የምፈልገው ትናንት በነበራት ቁመና ከዚያም አለፍ ሲል በተሻለ ማንነት ውስጥ ነው፡፡ እንደእስልምና ታሪኬ ደግሞ የተመረጠች፣ ለሰው ዘር መጠጊያ የሆነች፣ ለእምነት ነጻነት ዋስትና የሰጠች ፣ብዙዎችን አክብራ መኖር የቻለች፣ በሰላምም በኢኮኖሚም የተሟላ ዋስትና ያላት ሀገር እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ፡፡ ያ እንዲኖረኝ ግን የእኔ አበርክቶ ምንድን ነው? ብዬ ማሰብ ይጠበቅብኛል፡፡ ወደ እንቅስቃሴ ውስጥም መግባት ይጠበቅብኛል፡፡

የእኛ አስተምህሮ መለወጥ አለበት ባይ ነኝ፡፡ ማኅበረሰቡን ከመቅረጻችን በፊት ጅማሬያችን ከቤት ውስጥ መሆን አለበት፡፡ ልጆቻችን ጤነኛ ሆነው እንዲያድጉ ያለንን ቁርጠኝነት ማጤን ይጠበቅብናል እላለሁ፡፡ ትምህርት ቤት ስናስተምራቸውስ በምን አይነት መልኩ እየተማሩ ነው? የሚለውን ማገናዘቡ መልካም ነው፡፡ እየፈጠርን ያለነው ምን አይነት ትውልድ ነው? መለመንን፣ ውርደትን፣ የበታችነትን፣ መስረቅን ወይም ደግሞ ጉቦን የሚጠየፍ ትውልድ ካልፈጠርን ችግር ነው፡፡ ይህ መሰራት ያለበት ከታች ከቤተሰብ እና ከትምህርት ቤት እንዲሁም ከሃይማኖት ተቋማት በኩል ነው፡፡ ይህን የእምነቱ ኃላፊነት፣ የማኅበረሰቡ ኃላፊነት በጥቅሉ የሀገር ኃላፊነታችን ነው ብለን ማመን አለብን፡፡ ስለዚህም የሁሉም ድርሻ መቀናጀት መቻል አለበት፡፡ ማኅበረሰባችንን የምናገኘው መቼም በሰራነው ልክ ነው፡፡ ያልሞላነውን ከየትም አናመጣውም፡፡ ምክንያቱም የውሃው ማንቆርቆሪያ የተሞላው ውሃ እስከሆነ ድረስ የሚቀዳው ውሃ እንጂ ወተት አይደለም፡፡ ወተት እንዲወጣልን ስንፈልግ ማንቆርቆሪያውን መሙላት የሚጠበቅብን ወተት ነው፡፡ ሁሉም የሚያወጣው ውስጡ ያለውን ነው፡፡

ልመናን፣ ራስን አለመቻልን፣ ተመጽዋችነትንና የበታችነትን የሚጠየፍ ትውልድ መፍጠር የጋራ ኃላፊነት ነው፡፡ በቤተሰብ፣ በትምህርት ቤት፣ በሃይማኖት ተቋማት፣ የማኅበረሰብ መሪዎቻችን በዚያ ልክ ትውልዱን ማነጽና ማስተማር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሰዎች አዕምሯቸው



**ትውልዱ እኛ ያላስተማርነውን ከየትም ማምጣት አይችልም፡፡ ለምሳሌ አባት ቤት ተቀምጦ እያለ “ቤት የለም በል” የሚል አባት ነገ ጠዋት ልጁ ቢዋሸው ለምን ይቀጣዋል? ልጁ የደገመው እሱ ያስተማረውን ውሸት ነው፡፡ ምክንያቱም ያላደገበትን ነገር ከየት ያመጣዋል?**

የሚያድገው በተሰጣቸው ልክ ነው፡፡ ጥሩ ነገር ማግኘት የሚቻለው አዕምሮ በወጉ ሲገነባ ነው፡፡

እኛ ዛሬ ትልቁ ጭንቀታችን ከአንገት በታች ላለው አካላችን ሆነ፡፡ ትልቁን ሥራ ማድረግ እና መልፋት የነበረብን አዕምሮ ላይ ነው፡፡ ወጪም መውጣት የነበረው ከአንገት በላይ ለሆነው የአካል ክፍል ነው፡፡ ምክንያቱም እሱ ሲስተካከል ሁሉም መስተካከል ይችላል፡፡ እኛ ግን በአብዛኛው ክብር የሰጠነው ከአንገት በታች ላለው የአካል ክፍላችን ነው፡፡ ስለዚህ ሁሉም መስተካከል እንዲችል የሁላችንንም ርብርብ የሚጠይቅ ነው፡፡ ያንን መስራት ከቻልን የማይለወጥ ነገር አይኖርም፡፡ ለዚህ ደግሞ ብዙ ማሳያ መጥቀስ ይቻላል፡፡

ለምሳሌ አዲስ አበባ ቀደም ሲል የነበራት ምስልና አሁን ያላት በጣም የተለያየ ነው፡፡ አሁን የመጣውን ለውጥ ከዛሬ ሃያ ዓመት በፊት ማየት አንችልም ነበር፡፡ የተለወጠው አስተሳሰብ ብቻ ነው፡፡ ማድረግ እንችላለን የሚል አመለካከት ሲመጣ ማከናወን ይቻላል ማለት ነው፡፡ ከዚያ የተነሳ ዛሬ አዲስ አበባን በተለየ ቁመና ውስጥ እያየናት እንገኛለን፡፡ ይህንን ትናንትናም ማድረግ ይቻል ነበር፡፡ ነገር ግን አስተሳሰብ ይፈልጋል፡፡ ይህን የሚያቀናጅ እና የሚመራ አካል ይፈልጋል፡፡ ይህን አስተሳሰብም መቀበል የሚችል ትውልድም ይፈልጋል፡፡ የማንችላቸው የሚመስሉን ነገሮች የምንችላቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡ ቀደም ሲልም መሥራት ያልቻልነው አንችልም ብለን ስለመጣን ነው፡፡ አዲስ አበባ ዛሬ ያለችበትን አይነት ቁመና ሌሎቹ ክልሎቻችንም መሆን ይችላሉ፡፡ የሚፈልጉት የማኅበረሰቡን ጥረት ነው፡፡ የሚፈልጉት የጋራ ጥረትን ነው፡፡ ሁሉም የየድርሻውን ከተወጣ የማይቻል ምንም ነገር አይኖርም፡፡

ወደቻይና እና ሌላው አካባቢ ሔደን ብናይ ልጆች በየትምህርት ቤታቸው የሚማሩት ለነገ ሕይወታቸው መሰረት የሚሆነውን ነገር ነው፤ ዛሬ ላይ የሚመገቡበትን ሳህን ራሳቸው እንዲያጥቡ ከማድረግ የሚጀምር ትምህርት ከተማሩ ነገ እንዴት መስራት እንዳለባቸው የሚጠፉቸው አይሆንም፡፡ እናም ሀገራት ልጆች እንዲያድጉ የሚያደርጓቸው በእያንዳንዱ እንቅስቃሴ የሥራ ባህል እንዲኖራቸው ነው፡፡ መሆን ያለበትም ይህ ነው፡፡ የእኛ አስተምህሮ እና ቤተ እምነቶቻችን ይህን ማድረግ ካልቻልን አሁንም ትውልድም ሀገርም እያጣን እንሄዳለንና የሁላችንን ጥረትና ርብርብ የሚፈልግ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በእስልምና አስተምህሮ ሥራ ከመሥራት ጋር ተያይዞ ያለው ጉዳይ የሚገለጸው እንዴት ነው ?**

**ሡስታዝ አቡበከር፡-** በእስልምና አስተምህሮ ውስጥ አስቀድሜ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት፤ ለሥራ የተለየ ቦታ ይሰጣል፡፡ የሰው ልጅ ዝቅ ብሎ እንዲታይ የማይፈልግ ማኅበረሰብ የተሻለ ቁመና ላይ እንዲቆም የሚሻ ነው፡፡ በመሰረቱ ይህች ምድር ስትፈጠር ለሰው ልጅ እንድትጠቅም ነው፡፡ የምንጠቀምባት እኛ ሰዎች ደግሞ ሥራችን መሆን ያለበት ተጠቅመንባት አጥፍተን እንድትሔድ አይደለም፡፡ የሚፈለገው አልምተናት፣ ለውጠናት እና ቀይረናት እንድንሔድ ነው፡፡

ነብዩ መሐመድ (ሰዐወ) በተለዩ መልዕክቶቻቸው ላይ “በሥራ ደክሞ ያደረ እጅ በአላህ ዘንድ የተማረ ነው፡፡” ይላሉ፡፡ አስቀድሜ እንዳልኩት “አላህ የሚወዳት እጅ በሥራ የደከመች እጅ ናት” ይላሉ፡፡ ከሰው ጠባቂ ያልሆነ ከራሱ አልፎ ቤተሰቦቹን የሚደግፍ ነው፡፡ በምንም አይነት መልኩ ለሰው ዝቅ እንዳንል ሥራ የእኛ ኃላፊነት ስለሆነ “ሥራችሁን ሥሩ፤ አላህ ሥራችሁን ይመለከታል፡፡” ሲሉ ነብዩ መሐመድ (ሰዐወ) ገልጸዋል፡፡ ሥራ የአማኞች ባህል ነው፡፡ ለዚህም ነው ነብያት ሳይቀሩ በሥራ ውስጥ እንዲያልፉ የመደረጉ ምስጢር፡፡ አማኝ ሆኖ ይህን የሥራ መንፈስ ያላከበረ እምነቱን አላወቀም፤ አልተረዳምም፡፡ ከእምነቱ ራሱን እንዳገለለና ከእምነቱ ውጪ እንደሆነ ማሳያዎች ናቸው ማለት ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ታላላቆችን የማክበር ባህላችንና ሽማግሌዎችን የመስማት ባህላችን በጣም ደብዝዟል፡፡ እዚህ ላይ የሚሉን ነገር ይኖር ይሆን? የሚመክሩትም ነገር ካለ አይይዘው ቢገልጹልን፡፡**

**ሡስታዝ አቡበከር፡-** ይህ የሆነበት ምክንያቱ የሥራችን ውጤት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ያልዘራነውን አናጭድም፡፡ አስተምህሮቱ መፈተሽና መታየት መቻል አለባቸው፡፡ ብዙ ጊዜ የእምነት አባቶች ጋር ስንገናኝ ቤቶቻችንን ዘግተን ልንነጋገርባቸው የተገቡ ጉዳዮች አሉ ብዬ አምናለሁ፡፡ ይህ ደግሞ የሁላችንም ችግር ስለሆነ ነው፡፡

ወላጅን፣ ታላላቅን አለማክበርና የሚገባቸውን ቦታ አለመስጠት ላይ ነብዩ መሐመድ (ሰዐወ) የተናገሩት ነገር አለ፤ ይኸውም “ታላቁን የማያከብር፣ ለታናሹ የማያዝን ከእኛ አይደለም፣ ከአማኞች ጎራ አይደለም፡፡” የሚል ነው፡፡ ይህ ማለት እንደ ማኅበረሰብ ዛሬ የሃይማኖት አባትን የሚሰድብ፣ መሪን የሚሰድብ፣ ታላቅን የሚሰድብ፣ መምህርን የሚሰድብ ትውልድ ፈጥረናል፡፡ ይህ ትውልድ የወጣው ከማንም አይደለም፤ ከእኛው ከራሳችን የወጣ ትውልድ ነው፡፡ ከእኛው ቤተ እምነት የወጣ ነው፡፡ ማን ቀረጸው? ማንስ አነጸው? ለምን እዚህ ደረጃ ደረስን? ብለን ሌላውን ከመውቀሳችን በፊት መጠየቅ ያለብን እኛው ራሳችንን ነው፡፡

ትውልዱ እኛ ያላስተማርነውን ከየትም ማምጣት አይችልም፡፡ ለምሳሌ አባት ቤት ተቀምጦ እያለ “ቤት የለም በል” የሚል አባት ነገ ጠዋት ልጁ ቢዋሸው ለምን ይቀጣዋል? ልጁ የደገመው እሱ ያስተማረውን ውሸት ነው፡፡ ምክንያቱም ያላደገበትን ነገር ከየት ያመጣዋል? ስለዚህም ነው መከባበሩ እንዲጠፋ እያደረግን ያለነው እኛው ራሳችን በእጃችን በሠራነው ሥራ ነው የምለው፡፡

ለዚህ ደግሞ ቤተ እምነቶች ትልቅ ድርሻ አለባቸው፡፡ ልጆቻችን ምን ላይ ነው ያሉት? ብሎ መፈተሽ፣ ከአስተዳደጋቸው ጀምሮ ማየት ያስፈልጋል፡፡ የምናስተምረው ትምህርት ያረፈው ምን ላይ ነው? ያስተማርናቸው እንዴት አድርገን ነው? ከሙስሊሙ መስጂድ ተነስቶ ክርስቲያኑን የሚሰድብ፤ ከክርስቲያኑ ቤተ ክርስቲያን ተነስቶ ሙስሊሙን የሚሰድብ ነገ ጠዋት ቄሱን እና ሼኪውን ላለመስደቡ ምንም ዋስትና የለውም፡፡ ደግሞም ይሳደባል፡፡ ምክንያቱም ያስተማርነው እኛው ነን፡፡ ሲሳደብ መሳደብ ክልክል እንደሆነ ያልነገርነው እኛ ነን፡፡ ለሌሎች ሲሆን እንደሚፈቀድ አሳይተነዋል፡፡

እስልምናችን ግን የሚለው “የሌሎችን እምነት አትሳደብ፤ የሌሎችን ፈጣሪ አትሳደብ፡፡ የእናንተን ፈጣሪ ይሰድቡባችኋልና ወንጀለኞቹ እናንተ ትሆናላችሁ፤ ምክንያቱም ፈጣሪያችሁ እንዲሰደብ ያደረጋችሁት እናንተ ናችሁና፡፡ ክብሩ እንዲጣስ ያደረጋችሁት እናንተ ናችሁ፡፡ ምክንያቱም የእነርሱን ክብር ባትነኩ ኖሮ የእናንተን ክብር አይነኩም ነበር፡፡ ተጠያቂዎቹ እናንተ ናችሁ፡፡” ይላል፡፡

ስለዚህ በየቤተ እምነቶቻችን እንመለስና እንፈትሽ፤ ትውልዱ አማኙ የት ላይ ነው፡፡ ኅብረተሰባችን የት ላይ ነው፡፡ ልጆቻችን ምን ላይ ናቸው ብለን እንመልከታቸው፡፡ ይህን መሥራት ከቻልን የወደፊታችንን ማስተካከል እንችላለን፡፡ ካልሆነ ግን ከዚህ የከፋ ነገር ይመጣል፡፡ ሰው ሲሰቀል ያየንበት ሀገር ነው፡፡ ወገን ወገኑን ሲያሳድድ እያየነው ነው፡፡ “እኔ ልሙት እንጂ ይህን መጥፎ ተግባር አትፈጽሙም” የሚል ሽማግሌ የጠፋበት፣ የሃይማኖት መሪ የሌለበት ሀገር ነው፡፡ “እኔ ልሙት እንጂ ሀገር ሲጠፋ፤ ማኅበረሰብ ሲጎዳ አላይም፤ አቁሙ” ብሎ እዛ ከፉ ነገር ፊት የቆመ የሃይማኖት አባት ተመልክተናል? አላየንም፤ ከየት ይምጣ? ይህ ነው ችግሩ ብዬ አስባለሁ፡፡ እኛ ነን የሃይማኖት ትምህርታችንን ልንፈትሽና ልናስተካክል ያለብን ባይ ነኝ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እንግዳችን ስለሆኑ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡**

**ሡስታዝ አቡበከር፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

## ማህደረ ጤና

# ተቋማዊ የጤና እንክብካቤ በ‹‹ተማሪ ኬር››

**አስናቀ ፀጋዬ**

በኢትዮጵያ የሕክምና ተቋማት ቁጥር አሁን ካለው የሕዝብ ቁጥር ጋር ሲነፃፀሩ እዚህ ግባ የሚባሉ አይደሉም:: የሕክምና ባለሙያዎችም አሃዝ ቢሆን ከሕዝቡ ቁጥር ጋር ፈፅሞ የሚጣጣም አይደለም:: ምንም እንኳን በአንድ የጤና ሥርዓት ውስጥ በሽታን መከላከል፣ ጤናን ማስተዋወቅ፣ ሕክምና፣ ሪሃቢሊቴሽንና ፓሊዬቲቭ ኬር /የሥነ ልቦና ሕክምና/ ወሳኝ መሆናቸው ቢነገርም በኢትዮጵያ የጤና ሥርዓቱ በአብዛኛው የሚያተኩረው ምርመራና ሕክምና ላይ ብቻ ነው:: ይህም ሕክምናው የተሟላ እንዳይሆን ያደርገዋል::

በዚህ ረገድ ክፍተት በመኖሩ ነው በሽታ መከላከል፣ ግንዛቤ ማስጨበጥና የጤና ትውውቅ ሥራዎች ላይ ይበልጥ ትኩረት አድርጎ መሥራት ወሳኝ መሆኑ በበርካታ የጤናው ዘርፍ ባለሙያዎች የሚነገረው:: በተለይም የቅድመ ጤና ምርመራ በማድረግ ከከፋ የጤና ጉዳትና የሕክምና ወጪ መዳን እንደሚቻል ነው ብዙ ጊዜ በጤና ባለሙያዎች የሚመከረው::

በዚህ መነሻነትም ነው ባሳለፍነው ሳምንት የ2016 ዓ.ም የጤናው ዘርፍ የክረምት በጎ አድራጎት ትግበራ "በጎነት ለጤናችን" በሚል መሪ ቃል ከፍለው መታከም ለማይችሉ ከ2 ሚሊዮን በላይ ዜጎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ነፃ የጤና ምርመራና ሕክምና አገልግሎት የተጀመረው:: በቅድመ ጤና ምርመራ ላይ በመሥራትና በተለይ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ወደተቋም እንዲወርድ በማድረግ በአይ ጤና ሄልዝ ኬር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ስር ተግባራዊ እየተደረገ ያለው ‹‹ተማሪ ኬር›› ፕሮጀክት ደግሞ የዚሁ ተግባር አንዱ ማሳያ ነው::

የተማሪ ኬር ፕሮጀክት መሥራችና ሥራ አስኪያጅ ዶክተር ኪሩቤል ጫንያለው እንደሚናገሩት፣ እ.ኤ.አ በ2020 በዋናው እህት ኩባንያ አይ ጤና ሄልዝ ኬር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ አማካኝነት ፕሮጀክቱ በሥራ ፈጠራ ውድድር ቀርቦ በጤና ተቋማት ላይ የሚሰጥ የጤና አሠራር ወይም ተቋማትን መሠረት ያደረገ የጤና እንክብካቤ በሚል አሸናፊ ሆኖ ነበር:: የሥራ ፈጠራ ውድድሩ ጭብጥ ሰው ወደ ሆስፒታል ከሚሄድ ሆስፒታል ለምን ወደ ህብረተሰቡ አይሄድም የሚል ነበር:: የፈጠራ ሃሳቡ አመንጪዎችን ጨምሮ በሕክምናው ዘርፍ የተመረቁ ባለሞያዎች ሥራ አጥነት መጨመር ደግሞ እንዲህ ዓይነቱን መፍትሔ ለማምጣት በእጅጉ ገፋፍቷል::

ዩኒሴፍ ባወጣው መረጃ መሠረት የአሁኑ የኢትዮጵያ አማካይ እድሜ 18 ነጥብ 8 እንደሆነ ያሳያል:: ይህም ወጣት ትውልድ በብዛት ያለባት ሀገር መሆኗን ይጠቁማል:: ከ15 ዓመት እድሜ በታች ያሉት ደግሞ 48 ከመቶ ያህሉን የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደሚይዙ ይኸው መረጃ ይጠቁማል:: 30 ሚሊዮን የሚጠጋው ሕዝብ ደግሞ ከአንደኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚገኝ የህብረተሰብ ክፍል እንደሆነ ይገመታል:: ይህም በትምህርት ተቋማት ውስጥ ያለው የህብረተሰብ ክፍል ከፍተኛ እንደሆነ ያሳያል:: በትምህርት ተቋማት ውስጥ ያለውን ከፍተኛ የሰው ቁጥር ከግምት ውስጥ በማስገባትም ነው የተቋማዊ የጤና እንክብካቤ ለማድረግ ተማሪ ኬር ተብሎ ሃሳቡ ሊፈጠር የቻለው::

በኢትዮጵያ በጤና ሥርዓት ውስጥ አስፈላጊ ናቸው የሚባሉት አምስት ምሰሶዎች ማለትም በሽታን መከላከል፣ ጤናን ማስተዋወቅ፣ ሕክምና፣ ሪሃቢሊቴሽንና ፓሊዬቲቭ ኬር በተሟላ መልኩ ተግባራዊ እየተደረጉ አይደሉም:: በብዛት ተግባራዊ ሲደረግ የሚታይው ምርመራውና ሕክምናው ብቻ ነው:: ነገር ግን የፈጠራ ሃሳቡ አመንጪዎች በተቀሩት ምሶሶዎች ላይ ኢላማ አድርገው የመሥራት ሃሳብ ነው ያመጡት:: ከዚህ በመነሳት ፕሮጀክቱ በተማሪዎች ላይ መከላከልን፣ የጤና ትውውቅን የያዘ ስልጠና ከሕክምናውና ሪፈር ሥርዓቱ ጋር አጣምሮ አገልግሎት ይሰጥበታል:: የተቀረው የህብረተሰብ ክፍል ማለትም ከ18 እስከ 60 የእድሜ ክልል ውስጥ ላለው ደግሞ ሌላ ፕሮጀክት እየተዘጋጀ ነው::

ሥራ አስኪያጁ እንደሚያብራሩት፣ ፕሮጀክቱን ለመጀመር በዋናነት ምክንያት የሆነው በኢትዮጵያ የሕክምና ባለሙያዎችና የጤና ተቋማት ቁጥር ተመጣጣኝ አለመሆንና ፈላጊው ታካሚና ተፈላጊው የሕክምና



በአገልግሎቱ ተማሪዎችና ወላጆች ተጠቃሚ ሆነዋል፤

**‹‹የቅድመ ጤና ምርመራ ባሕልን ማሳደግ የሚቻል ከሆነ በተለይ ተላላፊና ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች በየዓመቱ የሚወጣውን ሀገራዊ ወጪ መቀነስ ይቻላል፡፡ በዛ ልክ ግንዛቤውን ማስፋት የሚቻል ከሆነ ደግሞ ለሕክምና ወደ ሆስፒታል የሚሄደውን የህብረተሰብ ቁጥር መቀነስ ይቻላል፡፡ ይህም በመንግሥት ላይ ያለውን ጫና ለመቀነስ ያግዛል፡፡››**

ባለሙያ አለመገናኘት ነው:: ታካሚውንና የሕክምና ባለሙያውን የሚያገናኝ ሁኔታ ባለመኖሩ ከዚህ ክፍተት በመነሳት ተማሪ ኬር የተሰኘው ፕሮጀክት ይፋ የሆነው:: የተለመደው አሠራር ሆስፒታል ገንብቶ ህብረተሰቡን ማከም ነው::

ነገር ግን መንግሥት ሁልጊዜ ሆስፒታል እየገነባ ህብረተሰቡን ያክም ቢባል ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ነው:: ለሆስፒታሎች ግንባታም የሚወስደው ጊዜ ቀላል የሚባል አይደለም:: ስለዚህ ጊዜና ገንዘብ ቆጣቢ መፍትሔ ያስፈልጋል ማለት ነው:: በዚህ ፕሮጀክትም በጤናው ሥርዓት ክፍተቱን በማየት ሀገራዊ መፍትሔ ለማምጣት ነው እየተሰራ ያለው::

ከዛሬ ሶስት ዓመት በፊት የተማሪው ቁጥር እጅግ ከፍተኛ መሆኑን በመገንዘብና ተማሪው ላይ በማተኮር ፕሮጀክቱ እስካሁን ድረስ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል:: የፕሮጀክቱ ዋነኛ ዓላማም በቀጣዩ ትውልድ ላይ ኢንቨስት ለማድረግ፣ ጤናማ ትውልድ ለመፍጠርና የጤናውን ሥርዓት ለማዘመን ነው:: በጤናው ዘርፍ ሕክምና መስጠት አንዱ ሥራ ሆኖ ሳለ መከላከል፣ የጤና ትውውቅ፣ ግንዛቤ ደግሞ ሌላኛው አስፈላጊ ሥራ ነው:: ይህ ነው በተማሪ ኬር ፕሮጀክት አማካኝነት እየተከናወነ ያለው ሥራ::

ለምሳሌ በጊዜው በቂ ግንዛቤ ባለመኖሩ በኢትዮጵያ የኤች አይ ቪ ወረርሽኝ ከፍ ብሎ ነበር:: ነገር ግን በመከላከል ዙሪያ ግንዛቤ እየተሰጠ በመምጣቱና የጤና ማስተዋወቅ ሥራ በመሠራቱ ወረርሽኙ ቀንሶ ታይቷል:: በተመሳሳይ ግንዛቤውና የጤና ማስተዋወቅ ሥራው ሲቀንስ ወረርሽኙ ዳግም አንሰራርቷል:: ይህም መከላከልና ጤና ማስተዋወቅ ትልቅ ቦታ እንዳለው ያሳያል::

ከዚህ በመነሳት የጤና ፌስቲቫሎችን በትምህርት ቤቶች በማዘጋጀት ከተማሪዎች ጀምሮ መላው የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ እንዲገኙ ተደርጎ ከሰባት በላይ የሚሆኑ ስፔሻሊስት ሐኪሞች ይቀርባሉ:: በመከላከል ሥራው ሁሉም ወላጅ ቤተሰቡን፣ ልጆቹን፣ ዘመዶቹን ይዞ መጥቶ የአንድ ወይም የሁለት ሰው ካርድ በሚከፈልበት ዋጋ ከዓይን፣ ጥርስ፣ ሥነ ልቦና፣ ሥነ ምግብ፣ ቆዳ፣ ሕፃናት፣ የውስጥ ደዌ ሐኪሞች ጋር ተገናኝተው ምርመራ፣ ምክርና ሕክምና አገልግሎት አግኝተው ይሄዳሉ:: ይህም የቅድመ ምርመራ ባሕልን ከማሳደግ አኳያ በጎ አስተዋጽኦ ይኖረዋል::

በጤና ማስተዋወቅ ሥራ በፌስቲቫሉ ቀን ወላጆች የሚመርጧቸውና አስፈላጊ ናቸው ብለው ያመኑባቸውን የጤና ጉዳቶችን ያነሳሉ:: የፓናል ውይይቶች ተዘጋጅተው ወላጆች ከአመጋገብ ጋር፣ ከኢንተርኔት አጠቃቀም ጋርና ከሌሎች የጤና ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ጥያቄዎችን አንስተው ወይይት ተደርጎ ለጥያቄያዎቻቸው መልስ እንዲያገኙ ይደረጋል:: በባለሙያዎች ስልጠና የሚያገኙበት ሁኔታም ይመቻቻል::

ሌላው በአካል ብቃት እንቅስቃሴ ላይ የሚሰራው ሥራ ሲሆን በተለይ በአሁኑ ጊዜ ሰዎች በቴክኖሎጂ ውጤቶች ላይ ረጅም ሰዓት ስለሚያሳልፉ የአካል ብቃት እንቅስቃሴያቸው እየቀነሰ በመምጣቱ በተማሪ ኬር ፕሮጀክት ልጆች የሚሳተፉበት የእግር ኳስ፣ የቅርጫት ኳስ ውድድሮች ይደረጋሉ:: በጤና ስፖርትና ዌልነስ ላይ የሚሰሩ ተቋማት ከትምህርት ቤቶችና ከትምህርት ቤቶች ማህበረሰብ ጋር የሚገናኙበት ሁኔታ እንዲፈጠሩ በማድረግ ጤናን የመጠበቅ ሥራዎች ይሰራሉ::

ዋናው ጉዳይ ግንዛቤ መፍጠር በመሆኑ ተማሪዎች ከአመጋገብና ከሌላም የጤና ጉዳዮች ጋር በተገናኘ ለወላጆቻቸው የጤና ኤግዚቢሽን እንዲያዘጋጁ ይደረጋል:: እድሜያቸው ከፍ ያሉ ተማሪዎች ደግሞ የልብ፣ የሳምባ ሞዴሎችን ሰርተው በማቅረብ በነዚህ በሽታዎች ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ይሰራሉ::

ሥራ አስኪያጁ እንደሚሉት፣ በዚህ ፕሮጀክት ከነርስ ጀምሮ እስከ ስፔሺሊስት ሐኪሞች ድረስ ሙሉ የሕክምና ቡድን በመያዝና አስፈላጊ የሆኑ የሕክምና መሳሪያዎችን በማሟላት በየትምህርት ቤቶች በመሄድ የምርመራ ብቻ ሳይሆን የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል:: በትምህርት ቤቶቹ ክሊኒክ ተከፍቶም ነው ምርመራና ሕክምናው የሚደረገው:: ሕክምናው ላብራቶሪ የሚፈልግ ከሆነ እዛው በትምህርት ቤቱ ውስጥ ይዘጋጃል:: ይህም በወላጅና በተማሪዎች በኩል ትልቅ መነቃቃትን ይፈጥራል::

በዚሁ የፕሮጀክት እንቅስቃሴ ባለፈው ዓመት ብቻ ወደ 8 ሺ የሚጠጉ ወላጆችና ተማሪዎችን በምርመራ መለየት ተችሏል:: ከነዚህ ውስጥ የዓይን ችግር የነበረባቸው ልጆች 10 ከመቶ ነበሩ:: ይህም ልጆቹ አስቀድመው ባይታዩና ባይመረመሩ ኖሮ ችግሩ የከፋ ሊሆንባቸው ይችል ነበር:: ወደ 83 ከመቶ ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ የጥርስ ችግር ነበረባቸው:: 10 ከመቶ ያህሉ ከክብደታቸው በታች፣ 17 ከመቶ በላይ የሚሆኑት ከክብደታቸው በላይ ሆነው የአመጋገብ ችግር ነበረባቸው:: በልየታው ወቅት ስኳርና የደም ግፊት የተገኘባቸው ወላጆችም ነበሩ:: ቀዶ ሕክምና የሚጠይቅ የዓይን ችግር የተገኘባቸውም አሉ::

ስለዚህ በዚህ የተማሪ ኬር ፕሮጀክት አማካኝነት 800 ብር ባለሞላ ዋጋ ተማሪ፣ የተማሪው ቤተሰብና ዘመድ አዝማድ ሙሉ ምርመራና ሕክምና ማግኘት ይችላል:: ስለጤናቸው መጠየቅ ያለባቸውን ጠይቀውና አውቀው ብሎም ተመካክረው የሚወጡበት ቤተሰባዊ ጤና አጠባበቅ ሥርዓት ነው:: ይህ ደግሞ የቅድመ ጤና ምርመራ ባሕልን ያዳብራል:: የጤና አገልግሎት ተደራሽን ሁሉም እንደአቅሙ የሚያገኘው ማድረግ ይቻላል::

ፕሮጀክቱ በአብዛኛው ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኘው በአብዛኛው በመንግሥት ትምህርት ቤቶች ላይ ቢሆንም በግል ትምህርት ቤቶች ላይም እየተሰራበት ሲሆን ሥራውም ከአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ እውቅና አግኝቷል:: የአገልግሎት ክፍያ ዋጋውን ዝቅ በማድረግ የጤና አገልግሎት ተደራሽነቱ ላይ እየተሰራ የሚገኘው:: በመንግሥት ትምህርት ቤቶች በምገባ ሥርዓት ውስጥ ላሉ ተማሪዎች ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በመሆኑ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ ሥራዎች እየተከናወኑ ነው::

ለግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ደግሞ ከቤተሰብ ጋር በተያያዘ አገልግሎቱን የሚያገኙ ስለሆነ ፌስቲቫል በማዘጋጀት ነው እንዲከፍሉ የሚደረገው:: ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚመጡ ተማሪዎች ከ700 እስከ 800 ባለው መካከል እንዲከፍሉ ይደረጋል:: በዚህ የገንዘብ መጠን ወላጆችም ሆነ ተማሪዎች የጤና ምርመራና ሕክምና አገልግሎቱን ካገኙ በኋላ አብዛኛዎቹ ደስተኛ ናቸው:: ይህንኑ አገልግሎት የሚሰጡ በፕሮጀክቱ ያሉ አጠቃላይ ሐኪሞች ቁጥር ደግሞ አስራ ሰባት ደርሷል::

እንዲህ ዓይነቱ የጤና አገልግሎት ተማሪዎች ህመም ሲሰማቸው ብቻ ሳይሆን ሳይታመሙም ጤናቸውን መንከባከብ የሚችሉበትን ባሕል እንዲያዳብሩ የሚያስችል ነው:: በየዓመቱ ጤናቸውን እንዲከታተሉ፣ በዓመት ሁለት ጊዜ የደምና የኩላሊት ምርመራ እንዲያደርጉ ትምህርት የሚሰጥ ነው:: የቅድመ ጤና ምርመራ ባሕልን ማሳደግ የሚቻል ከሆነ በተለይ ተላላፊና ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች በየዓመቱ የሚወጣውን ሀገራዊ ወጪ መቀነስ ይቻላል:: በዛ ልክ ግንዛቤውን ማስፋት የሚቻል ከሆነ ደግሞ ለሕክምና ወደ ሆስፒታል የሚሄደውን የህብረተሰብ ቁጥር መቀነስ ይቻላል:: ይህም በመንግሥት ላይ ያለውን ጫና ለመቀነስ ያግዛል::

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# በእንጨት ሥራ የተካነው የጅማ ነዋሪው ወጣት

ፍሬሕይወት አወቀ

ጅማ ከምትታወቅበት የቡና ምርቷ በተጨማሪ በእንጨት ሥራዎቿም ዕውቅናን አትርፋለች፡፡ ጅማን ስናስብ ከአንድ ግንድ ተፈልፍሎ የሚሰራው ባለ ሶስት እግሩ የአባ ጅፋር በርጩማ ቀድሞ ይታወሰናል፡፡ አለፍ ሲልም የስኒ ረከቦቶቹ /በዓይነትና በመጠን/፣ አልጋው፣ የቡና ጠረጴዛው፣ የፎቶ ማስቀመጫና ሌሎች ከእንጨት የሚሰሩ ቅርጻ ቅርጾችን ማንሳት የግድ ነው፡፡ የእንጨት ሥራ የዕድ ጥበብ ውጤት እንደመሆኑ ጅማ ጎራ ያለ እንግዳ በሙሉ ጥበበኛ እጆች የተጠበቡባቸውን የእንጨት ውጤቶች ተመልክቶ መማረኩና የራሱ ማድረጉ የማይቀር ጉዳይ ነው፡፡

የጅማ እንጨት ሥራ መነሻው የአባጅፋር ወንበር ሲሆን፤ ወንበራቸው በተፈጥሮ ከአንድ ግንድ ተፈልፍሎ የወጣ ባለሶስት እግር በርጩማ ነው፡፡ ይህ በርጩማ ከአንድ የዋንዛ ግንድ ተፈልፍሎ የተሠራ ነው፤ መቀመጫው ምንም ዓይነት ዘመናዊ መሳሪያ ወይም ማሽን ያልነካውና በመጥረቢያና በእጅ ብቻ የተሰራ ዘመን ተሻጋሪ ስለመሆኑም ይነገራል፡፡ በዚሁ መነሻነት የተጀመረው የእንጨት ሥራም አሁን ላይ ጅማ ከምትታወቅባቸው ዋና ዋና ጉዳዮቿ መካከል አንዱ መሆን ችሏል፡፡ የእንጨት ሥራዎቿ ዛሬም ድረስ እየተሻሻሉ ቀጥለዋል፡፡ በተለይም ባለሶስት እግር ወንበሩ ወይም በርጩማ በዘመን ተሻጋሪነቱ ይታወቃል፡፡

የእንጨት ሥራ በስፋት በተለመደባት ጅማ አብዛኛው ወጣት እጁን የሚያፍታታውና ሥራ የሚጀምረው በእንጨት ነው ቢባል ከእውነት የራቀ አይደለም፡፡ በአካባቢው እንጨት ተፈልፍሎ ተገቢውን ቅርጽ ይዞ ለተለያየ አገልግሎት ሲውል መመልከት የዕለት ተዕለት ተግባሩ ለሆነው የጅማ ወጣት የእንጨት ሥራ ሙያ በእጁ ላይ ነው ማለት ይቻላል፡፡ አብዛኛው ወጣት የእንጨት ሥራን በቀላሉ በመልመድ የመጀመሪያው የሥራ አማራጩ የሚያደርገውም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡

የዕለቱ የስኬት እንግዳችንም እንደ አብዛኛዎቹ የጅማ ልጆች ለእንጨት ሥራ እንግዳ አይደለም፡፡ ጅማ ከተማ ተወልዶ እንደማደጉ በየአካባቢው የእንጨት ሥራን እየተመለከተ አድጓል፡፡ ከመመልከት ባለፈም ውስጣዊ ፍላጎትና ለጥበብ የተሰጠ ማንነት ያለው በመሆኑ እንጨቱን ይጠበብበታል፡፡

‹‹የእንጨት ሥራ ዕደጥበብ ነው›› የሚለው እንግዳችን እንጨት ፈልፍሎ የተለያዩ ቅርጻ ቅርጾችን ይሠራል፡፡ ትናንሽ ከሚመስሉ ቅርጻ ቅርጾች በተጨማሪም ትላልቅ የሚባሉ እንደ ቁም ሳጥን፣ አልጋ፣ ወንበር ጠረጴዛ፣ በርና መስኮቶች፣ በርጩማና ሌሎችንም ይሰራል፡፡ አጠቃላይ ከእንጨት የሚሰሩ ማናቸውንም ቁሶች በመሥራት የሚታወቀው ጥበበኛው እንግዳችን ወጣት ሙሉቀን ወንድሙ ይባላል፡፡

ጅማ ላይ ተወልዶ ያደገው ወጣት ሙሉቀን፤ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱንም በዚያው ተምሯል፡፡ የከፍተኛ ትምህርቱንም እንዲሁ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ተከታትሎ በማኔጅመንትና በአርት (በሙዚቃ ትምህርት ክፍል) የመጀመሪያ ዲግሪውን አግኝቷል፡፡

ትምህርት የተሻለ ዕውቀት የሚሰጥ ስለመሆኑ የሚያምነው ወጣት ሙሉቀን፤ ለሚሰራው የእንጨት ሥራ አቅምና ጉልበት እንደሆነው ይናገራል፡፡ ‹‹በተለይ አርት ሰዎች እራሳቸውን ፈልገው የሚያገኙበት መንገድ ነው›› ይላል፡፡ ከከፍተኛ ትምህርት በኋላ እራሱን ጥበብ ውስጥ እንዳገኘው የሚናገረው ወጣት ሙሉቀን ከትምህርት በኋላ በቀጥታ ወደ እንጨት ሥራ እንደገባና የፈጠራ ችሎታውን በመጠቀም የተለያዩ ቅርጻ ቅርጾችን መሥራት እንደጀመረ አጫውቶናል፡፡

እሱ እንደሚለን፤ ከከፍተኛ ትምህርት በኋላ ተቀጥሮ የመሥራት ፍላጎት አልነበረውም፡፡ ከዛ ይልቅ በውስጡ የሚመላለሰውን የቅርፃ ቅርፅ ጥበብ ለማውጣት ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡ በጥረቱም ዕውቀቱንና ውስጣዊ ፍላጎቱን ብቻ መነሻ በማድረግ በወላጆቹ መኖሪያ ግቢ ውስጥ እንጨት ሰብስቦ ፈጠራ የታከለበት ሥራ መሥራት ጀምሯል፡፡ ታዲያ ትናንሽ ከሚባሉ ቅርጻ ቅርጾች ጀምሮ ከእንጨት የሚሰሩ ትላልቅ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን ለመሥራት ጊዜ አልወሰደበትም፡፡ ምክንያቱም ይላል፤ ‹‹ምክንያቱም ማንም ሰው አሻፈረኝ ካላለ በስተቀር የጅማ



ወጣት ሙሉቀን ወንድሙ

ልጅ ሆኖ ለእንጨት ሥራ ባዳ የሚሆን ሰው የለም፡፡ ፍላጎት ያለው ሁሉ የእንጨት ባለሙያ መሆን ይችላል፡፡ ለዚህ ደግሞ ጅማ ውስጥ በብዛት ፋብሪካ አለመኖሩም ሌላው ምክንያት ነው›› ይላል፡፡

ጅማ ውስጥ የሚፈለገውን ያህል ፋብሪካዎች ባለመኖራቸው አብዛኛው ወጣት እንጨት ሥራን እንደ አንድ አማራጭ ወስዶ ወደ ሥራው ይገባል፡፡ የሚለው ወጣት ሙሉቀን፤ የእርሱም አጋጣሚ ከዚህ የተለየ እንዳልነበር ይናገራል፡፡ በዚህም የተለያዩ ከእንጨት የተሰሩ የጥበብ ሥራዎች ጅማ ውስጥ ይታያሉ፡፡ ምንም ዓይነት ማሽን ሳይጠቀሙ እንጨት ፈልፍለው በእጃቸው ብቻ ከሚሰሩት የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችና ቅርጻ ቅርጾች መካከል ቀጭኔን ጨምሮ የተለያዩ የእንስሳት ቅርጽ፣ የቡና ጠረጴዛ፣ የስኒ ረከቦት፣ ፎቶ ፍሬም፣ ዱካ፣ መቀመጫዎችና ሌሎችም ይጠቀሳሉ፡፡

በከተማዋ ከሚታዩት የእንጨት ሥራዎች መካከል ሁሉንም ዓይነት የእንጨት ሥራዎች በሚባል ደረጃ የሚሰራው ወጣት ሙሉቀን፤ እንጨት የተባለ ሁሉ እጁ ሲገባ ሕይወት ይዘራበታል፡፡ ሳቢና የሚያማምሩ ቅርጻ ቅርጾችን እንዲሁም የተለያዩ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን ያመርትበታል፡፡ ባጠቃላይ እንጨቱን ይጠበብበታል ብንል ማጋነን አይሆንም፡፡ በወላጆቹ መኖሪያ ግቢ ውስጥ ብቻውን አንድ ብሎ የጀመረው የእንጨት ሥራ ዛሬ በከተማዋ አሉ ከሚባሉ እንጨት ሠራተኞች ተርታ አሰልፎታል፡፡

ገና በልጅነቱ የእንጨት ሥራዎች ሲሰሩ እየተመለከተ ያደገው ወጣት ሙሉቀን፤ ሙያውን ለመማር ብዙ አልተቸገረም፡፡ በቀላሉ ሰዎች ጋር ተጠግቶ በመላላክ እንዲሁም ረዳት በመሆን ነው ሙያውን የለመደው፡፡ ይሁንና ለሙያው ጠለቅ ያለ ፍቅርና ከፍተኛ ተነሳሽነት ያዳበረውም በዚያ ምክንያት ነው፡፡ በዚህ መነሻ በቀጥታ ወደ ሥራው በመግባትም የእንጨት ሥራዎቹን እያመረተ ለገበያ ያቀርባል፡፡

ጅማ ላይ ያለው የእንጨት ሥራ ትኩረት ቢሰጠው አሁን ላይ ካለው አበርክቶ የበለጠ ለወጣቱ ሥራ ዕድል ፈጠራ ብዙ ሊያበረክት የሚችል ነው፡፡ የሚለው ወጣት ሙሉቀን፤ በርካታ ወጣቶች ሕይወታቸውን የለወጡበትና የተሻሻሉበት ቢሆንም የበለጠ እንዲታወቅ መንግሥት ትኩረት ቢሰጠው መልካም መሆኑን ሲያስረዳ፤ የገበያ ትስስር ተፈጥሮለት ሥራው እንዲሰፋ መንግሥትን ጨምሮ የሁሉንም ትብብር የሚፈልግ ነው፡፡ በርካታ ወጣቶችም ሙያውን በቀላሉ መማር የሚችሉበትና መጠነኛ በሆነ መነሻ ካፒታል መሥራት የሚችሉት ሥራ ነው፡፡

እንጨት ሥራ ጅማ ውስጥ በቀላሉ የሚጀመር ሥራ እንደመሆኑ ከፍተኛ ጥረት ሲታከልበት ውጤታማ የሚያደርግ ነው፡፡ የወጣት ሙሉቀንም ተሞክሮ ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ቀን ከሌሊት በመሥራት ውጤታማ መሆን ችሏል፡፡ ይህም ሲባል አሁን ላይ ከሚያመርታቸው ምርቶች መካከል የስኒ ረከቦት በተለያየ መጠንና ቅርጽ በስፋት አምርቶ አዲስ አበባን ጨምሮ ለክልል ከተሞች ይልካል፡፡ የማምረት አቅሙንና የገበያ ፍላጎቱን በማጣጣም ትዕዛዝ ሲበዛ ለሌሊት ጭምር በመሥራት ወደ ስኬት እየተንደረደረ ያለ ወጣት ነው፡፡

ለሥራ ያለውን ውስጣዊ ፍላጎትና ተነሳሽነት መሠረት በማድረግ አንድ ብቻውን ሆኖ በወላጆቹ መኖሪያ ግቢ ውስጥ የጀመረው የእንጨት ሥራ ዛሬ ላይ 24 ለሚደርሱ ወጣቶች በቋሚነት የሥራ ዕድል ፈጥሯል፡፡ ከ24ቱ በተጨማሪም የሥራ ትዕዛዝ ሲጨምር ጊዜያዊ የሥራ ዕድል በመፍጠር ያሰራል፡፡ የመሥሪያ ቦታውን በተመለከተም ሁለት የማምረቻ ቦታ ያለው ሲሆን፤ አንደኛውን ቦታ በጥቃቅንና አነስተኛ ተደራጅቶ ከከተማ አስተዳደሩ ያገኘው ሲሆን፤ ሁለተኛውን ከግለሰቦች ተከራይቶ ይሰራል፡፡ አንደኛው የማምረቻ ቦታ ትላልቅ የሚባሉ እንደ አልጋ፣ ቁምሳጥን፣ በሮች፣ መስኮቶችና የምግብ ጠረጴዛዎች የሚመረቱበት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ቀለል ያሉ እንደ ስኒ ረከቦት የቡና ጠረጴዛ፣ የፎቶ ማስቀመጫ የተለያዩ ቅርጻ ቅርጾች ሆነው ሱቅ ላይ መሸጥ የሚችሉትን ያመርታል፡፡

**ለሥራ ያለውን ውስጣዊ ፍላጎትና ተነሳሽነት መሠረት በማድረግ አንድ ብቻውን ሆኖ በወላጆቹ መኖሪያ ግቢ ውስጥ የጀመረው የእንጨት ሥራ ዛሬ ላይ 24 ለሚደርሱ ወጣቶች በቋሚነት የሥራ ዕድል ፈጥሯል**

የሚያመርታቸው ምርቶች ባፈራቸው ደንበኞቹ አማካኝነት በክልል ከተሞችና በአዲስ አበባ ከተማ ተደራሽ እንደሚሆኑ ያነሳው ወጣት ሙሉቀን፤ በተለይም አልጋ የጅማ ሕዝብ በስፋት እንደሚገዛና ወደ አዲስ አበባም እንደሚልክ ይናገራል፡፡ ከተማ ውስጥ ከሚገኘው መሸጫ ሱቅና ከክልል ደንበኞች በተጨማሪ በማህበራዊ ሚዲያ ማለትም በቲክቶክ፣ በፌስቡክና ኤም ኤም ፈርኒቸር በሚል በቴሌግራም ምርቶቹን የማስተዋወቅና የመሸጥ ሥራ ይሰራል፡፡

ለምርቶቹ አስፈላጊ የሆነው ጥሬ ዕቃ በዋናነት እንጨት ነው፡፡ ይህ እንጨትም ጅማ ውስጥ በስፋት የሚገኝ ሲሆን፤ ዓይነቱም የዋንዛ እንጨት ነው፡፡ የእንጨት ሥራዎቹ በስፋት የዋንዛ እንጨት በመጠቀም የሚመረቱ ሲሆን፤ ከእንጨት በተጨማሪ እንደ አስፈላጊነቱ ኤምዲኤፍ፣ ላሚኔት፣ ኮምቤፍአይጂትና ሌሎችም ማንኛውም እንጨት ቤት የሚገኙ ጥሬ እቃዎችን ይጠቀማል፡፡ ለዘርፉ የጥሬ እቃ ችግር የለም፡፡ ነገር ግን የገበያ ትስስር ባለመኖሩ አምራቹ ማምረት በሚችለው አቅም ሳይሆን ገበያው በሚጠይቀው ልክ ብቻ እያመረተ መሆኑን በመግለጽ የገበያ ትስስር አለመኖሩ አንዱ ችግር ነው ይላል፡፡

ላለፉት 15 ዓመታት በእንጨት ሥራ ውስጥ ያሳለፈው ወጣት ሙሉቀን፤ የእንጨት ሥራ አንዱ የዕደ ጥበብ ውጤት እንደሆነ ያስረዳል። ጅማ ውስጥ ከእንጨት የሚሰሩ ውብ ሥራዎች እንዳሉና እነዚህን ውብ ሥራዎች ግን አውጥቶ የመጠቀምና የማስተዋወቅ ሥራ አልተሰራም፡፡ ስለዚህ መንግሥት ለዘርፉ ትኩረት ሰጥቶ መታየት ቢችል አሁን እየፈጠረ ካለው የሥራ ዕድል በበለጠ በርካታ ቁጥር ላላቸው ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር እንደሚችል አመላክቷል፡፡ ከሥራ ዕድል በተጨማሪም ምርቶቹ ውብ፣ ጠንካራ ዘመን ተሻጋሪ እንደመሆናቸው ከውጭ የሚገባውን ፈርኒቸር በመተካት የውጭ ምንዛሪን ማዳን እንደሚቻል አስረድቷል፡፡

ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድ ወጣት ሙሉቀን በአካባቢው ለሚገኙ ወጣቶች ሙያዊ ስልጠና በመስጠት ወደ ሥራው እንዲገቡ ያደርጋል፡፡ በተለይም በመንግሥት በኩል ከተለያዩ ቀበሌዎች ተደራጅተው ለሚመጡ ወጣቶች የስድስት ወር ስልጠና በመስጠት የእንጨት ሥራ ሙያን ቀስመው ይወጣሉ፡፡ በአንድ ጊዜ አምስትና አስር ወጣቶችን በማሰልጠኑም የምስክር ወረቀት አግኝቷል፡፡ በአሁን ወቅትም አምስት ወጣት ሴቶችን ከወረዳው ተቀብሎ እያሰለጠነ ይገኛል፡፡

በቀጣይም የእንጨት ሥራውን የማስፋትና የማዘመን ዕቅድ ያለው መሆኑን ያነሳው ወጣት ሙሉቀን፤ በተለይም ደረጃውን በጠበቀ መንገድ በማምረት እንዲሁም ሥራዎቹን በስፋት ማሳየት በሚችል ትልቅ የእንጨት ሥራዎች ማሳያ የመክፈት ዕቅድ አለው፡፡ ለዚህም ዘመናዊ ማሽኖች ሥራ የሚያቀሉ በመሆናቸው ዘመናዊ ማሽኖችን ለመጠቀም አስፈላጊውን የቅድመ ዝግጅት ሥራ እየሰራ ስለመሆኑም አጫውቶናል፡፡

ማንኛውንም ሥራ ሰዎች ፈልገውና ከውስጥ በመነጨ ተነሳሽነት መሥራት ከቻሉ ውጤታማ መሆን እንደሚቻል የሚመክረው ወጣት ሙሉቀን፤ በተለይም የጅማ ወጣቶች በቀላሉ የሚለመደውን እና በሁሉም ደጅ የሚገኘውን የእንጨት ሥራ ሙያ በመቅሰም መሥራት እንደሚችሉ ይናገራል፡፡ ለዚህም ከተማ አስተዳደሩ ለዘርፉ ትኩረት መስጠት እንዳለበት ያምናል፡፡ በአሁን ወቅትም የእንጨት ሥራው በርካታ ወጣቶችን የያዘ በመሆኑ የበለጠ ለመሥራት የመንግሥት ትኩረት ወሳኝ ነው ብሏል፡፡

# ተናጋሪው ዶሴ

# አስገድዶ ከመድፈርም በላይ



**ምህረት ሞገስ**

አላዩ ዓለምነህ ከሰው ተነጥሎ የሚኖር አኩራፊ ነው:: ትምህርት ካለመማሩም በላይ በዕድሜው የሰው ልጅ የሚደርስባቸው ደረጃዎች ላይ መድረስ አልቻለም:: ይህችን ምድር ከተቀላቀለ ግማሽ ምዕተ ዓመታት ሊሞሉት ሶስት ዓመታት ብቻ የቀሩት ቢሆንም፤ ትዳር አልመሠረተም:: የተሻለ ሥራ ሠርቶ ትልቅ ገቢ ለማግኘት አልታደለም:: የሚሠራው መርካቶ አካባቢ ቢሆንም፤ ከቀን ሰራተኝነት የተሻለ ሥራ ሠርቶ አያውቅም:: አንዳንድ ጊዜ ይሸከማል:: ገቢው ከእጅ ወደ አፍ ነው::

አንድ ቀን ጥቂት መቶ ብሮችን ካገኘ እስኪጠግብ ይበላል:: በቀረው ብር እስኪ ሰክር ይጠጣል:: የራሱ ቤት የለውም:: የሚኖረው ዘመድ ቤት ተጠግቶ ነው:: ሰዎችን ሲመለከት በመላ ሰውነቱ የሚሰራጨው ከፍቅር ይልቅ ጥላቻ ብቻ ነው:: ይህ የሆነበትን ምክንያት ለማጣራት የአላዩ አጠቃላይ ሕይወቱን በተመለከተ ጥናት ማካሔድ ያስፈልጋል:: ከጥላቻው ብዛትም ሰው በምንም መልኩ ይፈፅመዋል ብሎ ለማሰብ የሚዘገንን ከባድ ወንጀል ፈፅሟል::

## መከላከል ያቃታት ሕፃን

አላዩ በጥር 28 ቀን 2015 ዓ.ም ከሌላው ጊዜ በተለየ መልኩ ገንዘብ አግኝቷል:: ጥግብ ብሎ ከበላ በኋላ እስኪሰክር ጠጥቶ እንደለመደው ያስጠጉት ዘመዶቹ ቤት ከምሽቱ አራት ሰዓት አካባቢ ገባ:: የጠጣውን ለማውጣት ሽንት ቤት እየተመላለሰ አደረ:: ሲነጋለት ማለትም ጥር 29 ቀን 2015 ዓ.ም አንድ ሰዓት ተኩል አካባቢ እርሱም በሚኖርበት ግቢ ውስጥ የሚኖረው የአክስቱ ልጅ ባል ሁለቱን ልጆቹን ይዞ ወደ ትምህርት ቤት ሲሄድ አየ::

ከሽንት ቤት ሲመለስ ወደ አክስቱ ልጅ ቤት ገባ:: ሳሎኑን አልፎ ወደ መኝታ ቤት ሲያመራ የ14 ዓመት ዕድሜ ያላት እና የአክስቱ ልጅ ቤት ተጠግታ የምትኖረዋን ቃልኪዳን ዘነበ ወደ ትምህርት ቤት ለመሔድ ደብተሯን እያስተካከለች አገኛት::

ቃልኪዳን አላዩን እንዳየች ደነገጠች፤ አይኑ እንደደፈረሰ ነው:: እያፈጠጠ ሲጠጋት ደብተሯን ጥላ፤ «ልትደፍረኝ ነው? » ብላ ጮኸች:: አላዩም፤ «አዎ» ብሎ በሃይል በጥፊ ሲላት አልጋው ላይ ወደቀች:: ዘሎ ወጥቶባት አንገቷን አነቃት:: እንዳትጮህ በቅርብ ያለውን የልጆች ኮፍያ ሳይቀር አፏ ውስጥ ጠቀጠቀ:: በሕፃን አቅሟ ብትታገለውም የ47 ዓመት ዕድሜ ያለውን እና የቀን ሥራ የሚሰራውን ጎልማሳ ከላይዋ ላይ ማንሳት አልቻለችም::

እንደፈራችው አንገቷን እንዳነቀ ቀሚሷን ወደ ላይ ሰብስቦ የለበሰችውን ቱታ አወለቀ:: በድጋሚ ታገለችው ነገር ግን ልትቋቋመው አልቻለችም:: የራሱን ሱሪ አውልቆ በኃይል አካላቱን ሰውነቷ ውስጥ ከተተው:: በጭኖቿ መሃል ደም መፍሰስ ጀመረ:: ቃልኪዳን ገና ሕፃን ያልጠነከረች በመሆኗ መቋቋም አቃታት:: ብዙም ሳትቆይ በዛችው ቅፅበት ህይወቷ አለፈ:: ሳትኖር የሕይወትን ትርጉም በቅጡ ሳትረዳ በደረሰባት የአስገድዶ መደፈር ጥቃት እስከ ወዲያኛው አሸለበች:: አላዩ የሚፈልገውን ፈፅሞ ሱሪውን አጥልቆ ቃልኪዳንን እዛው እግሯ እንደተከፈተ አፏ ጨርቅ እንደተጠቀጠቀበት ትቷት ሮጦ ወጣ::

ቃልኪዳን ምንም እንኳ ጠዋት አንድ ሰዓት ተኩል ህይወቷ ቢያልፍም፤ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት እስከሚሆን አስክሬኗን ያየ አልነበረም:: አሳዳጊዋ ትዕግስት ዘጠኝ ሰዓት ከሥራ ስትገባ ቦርሳዋን ለማስቀመጥ ወደ ጓዳዋ ስትዘልቅ አልጋ ላይ ያየችውን ማመን አልቻለችም:: የቃልኪዳንን አስክሬን ተጠግታ ለማየት ፈራች:: እደጅ ወጥታ መጮህ ጀመረች:: ሰዎች ተሰበሰቡ:: የምስኪኗ የቃልኪዳንን ገበና ሁሉም አየው:: ጎረቤት ተጯጯኸ:: ፖሊስ ተጠራ:: ያልታደለችዋ ሕፃን ቃልኪዳን አስክሬኗ የተሰበሰበው ቀኑን ውሎ ሙሉ ለሙሉ ከደረቀ በኋላ ነበር:: ጎረቤት አልገነዛትም፤ ብዙዎች ግን እምባቸውን እያፈሰሱ ነውሩን አዩ:: ፖሊስ አስክሬኗን አንስቶ ለምርመራ ወደ ሆስፒታል ላከ::

## ምስክርነት

የቃልኪዳን አሳዳጊ ሥራዋ የሚከናወነው ከለሊት ጀምሮ በመሆኑ ማልዳ ጠዋት 12 ሰዓት ከቤት ወጥታለች:: ልጆቿን ትምህርት ቤት የሚያደርሰው ባለቤቷ ነው:: ቃልኪዳን ደግሞ አድጋለችና ወደ ትምህርት ቤት የምትሄደው ብቻዋን ነው:: መስካሪ ትዕግስት የቃልኪዳን አሳዳጊ በጥር 29 ቀን 2015 ዓ.ም ከቤት የወጣችው ልክ 12 ሰዓት ነበር:: እንደልማዷ ከቤት ወጥታ ሮጠች:: ከቤቷ ስትወጣ የምታሳድጋትን የ14 ዓመት ሕፃን ቃልኪዳን ብቻ ሳይሆን ሁለት ልጆቿ እና ባለቤቷ ቤት ነበሩ::

ዘጠኝ ሰዓት ከሥራ ስትመለስ ያጋጠማት ዱብ ዕዳ ለዘላለም አብሯት መቃብር ድረስ የሚወርድ ፀፀት ጣለባት:: ከሥራ መጥታ ወደ መኝታ ቤት ስትገባ፤ ትምህርት ቤት ትሆናለች ብላ ያሰበቻት ልጅ ቃልኪዳን አፏ ውስጥ ጨርቅ ተጠቅጥቆ አልጋ ላይ ተንጋላለች:: እግሯ ተከፍቷል:: ቀሚሷ ወደ ላይ ተሰብስቧል፤ ሱሪዋ ወልቆ መሬት ወድቋል:: በጭኖቿ መሃል የደረቀ ደም ይታያል:: ጠጋ ብላ ስታረጋግጥ የቃልኪዳን ህይወት አልፏል::

የቃልኪዳንን ሞት ያረጋገጠችው አሳዳጊ ድረሱልኝ ብላ መጮህ ጀመረች:: የአካባቢው ሰዎች ተሰበሰቡ፤ ፖሊስ ተጠራ በመጨረሻም የፖሊስ የምርመራ ቡድን አስከሬኑን በጥንቃቄ አነሳ ስትል መስክራለች:: በመጨረሻም ቃሏን የሰጠችው ቃልኪዳን ከተቀበረች በኋላ ሲሆን፤ ተከሳሽ የአክስቷ ልጅ አላዩ እንዲህ ዓይነት ከባድ ወንጀል ይፈፅማል ብላ እንዳልጠረጠረች፤ ነገር ግን አላዩ ቃልኪዳን ከሞተችበት ቀን ጀምሮ መጥፋቱን እና የጠፋውም ምናልባት ድርጊቱን የፈፀመው እርሱ ይሆናል ብላ ተናግራለች::

ሕፃን ቃልኪዳንን ከመድፈር አልፎ ሕይወቷን ያጠፋው አላዩ በፖሊስ ብርቱ ክትትል በቁጥጥር ስር ዋለ:: እውነት ተደብቆ አይቀርም እና ከፉ ድርጊቱ አሳልፎ ሰጠው:: በመርማሪ ፖሊስ ፊት ቀርቦ ድርጊቱን መፈፀሙን አመነ:: ራሱ በሰጠው የእምነት ክህደት ቃል ላይ እንደሰፈረው፤ የቀን ሠራተኛ የሆነው አላዩ ዓለምነህ ዕድሜው 47 ነው:: ትምህርቱን ያቋረጠው ገና የስድስተኛ ክፍል ተማሪ እያለ ነበር:: አዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር 286 ከዘመዶቹ ጋር ተጠግቶ ይኖር እንደነበር ጠቁሞ፤ ድርጊቱን የፈፀመው በጥር 29 ቀን 2015 ዓ.ም በግምት ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ከሰላሳ አካባቢ፤ በዛው በሚኖርበት በጉለሌ ክፍለ ከተማ ሽሮ ሜዳ አዲስ ተስፋ ትምህርት ቤት ወለጋ ሠፈር እየተባለ በሚጠራው አካባቢ መሆኑን አምኗል::

## የወንጀሉ ዝርዝር

ወንጀሉ የተፈፀመው በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ሕግ አንቀፅ 620 (2)(ሀ)እና (3) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ መሆኑን የጠቀሰው የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ፤ የወንጀሉን ዝርዝር ሲያስረዳ ተከሳሽ የኃይል ድርጊት በመጠቀም ከጋብቻ ውጪ የ14 ዓመት ሕፃን የሆነችውን ሟች ቃልኪዳን ዘነበ የምትኖርበት ቤት ውስጥ በመግባት በጥፊ ፊቷ ላይ በመምታት አልጋ ላይ በኃይል በመወርወር ጥሏታል:: እዛው አልጋ ላይ እንዳለች አንገቷን በሁለት እጆቹ በማነቅ ሟች ስትጮህ አንገቷን ከመጫን ባለፈ አፏ ውስጥ ጨርቅ በመጠቅጠቅ እና በማፈን በመታገል የኃይል ድርጊት በመጠቀም እራሷን እንዳትከላከል አድርጓል:: የለበሰችውን ቱታ በማውለቅ የራሱንም ሱሪ በማውለቅ ግብረስጋ ግንኙነት ፈፅሞባታል:: በፍፁም ሰው በሰው ላይ ይፈፅመዋል ተብሎ የማይገመት አስነዋሪ ድርጊት የፈፀመባት ሲሆን፤ ግፈኛነቱን እና የጨካኝነቱን በአዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር 286 በዛው ቤት ውስጥ ያሳየ መሆኑን በወንጀሉ ዝርዝር ላይ ተመላክቷል::

የአስክሬን የምርመራ ውጤትም ከኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ የፎረንሲክ ምርመራ ላብራቶሪ የቀረበ ሲሆን፤ የህክምና ማስረጃው እንደሚያሳየው ዜሮ ነጥብ አንድ ሳንቲ ሜትር ርዝመት እና በስድስት ሳንቲ ሜትር ስፋት ያለው የቆዳ መጋጥ ጉዳት ከግራ የታችኛው መንጋጋዋ መዓዘን ዝቅ ብሎ የሚገኝ የአንገት ክፍሏ ላይ ታይቷል:: ሁለተኛ ቁመቱ ዜሮ ነጥብ አምስት እና ስፋቱ ሶስት ሳንቲ ሜትር የሆነ የቆዳ መጋጥ ጉዳት በግራ መንጋጋ ማእዘን ላይ እንደደረሰባት ማረጋገጥ ተችሏል::

ሌላው የቀኝ የአይኗ ቅንድብ የታችኛው ቆብ የጠቆረ ሲሆን፤ በአይኗ እና አፍንጫዋ መካከል መበለዝ የታየ ሲሆን፤ በዛ አካባቢም ጉዳት እንደደረሰባት ለማወቅ ተችሏል:: የታችኛው ከንፈሯም በቀኝ በኩል መበለዙ እና የቀኝ ጡቷ ላይም የቆዳ መጋጥ መኖሩ ታውቋል::

ከተጠርጣሪው አላዩ የጉንጭ ህዋስ እና የምራቅ ናሙና የተወሰደ ሲሆን፤ ከሟች ቃልኪዳን ከመራቢያ አካል ተሰበሰበ ከተባለው ናሙና የተገኘው ዘረመል ሲመሳከር ሙሉ ለሙሉ ተመሳሳይ መሆኑ ተረጋግጧል:: በአጠቃላይ ይህን የወንጀል ዝርዝር አካቶ የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን የሰው መግደል ወንጀል ምርመራ ዲቪዥን ሞትን ያስከተለው የአስገድዶ መድፈር ወንጀል የክሱን ፍሬ ነገር በአጭሩ አብራርቶ ለአቃቤ ሕግ አቅርቧል::

አቃቤ ሕግም ተጠርጣሪው በጥር 29 ቀን 2015 ዓ.ም በግምት ከጠዋቱ አንድ ሰዓት አካባቢ በዚሁ በአዲስ አበባ ከተማ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ክልል ልዩ ቦታው ሽሮ ሜዳ አዲስ ተስፋ ትምህርት ቤት አጠገብ መኖሪያ ቤት የምትኖረውን የ14 ዓመት ሕፃን ልጅ የሆነችውን ሟች ተማሪ ቃልኪዳን ዘነበ አንገቷን አንቆ በመያዝና በማፈን የአስገድዶ መድፈር በመፈፀም ሕይወቷ እንዲያልፍ አድርጓል በሚል የወንጀል ምርመራ ተጣርቶበታል ሲል የሰው ምስክር እና የሰነድ ማስረጃ በማቅረብ ክስ መስርቶ ጥፋተኛው ላይ ተገቢው ውሳኔ እንዲተላለፍ አቅርቧል::

## ውሳኔ

**የሴቶችና ሕፃናት ዓቃቤ ህግ ዳይሬክቶሬት መዝገብ ቁጥር 008/16 በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን መዝገብ ቁጥር 890/15 እና በፌዴራል አቃቤ ሕግ እና በተከሳሽ አላዩ ሞገስ ደሳለኝ መካከል ሲካሔድ የነበረው ክርክር በመጨረሻም መቋጫ አግኝቷል፡፡ ተከሳሽ የተከሰሰበትን አስገድዶ የመድፈር እና ከባድ የግድያ ወንጀል መፈፀሙን ማስረጃዎች ተሰምተው በበቂ የቀረቡ በመሆናቸው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ችሎት የነበረው ክርክር ሲጠናቀቅ የቀረበውን ሰው የመግደል ወንጀል በተመለከተ ክስና ማስረጃውን ከሕግ ጋር አገናዝቦ ወንጀል ፈፃሚውን ያርማል ሌሎችንም ያስተምራል ብሎ ባመነበት በግንቦት 09 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተከሳሹ የ19 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡**

መዝናኛ

## ማረፊያ/ ትዝብት

# ቦንዳ ከፍርሃት ወደ ኩራት

**ዋሰልኝ አየለ**

ቦንዳ የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የማውቀው ልጅ እያለሁ በአካባቢያችን ልብስ የሚሰፉ ሰዎች የሚሸጡት ብትን ጨርቅ ነበር:: ልብስ የሚያሰፉ ሰዎች ተለክተው ከብትን ጨርቁ የመረጡትን አይነትና ቀለም አዝዘው ይሄዳሉ:: ይሄው ብትን ጨርቅ የጣውላ ቅርጽ ባላት ስስ መጠቅለያ ተጠቅልሎ ገበያ ላይ ይሸጣል:: የሚሸጡትም በብዛት በልብስ ስፌት ሥራ ላይ ያሉ ሰዎች ናቸው:: ወንድሜ ከእነዚህ አንዱ ስለነበር የብትን ጨርቁ መጠቅለያዋን ስስ ጣውላ በእርሳስ እየጻፍኩ እለማመድባት ነበር:: ይህ የተጠቀለለ ብትን ጨርቅ ቦንዳ ይባል ነበር::

ከዓመታት በኋላ በማኅበራዊ መገናኛ ዘዴዎችም ሆነ በዙሪያዬ ባሉ ሰዎች ‹‹ቦንዳ›› ሲባል መስማት ጀመርኩ:: ደግሞ ከተማ ቦታ ቦንዳ ምን ይሠራል? እያልኩ ብዙም ትኩረት ሳልሰጠው ቆየ:: በኋላ ነገሩን ስረዳ ቦንዳ ማለት ለካ የሰልባጅ ስም ተሽሞንሙኖ ማለት ነው:: እዚች ላይ አንድ የአካባቢያችን ገበሬ ከተማ ቦታ ሄዶ የተናገራትን አስቂኝ ገጠመኝ ላካፍላችሁ:: ያደረ እንጀራ (ደረቅ ማለት የጀመረ ማለት ነው) ጠዋት በድስት ቁሌት ነገር ተሠርቶ ይፈተፈታል:: ይህም በአካባቢያችን ግፍልፍል ተብሎ ይጠራል:: በሥራ ተወጥረው ወይም በሆነ አጋጣሚ ምግብ ማዘጋጀት የማይቻል ሲሆን ለመቆያ ተብሎ የሚደረግ ስለሆነ ብዙም ተመራጭ አይደለም:: እንዲያውም ሙያ የሌላትን ሴት ሲሳደቡ ‹‹ይቺ ግፍልፍላም!›› ይባላል::

እና ይህ የአካባቢያችን ገበሬ ከተማ ቦታ ይሄድና ምግብ ቤት ይገባል:: ምን ምን እንዳለ ሲጠይቅ ‹‹ፍርፍር›› የሚል ቃል ይሰማል:: የሆነ የተለየ ነገር መስሎት ፍርፍር አዘዘ:: ተሠርቶ መጣ፡፤ ሲያየው ያው ከቤቱ የሚያውቀው ነው:: ‹‹አይ! ግፍልፍል ስምሽን ቀይረሽ መጣሽ?›› አለ እየተባለ ሲቀለድ እሰማ ነበር::

ቦንዳ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ስሰማ ልክ እንደ ገበሬው ‹‹ሰልባጅ ስምሽን ቀይረሽ መጣሽ?›› የሚለው ነው ትዝ አለኝ:: ሰልባጅ ማለት ከዚህ በፊት የተለበሰ እና ታጥቦ የሚሸጥ ማለት ነው:: ይህ ቃል ከመለመዱ የተነሳ ለስድብነት ሁሉ ያገለግል ነበር:: የአሊቃ ዕቃ ማለት ነው:: የማይረባ፣ በቀላሉ የሚበላሽ ማለት ነው::

> **ዛሬስ? ዛሬማ ‹‹ቦንዳ›› የሚለው ቃል በትልቅ ባነር በኩራት የሚለጠፍ ነው**

ቦንዳ ግን ትንሽ ለየት የሚያደርገው ነገር አለ:: በአጭሩ ቦንዳ ማለት ብራንድ ልብስ ሆኖ በሀብታም ሃገራት የተለበሰ ማለት ነው:: በሀብታም ሀገራት ተለብሶ ወደ ድሃ ሃገራት የሚሸጥ ማለት ነው:: ለባሾቹ ድሃ ስላልሆኑ ምናልባትም ከአንድና ሁለት ቀን፣ ቢበዛ ከሳምንት ዕድሜ በላይ አይለብሱትም ተብሎ ይገመታል:: ያው ይገመታል ነው እንግዲህ!

ይህ የቦንዳ ልብስ ከዓመታት በፊት በድብቅ የሚሸጥ ነበር:: በድብቅ ማለት ሻጮቹ ቦንዳ መሆኑን ሳይናገሩ ማለት ነው:: ገዥዎቹም ቦንዳ መግዛታቸውን ሳይናገሩ ማለት ነው:: ከአንድ ዓመት በፊት ራሱ ቦንዳ እንዲህ እንደዛሬው በኩራት የሚሸጥ አልነበረም:: ‹‹ከቦንዳ ገዝቼ፣ ከቦንዳ ልግዛ›› የሚባልም አልነበረም:: ገዥዎችም ቦንዳ ቤት ሲገቡ ተደብቀውና ግራ ቀኙን አይተው ነው እየተባለ በማኅበራዊ ገጾች ይቀለድ ነበር:: ቦንዳ መልበስ ያስፈራ ነበር፤ ትንሽ እንደማሳፈር ይል ነበር::

ዛሬስ? ዛሬማ ‹‹ቦንዳ›› የሚለው ቃል በትልቅ ባነር በኩራት የሚለጠፍ ነው:: ገዥዎችም ጥንድ ጥንድ ሆነው (ፍቅረኛሞችም ሊሆኑ ይችላሉ) ሲለኩና ሲመርጡ እናያለን:: ቦንዳ ቤቶች ከመደበኞቹ ልብስ ቤቶች በላይ በወረፋ ተጥለቅልቀው ይታያሉ:: ሰው ብልጥ የሆነ ይመስላል፤ በእርግጥ ኑሮ አስገድዶት ነው:: ዋጋውን እንጂ የግል ክብር በሚባለው ነገር መንጠራራት እየቀረ ነው::

ኧረ እንዲያውም አሁን አሁን በተቃራኒው እየሆነ ነው:: ቦንዳ በሀብታም ሃገራት ያሉ ዜጎች የለበሱት ነው ተብሎ ስለሚታሰብ የተሻለ አድርጎ የማየት አመለካከት እየሰረጸ ነው:: ቦንዳ መልበስ ያሳፍር የነበረው ቀርቶ የሚያኮራ ሊሆን ነው:: ‹‹ቦንዳም!›› ብሎ ከመሳደብ ወደ ‹‹ዋው! ቦንዳ ነው እኮ የገዛ›› አድናቆት ልንሄድ ነው ማለት ነው::

እዚህ ላይ ግን አንድ ትልቅ ሐሜት አለ:: መደበኛዎቹ ልብስ ቤቶች ከቦንዳ እየገዙ ይሸጣሉ ይባላል:: በእርግጥ ብልጥ ለሆነ ሰው የሚለይበት ዘዴ ይኖረዋል:: ሆኖም ግን ብዙ ሰው ያጭበረብሩበታል:: በመደበኛ ልብስ ቤት ዋጋ ሰልባጅ ይሸጣሉ ማለት ነው:: እንዲያ ከሆነ ደግሞ ከራሱ ከቦንዳ ቤቱ መግዛት ይሻላል ማለት ነው:: ይህ አሠራር ገበያቸውን ይዘጋባቸዋል:: እንዲያውም ከወራት በፊት በወጣ መረጃ በቦንዳ ምክንያት መደበኛዎቹ ልብስ ቤቶች እየከሰሩ እንደሆነ መነገሩን እናስታውሳለን::

ሌላው ችግር ደግሞ ከሃገር ውስጥ ልብስ ይልቅ ቦንዳ መመረጡ ነው:: ‹‹ቦንዳ ቤት›› ብለው በሚሸጡ ቤቶች ውስጥ ያለው ክርክር ‹‹የምር ግን ቦንዳ ነው?›› የሚል ነው:: ከሃገር ውስጥ ዋና (አዲስ) ይልቅ ቦንዳው የተሻለ ተደርጎ ይታሰባል ማለት ነው:: የዚህ ችግሩ ግን የአመለካከት ብቻ አይደለም፤ የምርም ቦንዳው (ሰልባጅ ማለት እኮ ነው!) የተሻለ ጥንካሬም ሆነ ጥራት ስለኖረው ነው:: በዚያ ላይ አመለካከታችንም ቀላል ሚና የለውም:: ምንም ቢሆን ፈረንጅ የሠራው ይሻላል የሚል አመለካከት የሰረፀብን ነን:: የሃገር ውስጥ ምርቶቻችን ግን ይህ ሊቆጫቸው ይገባል፤ መንግሥትም ተገቢውን ትኩረት ሊሰጥ ይገባል::

መደበኞቹ ልብስ ቤቶች ላይ ግን ቁጥጥርና ክትትል መደረግ አለበት:: በመደበኛ ልብስ ዋጋ የቦንዳ ልብስ ሊሸጡ አይገባም:: ይህ ማለት ብዙዎች ያደርጋሉ ማለት አይደለም:: ትልልቅ የገበያ አዳራሾች (ሞል) ይህን ላያደርጉ ይችላሉ:: ዳሩ ግን ብዙ ሰው ደግሞ ከእነርሱ የመግዛት አቅም አይኖረውም:: የቀበቶ ዋጋቸው ብቻ እኮ ከመደበኛ ልብስ ቤት ሦስት ሱሪ ሊገዛ ይችላል:: ስለዚህ ከእነርሱ በታች ያሉት መደበኛዎቹ ልብስ ቤቶች እርስ በእርሳቸው ሊገማገሙ ይገባል:: ምክንያቱም አንዱ የሚሠራው ስህተት የብዙዎችን ገበያ ያበላሻል::

‹‹ለመሆኑ ግን ቦንዳ ለምን ተስፋፋ? ሰዎችስ ለምን መረጡት?›› የሚለውን ግን እንደ መንግሥትም እንደ ግለሰብም ሊያሳስበን ይገባል:: ኑሮ ውድነት ነው:: ሰዎች በውድ ዋጋ ‹‹ኦርጂናል›› ነገር መግዛት ስላልቻሉ ነው:: በሃገራቸው ምርት ቢኮሩም በሚቀንስ ዋጋ የተሻለ ጥራት ያለው ነገር ይሻለናል ብለው በማመን ነው::

ሁለት ነገሮች ግን ልብ ይባሉ:: መደበኛዎቹ ልብስ ቤቶች ቦንዳ እንዳይቀላቅሉ ክትትል ሊደረግ ይገባል፤ የሃገር ውስጥ አልባሳት ላይ መንግሥት ትኩረት አድርጎ ተፈላጊ እንዲሆኑ ይደረግ!

## ዓለም አቀፍ

### ሰሜን ኮሪያ ትራምፕ ምርጫውን ካሸነፉ የኑክሌር ንግግር ለማድረግ ፍላጎት እንዳላት ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



ሰሜን ኮሪያ ትራምፕ ምርጫውን ካሸነፉ የኑክሌር ንግግር ለማድረግ ፍላጎት እንዳላት ተገለጸ።

ሰሜን ኮሪያ ትራምፕ በድጋሚ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሆነው የሚመረጡ ከሆነ የኑክሌር ንግግር የማድረግ ፍላጎት እንዳላት እና አዲስ የንግግር ስትራቴጂ እያዘጋጀች እንደሆነ በቅርቡ ሰሜን ኮሪያን ከድተው ወደ ደቡብ ኮሪያ የተቀላቀሉት ዲፕሎማት ተናግረዋል።

በኩባ ሰሜን ኮሪያን በዲፕሎማትነት ሲያገለግሉ የነበሩት ሪ ኢል ግዩ መከዳት ዓለምአቀፍ መነጋገሪያ ሆኖ ነበር።

ከፈረንጆቹ 2016 ወዲህ ሰሜን ኮሪያ የከዱ ከፍተኛ ባለሥልጣን ናቸው።

ከዓለምአቀፍ ሚዲያዎች ጋር ባደረጉት የመጀመሪያ ቃለ ምልልስ ሩሲያ፣ አሜሪካ እና ጃፓን ዋነኛ የሰሜን ኮሪያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ትኩረቶች መሆናቸውን ገልጸዋል።

ከሩሲያ ጋር ጠንካራ ወታደራዊ ግንኙነት እየመሠረተች ያለችው ሰሜን ኮሪያ ትራምፕ በመጭው ኅዳር በሚካሄው ምርጫ ካሸነፉ የመደራደር ፍላጎት አላት ብለዋል።

እንደገለጹት ሰሜን ኮሪያ ሽብርን ከሚደግፉ ሀገራት ዝርዝር ውስጥ ስሟ እንዲሰረዝ፣ በጦር መሣሪያ ፕሮግራሞቿ ላይ የተጣሉት ማዕቀቦች እንዲነሱ እና የኢኮኖሚ ርዳታ ተጠቃሚ እንድትሆን በማለም የፒዮንግያንግ ዲፕሎማቶች ለእዚያ ሁኔታ የሚሆን ስትራቴጂ እያዘጋጁ ናቸው።

ይህ አስተያየት ሰሜን ኮሪያ በቅርቡ ከአሜሪካ ጋር የሚደረግ ድርድር የመሳካት ዕድሉ ያነሰ መሆኑን እና ወታደራዊ ፍጥጫ እንደሚኖር ካስጠነቀቀች በኋላ የተሰጠ ነው።

በፈረንጆቹ 2019 የሰሜን ኮሪያው መሪ ኪም ጆንግ ኡን እና ትራምፕ በቬትናም በማዕቀብ ጉዳይ ያደረጉት ድርድር ሳይሳካ ቀርቷል። እንደሚሉት ከሆነ ድርድሩ ያልተሳካው በኑክሌር ዲፕሎማሲ ጉዳይ ልምድ በሌላቸው ወታደራዊ አዛዦች ምክንያት ነው ብለዋል።

ሰሜን ኮሪያ ሩሲያን፣ ደቡብ ኮሪያ ደግሞ አሜሪካን ከጎኗ በማሰለፍ ከፍተኛ ቅራኔ ውስጥ ከገቡ ውለው አድረዋል።

የሩሲያው ፕሬዚዳንት ፑቲን በቅርቡ ሰሜን ኮሪያን በጎበኙበት ወቅት፣ ሩሲያ እና ሰሜን ኮሪያ ወታደራዊ ስምምነት መፈራረማቸው ይታወሳል።

### ቱርክ ኢንስታግራም በግዛቷ እንዳይሠራ እግድ ጣለች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ቱርክ ኢንስታግራም በግዛቷ እንዳይሠራ እግድ ጣለች።

ቱርክ የሜታው የማኅበራዊ ሚዲያ መተግበሪያ ኢንስታግራም በግዛቷ እንዳይሠራ እግድ መጣሏን የሀገሪቱ የኢንፎቴክ ተቆጣጣሪ በትናንትናው ዕለት አስታውቋል።

ተቆጣጣሪው አካል እግድ የጣለበትን እና እግዱ እስመቼ እንደሚቆይ ግልጽ አላደረገም።

ይህ ርምጃ የተወሰደው የቱርክ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን ፋህረቲን አልቱን ለፍልስጤሙ ታጣቂ ቡድን ወሳኝ የሆነውን እስማኤል ሀኒየህ ግድያን አስመልክቶ የወጡ የኀዘን መግለጫዎች ኢንስታግራም አጥፍቷል ሲሉ ባለፈው ረቡዕ ትችት ከሰነዘሩ በኋላ ነው።

"ይህ ግልጽ እና ቀላል ነው፤ ሀሳብን መገደብ ነው" ያሉት የቱርክ ፕሬዚዳንት ጽሕፈት ቤት የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አልቱን ኢንስታግራም ለዚህ ድርጊቱ የተጣሰ ፖሊሲ ስለመኖሩ አልጠቀሰም ብለዋል።

የኢንስታግራም እናት ኩባንያ የሆነው ሜታ በእግዱም ሆነ በአልቱን አስተያየት ዙሪያ የሰጠው አስተያየት የለም።

የሀማስ የፖለቲካ መሪ እስማኤል ሀኒየህ በአዲሱ የኢራን ፕሬዚዳንት ፔዝሺኪያኒ በዓለ ሲመት ላይ ከተሳተፈ በኋላ ቴህራን ውስጥ በተፈጸመ ጥቃት ተገድሏል።

ሀማስ ጥቃቱን በማድረስ እስራኤልን የወነጀለ ሲሆን እስራኤል ግን ግድያውን በተመለከተ እስካሁን በይፋ ያለችው ነገር የለም።



# መጋቢ አዕምሮ

# እንዴት ጠንካራ መሆን ይቻላል?



**አስናቀ ፀጋዬ**

የሰው ልጅ በብዙ ውጣውረዶች ይፈተናል:: ፈተና ለሰው ልጅ አዲስ አይደለም:: በኑሮ የሰው ልጅ ይፈተናል:: በኢኮኖሚ ይፈተናል:: በጦርነት ይፈተናል:: በሰላሙ ጊዜም ፈተናው አይቀርለትም:: በፖለቲካ ይፈተናል:: በማህበራዊ ሕይወቱም ፈተናዎች ይገጥሙታል:: ሀዘንና መከራ ይፈራረቁበታል:: ብቸኝነትና ባዶነት ሊሰማውም ይችላል:: የሥነ ልቦና ጉዳትና የልብ ስብራትም ያጋጥመዋል:: ብቻ ምኑ ቅጡ የሰው ልጅ በብዙ የሕይወት ስንክሳር ውስጥ ከበርካታ አታካችና ተደጋጋሚ ፈተናዎች ጋር ይጋፈጣል::

ነገር ግን የሰው ልጅ ለተደራራቢ ፈተናዎች ብቻ አይደለም የተፈጠረው:: የሚገጥመውን ፈተና ያክል ደስታው፣ ኩራቱ፣ ፈንጠዝያው፣ ሃሴቱም የዛኑ ያህል ነው:: ኑሮው ሲሞላለት፣ ኪሱ ሲያብጥ፣ ጎተራው ሲሞላ የሚያደርገው ይጠፋዋል:: ምድር ትጠበዋለች:: ‹‹ምነው ደስታና ፈንጠዝያው፤ ምቾትና ድሎቱ ሁሌም በሆነ›› ይላል:: ይህ ደግሞ የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ባህሪ ነው:: እንዲያም ሆኖ ግን የሰው ልጅ ከሕይወት ውጣውረድና ፍትጊያ ሊያመልጥ አይችልምና በሕይወት ውጣውረድ ውስጥ እንዴት ፈተናዎችን ተቋቁሞ መዝለቅ እንዳለበት በቅጡ ሊረዳ ይገባል::

‹‹እንዴት ጠንካራ መሆን ይቻላል?›› የሚለው የብዙዎች ጥያቄ ነው:: ጥንካሬ ብዙዎች በሕይወታቸው ውስጥ ለማግኘት የሚጥሩት ተፈላጊ ባሕርይ ነው:: እራስን ከማወቅ፣ ማጎልበትና ከማሳደግ አንፃር እንዴት ጠንካራ መሆን እንደሚቻል ማወቅ ተገቢ ነው። የግል ኃይልን ለማግኘት በርካታ አስፈላጊ ነጥቦችን ከግምት ውስጥ ማስገባት እንችላለን:: በራስ የመተማመን ጠንካራ መሠረት መጣል ጠቃሚ ጅምር ነው። አንድ ሰው በችሎታው ላይ እምነት ሲኖረው ስኬትን ማግኘት እና ፈተናዎችን በልበ ሙሉነት ማሸነፍ ይችላል:: በተጨማሪም የግል ችሎታዎችን ማጎልበት ያስፈልጋል:: ይህም አዳዲስ እውቀቶችን እና ክህሎቶችን፣ ቋሚ ትምህርትን እና ቀጣይነት ያለው እድገትን በማግኘት ነው ሊሳካ የሚችለው::

አንድ ሰው ችሎታውን ማዳበር እና በተለያዩ የሕይወቱ ዘርፎች መሻሻል ሲችል ጥንካሬ እና በራስ መተማመንን ያገኛል። ቁርጠኝነትን ማጠናከር እና ጽናት ጠንካራ ለመሆን ሌሎች ሁለት አስፈላጊ ነገሮች ወሳኝ ናቸው። አንደኛ አንድ ሰው ተግዳሮቶችን እና ችግሮች ሲያጋጥመው በጽናት እና በቆራጥነት ወደፊት መቆም መቻል አለበት። ሁለተኛ ከሌሎች ጋር አዎንታዊ እና ጤናማ ግንኙነቶችን መገንባትን ግድ ይላል:: የአካል ብቃት እንቅስቃሴ በማድረግ፣ ለአመጋገብ ትኩረት በመስጠት እና በቂ እረፍት እና መዝናናት በማድረግ አካል እና አእምሮ እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል። አካል እና አእምሮ በጥሩ ሁኔታ ላይ ሲሆኑ የአካል እና የአዕምሮ ጥንካሬን ይጨምራል::

ሰዎች በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው የሚያጋጥሟቸውን የተለያዩ ችግሮች ለመቋቋም የሚያስችሏቸውን ባሕርያት ማዳበር ያስፈልጋቸዋል:: የጠንካራ ስብዕና ባህሪያት ለሰዎች በራስ መተማመን እና ስኬትን ለማግኘት እና ችግሮችን ለማሸነፍ ብርታት ይሰጣሉ:: ለጠንካራ ስብዕና አስፈላጊ ከሆኑት ባሕርያት አንዱ ጽናት ነው:: ፅናትና ቁርጠኝነት አንድ ሰው ጠንክሮ መሥራትን እንዲቀጥል እና ችግሮችን እንዲያሸንፍ የሚገፋፋው አንቀሳቃሽ ኃይል ነው። ጠንካራ ሰው በቀላሉ ተስፋ የሚቆርጥ ሳይሆን ፈተናዎችን ለማደግ እንደ እድል የሚጠቀም ነው::

አንድ ሰው ታጋሽ ከሆነና ግቦቹን ለማሳካት ቆርጦ ከተነሳ ተጨባጭ ውጤቶችን ማምጣትና የሚጠብቀውን ግብ ማሳካት ይችላል:: እዚህ ጋር በራስ መተማመን እንደ ጠንካራ ስብዕናም ይቆጠራል። በራስ የሚተማመን ሰው በችሎታው ያምናልና ስኬትን ለማግኘት ባለው ችሎታ ይተማመናል። ፈተናዎችን አይፈራም:: ለጥርጣሬ እና ለጭንቀት እጅ አይሰጥም:: ለራስ መተማመን ምስጋና ይግባውና አንድ ጠንካራ ሰው ከፊቱ እንቅፋቶች ቢያጋጥሙት ለመጋፈጥ ብርታት ይኖረዋል:: ስሜትን የመቆጣጠር ችሎታ የጠንካራ ስብዕና አስፈላጊ ከሆኑት ባሕርያት ሌላኛው ነው:: ጠንካራ ሰው ጫናዎችንና ውጥረቶችን በራስ መተማመን ሊቆጣጠራቸው ይችላል:: በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ በንቃት የማሰብ እና ትክክለኛ ውሳኔዎችን የማድረግ ችሎታም አለው::

> **‹‹አንድ ሰው ታጋሽ ከሆነና ግቦቹን ለማሳካት ቆርጦ ከተነሳ ተጨባጭ ውጤቶችን ማምጣትና የሚጠብቀውን ግብ ማሳካት ይችላል። እዚህ ጋር በራስ መተማመን እንደ ጠንካራ ስብዕናም ይቆጠራል። በራስ የሚተማመን ሰው በችሎታው ያምናልና ስኬትን ለማግኘት ባለው ችሎታ ይተማመናል። ፈተናዎችን አይፈራም። ለጥርጣሬ እና ለጭንቀት እጅ አይሰጥም።››**

አንድ ጠንካራ ሰው ስሜቱን መቆጣጠር ሲችል የራሱ መሪ ይሆናልና በዙሪያው ባሉት ሰዎች ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል:: ጠንካራ ስብዕና ስለመኖሩ የሚለዩት ሌሎች ባህሪያት ትዕግስትና መቻቻል ናቸው:: ጠንካራ ሰው ስኬት ፈጣን ርምጃ እንዳልሆነ ይገነዘባል:: ይልቁንም ጥረት እና ጊዜ እንደሚጠይቅ ያውቃል:: ስህተቶችን እና ውድቀቶችን በጥበብ ያስተናግዳል:: እነሱን ከማስወገድ ይልቅ ይማራል። ትዕግስት እና መቻቻል ለጠንካራ ሰው በሕይወቱ ውስጥ ሚዛን እንዲያገኝ እና ችግሮችን በአዎንታዊ መልኩ እንዲቋቋም ችሎታ ይሰጠዋል::

በሌላ በኩል ጠንካራ ለመሆን የሚረዱ ሌሎች በጎ ልማዶችም አሉ:: ጡንቻን ለማጠንከርና ጽናትን ለማሻሻል አዘውትሮ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ አስፈላጊ ነው። እንደ ክብደት ማንሳት፣ መሮጥ እና ዮጋ ያሉ የተለያዩ የስፖርት ዓይነቶችን መርጦ መለማመድ ይቻላል:: እንቅስቃሴ ከመጀመር በፊት ግን ከችሎታ ጋር የሚስማማ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ መርሃ ግብር መምረጥ ያስፈልጋል:: ጤናማ እና የተመጣጠነ ምግብ መመገብም ጥንካሬን ለማጎልበት ይረዳል:: እንደ ፕሮቲኖች፣ ካርቦሃይድሬትስ እና ጤናማ ቅባቶች ያሉ አስፈላጊ ንጥረ ነገሮችን የያዙ ምግቦችን መመገብ ይገባል::

በአመጋገብ ውስጥ ትኩስ ፍራፍሬዎችንና አትክልቶችን መመገብም ያስፈልጋል:: ጥሩ እንቅልፍ፣ ጥሩ እንቅልፍ ለጤናማ አካል እና አእምሮ አስፈላጊ ነው። ሰውነት ከከባድ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ በኋላ ለማገገም እና ለመዝናናት በቂ ጊዜ ይፈልጋል። ከ7-8 ሰዓታት ለመተኛት መሞከርም ይገባል:: የእንቅልፍ ጥራትን ለመጨመር የሚያረጋጋ የመኝታ ሰዓትን መተግበርም ብልህነት ነው።

በሌላ በኩል ጭንቀትና ውጥረት አጠቃላይ ጥንካሬንና የአካል ብቃትን ሊቀንስ ይችላል:: ስለዚህ የጭንቀት መንስኤዎችን ለመለየት መሞከር ያስፈልጋል:: ጭንቀትና ውጥረትን ለመቀነስ እንደ ዮጋ ፣ ማሰላሰል እና የመዝናኛ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ተገቢ ነው:: ዘና ማለት ለራስ ጊዜ መስጠትም ያስፈልጋል:: በነገሮች የተጠመደ ሕይወት ትዕግስትን ያዳክማል:: የማተኮር ችሎታን ይቀንሳል:: ስለዚህ የምንወዳቸውን ነገሮች በማድረግ ራስን ማስደሰት ይገባል:: ማንበብ፣ ሥዕል መሳል፣ ሙዚቃ ማዳመጥ ወይም ሌሎች አዝናኝ ነገሮችን መከወንም ይቻላል::

በአእምሮና በስሜት ጠንካራ ለመሆን የአእምሮ ጤናን መንከባከብ ያስፈልጋል:: ለዚህ ደግሞ እንቆቅልሾችን መፍታት ወይም ስለ አዳዲስ ነገሮች ማንበብ የአእምሮ ማነቃቂያ ሆነው ሊጠቅሙ ይችላሉ:: እንዲሁም ግቦችዎን እና እነሱን ለማሳካት እቅዶችዎን ያብራሩ:: ይህም የመቆጣጠር እና በራስ የመደሰት ስሜት ይጨምራል:: ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን መከተልም ይገባል::

የቅርብ እና ደጋፊ ግንኙነቶች ስሜታዊ ጥንካሬን ያጠናክራሉና ለደስታ እና እርካታ ስሜታችን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። ልዩ ጓደኝነትን ለመፍጠር እና አስደሳች እና ጥልቅ ግንኙነትን በመቀላቀል በማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ለመደሰት ጊዜን ማዋልም ተገቢ ነው:: ስለዚህ ለራስዎ ደግ ይሁኑ:: ለራስዎ ደግ ለመሆን እና እራስዎን ለመውደድ ይሞክሩ:: የማያቋርጥ አሉታዊ ትችቶችን ያስወግዱ:: ለራስዎ እና ለፍላጎቶችዎ ትኩረት ይስጡ::

የግል ጥንካሬን ለማግኘት በርካታ ጠቃሚ ምክሮች አሉ:: ከነዚህ ውስጥ በራስ መተማመንን ማሳደግ፣ በአዎንታዊ ማሰብ፣ በራስ መተማመን፣ መናገር እና ያለፉ ስኬቶች ላይ መታመን ከዋና ዋናዎቹ ጥቂቶቹ ናቸውና ተግባራዊ ያድርጓቸው:: በራስ መተማመንዎን ይጨምርልዎታል:: ነገር ግን ይህን ለማድረግ የተወሰነ ጊዜና ጥረት ሊጠይቅ ይችላል:: ግን ዋጋው ከፍ ያለ ነው:: ጠንካራ ሰው በፍርሃትና በጭንቀት ውስጥም ቢሆን መናገር እና ከባድ ውሳኔዎችን ማድረግ ይችላል:: ፍርሃታችንን በምንጋፈጥበት ጊዜ ታላላቅ ነገሮችን ለማግኘት የሚያስችል ጥንካሬ እናገኛለን።

በሌላ በኩል በትክክል ምላሽ ለመስጠትን ትምህርት መውሰድ ተገቢ ነው:: አንዳንድ ሰዎች ለጭንቀት ሊጋለጡ ይችላሉ:: ነገር ግን ትክክለኛው ልዩነት ችግሩን እንዴት መያዝ እንደሚችሉ ነው:: ለጭንቀት ጤናማ እና የተረጋጋ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል:: ጭንቀትን ወደ መልካም እድል መቀየርም ተገቢ ነው:: ስለዚህ ሰዎች በግላዊ የእድገት ጉዞ ወቅት ታጋሽ መሆን አለባቸው:: ለመለወጥ እና ለማሻሻል ጊዜ እና ጥረት ሊወስድ እንደሚችል መረዳት አለባቸው:: ትዕግስት እና ቀጣይነት ያለው መሻሻል ለጠንካራ ስብዕና ስኬት መሠረት ናቸው::

ከዚህ አንፃር ከሌሎች ጋር ጠንካራ ስብዕናን የተላበሰ ግንኙነት እንዲኖረን ከተፈለገ በመጀመሪያ ታጋሽ መሆን ይጠበቅብዎታል:: በማህበራዊ ሕይወታችን ከሌሎች ጋር ግንኙነት ስንፈጥር ከዛኛው ወገን የተለያዩ አስተያየቶችና እንግዳ ባህሪያት ሊያጋጥመን ይችላል። እዚህ ጋር ታዲያ ለመግባባትና ለይቅርታ እድል መስጠት አስፈላጊ ነው:: ትዕግስት እና መቻቻል ጥሩ ግንኙነትን ያበረታታል። በሌላ በኩል ደግሞ ፍትሃዊ እና አዛኝ መሆን ይኖርብናል:: እንዲሁም ለችግሮቻቸው እና ለስሜታቸው ርህራሄ እና አሳቢነት ማሳየት ይጠበቅብናል::

ፍትሃዊና ሩህሩህ መሆን የሌሎችን እምነት ለመገንባት እና ከእነሱ ጋር ያለዎትን ግንኙነት ያጠናክራል። በሌላ በኩል ደግሞ በራስዎ እና በችሎታዎ እርግጠኛ መሆን አለብዎት። ጠንካራ ስብዕና ያላቸው ሰዎች በልበ ሙሉነትና በግልፅ መናገርና ሃሳባቸውን መግለጽ የሚችሉ ናቸው። ስለዚህ፣ በራስ መተማመንዎን በግል እድገት፣ ችሎታዎን በማወቅ እና እሴቶችዎን እና መርሆዎችዎን በመግለጽ ያሳድጉ። ከውሳኔዎችዎ እና ሀሳቦችዎ በስተጀርባ ለመቆም ዝግጁ ይሁኑ።

ከዚህ ባለፈ ከሌሎች ጋር አወንታዊ እና ሚዛናዊ ግንኙነቶችን ይገንቡ:: ከሌሎች ጋር ግንኙነትን ለማሻሻል እና ጠንካራ ግንኙነቶችን ለመገንባት እድሎችን ይፈልጉ። በማህበረሰብ እንቅስቃሴዎች እና በሚፈልጉት ማህበራዊ ቡድኖች ውስጥ እራስዎን ያሳትፉ። እንዲሁም ለሌሎች ርዳታ እና ድጋፍ መስጠት እና በቅንነት ማዳመጥ ይቻሉ:: አዎንታዊ ግንኙነቶችን መገንባት ስብዕናዎን ያሳድጋል፤ ጠንካራም ያደርግዎታል።

ስለዚህ በጥቅሉ ችግሮች ሲያጋጥሙኝ እንዴት ጠንካራ መሆን እችላለሁ? ብሎ ራስን መጠየቅና በመጀመሪያ አንድ ሰው ጠንካራ ለመሆን እውነተኛ ፍላጎት ሊኖረው ይገባል:: ሁለተኛ በሁለተኛ ደረጃ ችግሮችን ለመቋቋም አስፈላጊውን እውቀትና ችሎታ ማግኘት አለበት:: ሦስተኛ ለራሱ ጠንካራ መሠረት መገንባት ይኖርበታል:: አራተኛ የአእምሮ እና የአካል ጤንነቱን መጠበቅ አለበት።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ውሳኔው የውጪ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የሚያስችል ትልቅ እድል ይዞ የመጣ ነው

መንግሥት ላለፉት ስድስት ዓመታት በተጠና መንገድ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ወደ ተሻለ ደረጃ ማሸጋገር የሚያስችሉ የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል። ከነዚህም ውስጥ በዋነኛነት የሚጠቀሰው ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ነው ።

ሀገሪቱ ያላትን አቅም ታሳቢ ያደረገ፤ እነዚህን አቅሞች ወደ ልማት በመለወጥ የሕዝባችንን የዘመናት የመልማት/የመበልጸግ ጥያቄዎችን መመለስ የሚያስችሉ የተለያዩ ስትራቴጂክ ዕይታዎችን ያካተተው ይህ ፕሮግራም፤ ከሁሉም በላይ የውስጥ አቅምን አሟጦ መጠቀምን ታሳቢ ያደረገ ነው ።

ፕሮግራሙ እስካሁን ባለው አፈጻጸም፣ ለሀገሪቱ ልማት ወሳኝ ናቸው ያላቸውን የቱሪዝም፣ የግብርና፤ የኢንዱስትሪ፣ የማዕድን እና የቴክኖሎጂ ዘርፎችን በመለየት እና ለዘርፎቹ ልዩ ትኩረት እንዲሰጣቸው በማድረግ ተስፋ ሰጭ ውጤት እንዲመዘገብ አስችሏል። በዚህም የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ከማነቃቃት ባለፈ ተከታታይ ዕድገት እንዲያስመዘግብ አስችሏል።

ይህንን እንደ ሀገር እየተመዘገበ ያለውን ልማት ለማስቀጠል እና ዘለቄታ እንዲኖረው ለማስቻል አሁን ላይ የተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል። ትግበራው ቀደም ሲል የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ሊበራይዝ ለማድረግ የተደረጉ ጥረቶችን ወደ ላቀ ደረጃ ማሸጋገር የሚያስችል እንደሆነ ይታመናል።

በተለይም የውጪ ኢንቨስትመንት ከመሳብ፣ በሕገወጥ መንገድ ከሀገር የሚወጣውን የውጪ ምንዛሪ በማዳን ሀገሪቱን ሁለንተናዊ በሆነ መንገድ እየተፈታተናት ያለውን የውጪ ምንዛሪ እጥረት ስትራቴጂክ በሆነ መንገድ በመፍታት ለተጀመረው ልማት አቅም የሚሆን ሀብት ለመፍጠር ትልቅ አስተዋፅዖ የሚያበረክት ይሆናል።

እስካሁን የነበረው የውጭ ምንዛሪ ሥርዓት የተረጋጋ የውጪ ምንዛሪ ተመንና ዝቅተኛ የዋጋ ንረት መኖሩን ለማረጋገጥ የታለመ ቢሆንም፣ በሂደት ግን ለጥቁር ገበያ መስፋፋት፣ ለከፍተኛ የዋጋ ንረት፣ በከበሩ ማዕድናት ለሚደረግ ሰፊ የኮንትሮባንድ ንግድ እንዲሁም የውጪ ምንዛሪ ከባንክ ሥርዓት ውጭ እንዲሆንና ከሀገር እንዲሸሽ አንዱና ዋነኛ ምክንያት ሆኖ ቆይቷል፡፡

በውጭ ምንዛሪ የሚካሄድ ኢ-መደበኛ ገበያዎች እንዲስፋፉ በማድረግ፣ አብዛኛው የንግድ ማኅበረሰብና የሐዋላ ተገልጋዮች የሚፈልጉትን የውጪ ምንዛሪ ከጥቁር ገበያ እንዲገዙ እና እንዲሸጡ አድርጓቸዋል፡፡ ይህም ከአምራች ዘርፎች ይልቅ ጥቂት ሕገወጦችና ደላሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ሥር የሰደደ የውጪ ምንዛሪ እጥረት እንዲከስት አድርጓል፡፡

በዚህ የተነሣ በርካታ የንግድ ድርጅቶችና ባለሀብቶች ተጎጂ ሆነዋል፤ የወጪ ንግድንና የፋብሪካ ምርቶችን ለማስፋፋት፣ የውጪ ኢንቨስትመንትን ለመሳብና የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ክምችት ለማሳደግ የተቀመጡ ፖሊሲዎችንና ጥረቶች በሚጠበቀው ደረጃ ውጤታማ እንዳይሆኑም ተግዳሮት ሆኗል፡፡

አሁን ላይ ወደ ሥራ የገባው አዲሱ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት፤ ሀገሪቱን በገበያ ላይ የተመሠረተ ተወዳዳሪ ወደሆነ የውጭ ምንዛሪ ሥርዓት የሚያሸጋግራት፣ በኢኮኖሚው ውስጥ ለረጅም ጊዜ ተንሰራፍቶ የቆየውንና ሥር የሰደደውን የማክሮ ኢኮኖሚ አለመረጋጋትና መዛባት እንደሚያሻሽልም ይታመናል፡፡

የውጭ ምንዛሪ እጥረትን ለመቅረፍ፣ የወጪ ንግድ ተወዳዳሪነትን ለማጎልበት፣ የውጪ ኢንቨስተሮችን በመሳብ፣ የውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ፣ የንግድ ሥርዓቱ ከአጎራባችና ከሌሎች ሀገራት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ትልቅ አስተዋፅዖ ይኖረዋል፡፡

በተለይም ሀገሪቱ ያላትን የተፈጥሮ ሀብት እና ከፍተኛ የሰው ኃይል አቀናጅቶ ዘላቂ ልማት ለመፍጠር የሚያስፈልገውን ሀብት ከተለያዩ አማራጮች /በብድር፣ በርዳታ እና በቀጥታ ኢንቨስትመንት/ ወደ ሀገር ውስጥ ለመሳብ የሚኖረው ፋይዳ ከፍ ያለ እንደሚሆን ይታመናል።

ሀገሪቱ ዓለም አቀፍ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ሂደት ውስጥ ተወዳዳሪ እንድትሆን በማስቻል፣ እንደሀገር ለጀመርነው ድህነትን ታሪክ የማድረግ ጉዞ ትልቅ አቅም መሆን እንደሚችል፣ በተመሳሳይ የታሪክ ምዕራፍ ካለፉ ሀገራት ተሞክሮ ለመረዳት በብዙ የሚያዳግት አይሆንም!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ያልተፈታው የቢሮክራሲ ሽምቀቆ

ታምራት ተስፋዬ

በአመራር ጥበብና ብቃታቸው «ምርጥ» ከሚባሉ እንዲሁም ስኬታማ ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች አንዱ ናቸው:: በርካቶችም ዓለማችን ከተመለከተቻቸው ዋና ሥራ አስፈፃሚዎች አንዱ ናቸው «greatest C.E.O. of the modern age» ሲሉም ስለ ሥራና አመራር ብቃታቸው ይመሰክራሉ:: እኤአ በ1999ኙም «የክፍለ ዘመኑ ምርጥ የሥራ መሪ በሚል ተመርጠዋል:: እኚህ ሰው ጃክ ፍራንሲስ ዌልች ወይም በአጭሩ ጃክ ዌልች ይባላሉ::

እ.ኤ.አ በ1935 በአሜሪካ ማሳቹሴት የተወለዱት እኚህ ሰው፣ ከጀማሪ ባለሙያነት ተነስተው የአውሮፕላን/ የአቪየሽን/ የሕክምና እና የፋይናንስ ቁሳቁሶችን በማምረት የሚታወቀው የጀነራል ኤሌክትሪክ ዋና ሥራ አስፈጻሚና ሊቀመንበር ሆነው ሠርተዋል:: በዚህ ኩባንያ ውስጥ ለአራት አስርት ዓመታት ከጀማሪ ባለሙያነት ተነስተው የላይኛውን የአመራር እርካብ በመጨበጥ ስኬትን በስኬት ላይ ደራርበዋል።

የኩባንያው የገበያ ዋጋ እአአ በ1981 ከነበረበት 12 ቢሊዮን ዶላር በ2001 ወደ 410 ቢሊዮን ዶላር መወንጨፉም የሰውየውን የአመራር ጥበብ፣ ብቃትና ስኬታማነት ለመረዳት በቂ ማስረጃ ሆኖ መቅረብ የሚችል ነው:: ሰውየው በአመራር ዘመናቸው የኩባንያው የገበያ ድርሻ እየሰፋ ትርፍን በትርፍ ላይ እየደረበ እንዲጓዝና ስምና ዝናው ከምርጦች ተርታ እንዲሰለፍ ለማድረጋቸው ታዲያ በተለይም የሚከተሉት ዋነኛ የሥራ አመራር ፍልስፍና ብሎም ማጠንጠኛ እጅግ ወሳኝ ስለመሆኑ ይታመናል:: ይህ ፍልስፍናም «ለሌሎች መማሪያ መሆን ይችላል» በሚል በንድፈ ሀሳብ ደረጃ «ዌልቼዝም» ቲዮሪ በሚል ተቀምሮ በርካቶች ዘንድ ደርሷል።

በሰውየው የአመራር ጥበብና ስኬት ዙሪያ በተለይም ዌልቼዝም ፍልስፍናን በሚመለከት የተጻፉ ጽሑፎችም፣ ለዌልች የስኬት ምክንያት ከሁሉም በላይ ውጤት ላያ ማተኮር፣ የአስተዳደር እርከን ሠንሠለትን ማሳጠርና የተስተካከለ ቢሮክራሲን መተግበር የምርትና ምርታማነት ቁልፍ ነው የሚል አስተሳሰብና የፀና አቋማቸው ስለመሆኑ ያትታሉ::

«የተስተካከለ ቢሮክራሲ የሁለንተናዊ እድገት ቁልፍ ነው» የሚሉት እኒህ ሰው፣ እሳቤያቸውን በስኬት አስደግፈው በአደባባይ ማስመስከር የቻሉ እንደመሆኑ በአካል ባይኖሩም ዛሬም ድረስ የበርካቶች ድጋፍና አድናቆት አላቸው:: የአመራር ጥበብና ይህ እሳቤያቸውን የሚከተሉና ሥራ ላይ የሚተገብሩ ተቋማት፣ ሃገራትና አመራሮችም ቁጥራቸው ቀላል የሚባል አይደለም::

በእርግጥም ቢሮክራሲ በተቋማት ብቻ ሳይሆን በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ አሉታዊ ወይንም አዎንታዊ ሊሆን ይችላል። ይህም ተፅዕኖ ሊወሰን የሚችለው በቢሮክራቲክ አሠራር መኖር አለመኖር ሳይሆን ቢሮክራሲው በተዋቀረበትና በሚተገበርበት ሂደት ላይ ነው። ይህም ማለት የቢሮክራሲ አሠራር በብቃት፣ በግልፅኝነትና ተጠያቂነት ላይ የተመሠረተ እንዲሁም የቢሮክራሲው አወቃቀር ሥራዎችን ሊያቀሉ የሚችሉ ዘመናዊ ስልቶችንና ቴክኖሎጂዎችን የሚጠቀም ከሆነ የሰው ኃይልንና የቁሳቁስ ብክነትን በመቀነስ በሀገር ሁለንተናዊ እድገት ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ ሊያስመለክት ይችላል።

ቢሮክራሲ በጣም የተንዛዛና ኋላቀር ከሆነ የሀገርን ኢኮኖሚ ክፉኛ ሊጎዳ ይችላል። በሌላ መልኩ ደግሞ የቢሮክራሲ አተገባበር ከአድልዎ፤ ከስርቆትና ከሙስና ፅዱ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ ካልተቻለ የሀገርን ሀብት በቢሮክራሲ ስም የመበዝበዝ ሁኔታ ስለሚፈጠር በዚህ ረገድ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል።

በተስተካከለ ቢሮክራሲ እጦት፣ በሙስና፣ በጣም በተጓተተ የሥራ ሂደትና ኃላፊነትን በአግባቡ ባለመወጣት ምክንያት የሃገርን ኢኮኖሚ ወደኋላ ይጎተታል:: በተቋማት ውስጥ ቢሮክራሲያዊ ብልሽቶች ሲፈጠሩ ሙስናን ጨምሮ ዘርፈ ብዙ ወንጀሎች ይፈፀማሉ:: ሕዝብ በመንግሥት ተቋማት ላይ ያለውን አመኔታ እንዲሸረሽር ከፍ ሲልም እንዲሟጠጥ ያደርጋል።

ዘርፉ ምሑራን እንደሚያስረዱን ከሆነም፣ የአንድ ሃገር የቢሮክራሲ አወቃቀር የሀገሪቱን ጥንካሬና ሁለንተናዊ እድገት ፍንትው አድርጎ ያሳያል:: ጠንካራ ሀገረ መንግሥታትም ምንጊዜም ቢሮክራሲያቸውን የሚያዋቅሩትና የሚገነቡት ዕውቀትንና ቴክኒካዊ ችሎታን መሠረት አድርገው ነው::

ለአብነትም የልማታዊ መንግሥት የዕድገት ፈለግ አብነት ተደርጋ የምትጠቀሰው ጃፓን፣ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከደረሰባት አሰቃቂ ሽንፈት አገግማ ዓለምን ያስደመመ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ማስመዝገብ የቻለችው ጠንካራ ቢሮክራሲ በመገንባቷ መሆኑ ይታመናል::

በኢትዮጵያ ቢሮክራሲው ብዙ ጊዜ በቀርፋፋነት ወይም ቀልጣፋ ባለመሆንና በውጤታማነት ማነስ ትችት የሚሰነዘርበት ነው:: በሀገሪቱ ቢሮክራሲ ያልተፈታ ሽምቀቆ ነው:: ቢሮክራሲው ያልተስተካከለና በተለይ ቀርፋፋ በመሆኑ ለፈጣንና ለተለዋዋጭ ሁኔታዎች ራሱን አላዘጋጀም:: የአቅምና የግንዛቤ ችግር ስላለበት ፈጣን ውሳኔ ለመስጠት ያመነታል:: «እሺ» ከማለት ይልቅ «እንቢ» ማለት ይቀናዋል:: ከዘመኑ አስተሳሰብ ጋር የሚራመዱ ብልህ ቢሮክራቶች ስለመኖራቸው ባይካድም አብዛኞቹ ግን የአቅም ግንባታ ከፍ ሲልም ተግሳፅና ማስጠንቀቂያ የሚያስፈልጋቸው ናቸው::

በእርግጥ የለውጡ መንግሥት ቢሮክራሲውን "ለማዘመን" ባደረገው ጥረት ብዙ ለውጦች ተደርገዋል:: ውጤት የታየባቸውም በርካቶች ናቸው:: ይሁንና ለውጡ ተገልጋዩ ኅብረተሰብ የሚፈልገውን ቀልጣፋ፣ በባለሙያ የተሞላ፣ ተጠያቂነት የሰፈነበት ሥርዓትን በማስፈን ረገድ ብዙ እንደሚቀር ለክርክር የሚያስቀምጥ አጀንዳ አይደለም:: በሀገሪቱ ከውስን ተቋማት በስተቀር አብዛኞቹ አገልግሎት አሰጣጣቸው የተጓተተና የሚያማርር እንደሆነ የአደባባይ ምስጢር ነው::

በተለይ አንዳንድ አመራሮች ቢሮክራሲያዊ አሠራርን በማንሻፈፍ ዜጎችና ባለጉዳዮች እንዲማረሩ በማድረጉ በኩል የተካኑ ስለመሆናቸው ሲገለፅ መስማት የተለመደ ነው:: በአንዳንድ ቦታዎች በስንት ማግባባት የመጣን የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ኢንቨስተር እንደማይፈለግ እንግዳ የማየት አሳዛኝ ድርጊት ይፈጸማል::

ማክስ ዌበርን ጨምሮ ሌሎችም ምሑራን፣ የቢሮክራሲ ፅንሰ-ሀሳብ ተዋረዳዊ መዋቅርን፣ በግልጽ የተለዩ ሚናዎችንና ኃላፊነቶችን፣ መደበኛ ሕጎችንና ሂደቶችን እንዲሁም ግላዊ ያልሆኑ ግንኙነቶችንና መስተጋብሮችን እንደሚያካትት በግልፅ አመላክተዋል:: ይሁንና በሀገራችን ይህን ፅንሰ ሃሳብ በተግባር መሬት ላይ የሚተገብሩ ተቋማት ቁጥር «ጥቂት» በሚል ብቻ የሚገለፅ አይደለም::

በአንዳንድ ተቋማት የሚገኙ አመራሮች በተለይም በግልጽ የተለዩ ሚናና ኃላፊነቶቻቸውን እንዲሁም መደበኛ ሕጎችንና ሂደቶችን በአግባቡ መወጣት ሲሳናቸው እንዲሁም በሌሎች የሥራ ሂደቶች መከናወን ያለባቸውን ተግባራት ጭምር «ካልጠቀለልኩ ሞቼ እገኛለሁ» በሚል እጃቸውን ሲያስገቡ ካልሆነም ለማስገባት ሲታትሩ እንደሚውሉ ይነገራል::

መሰል አመራሮች ሚናና ኃላፊነቶቻቸው በማይፈቅድላቸው ሁኔታ ውስጥ ታች ወርደው ሲደክሙ የሚውሉት በአብዛኛው ለተቀመጡበት ወንበር በሚመጥን መልኩ ሃገርና ተቋምን ለመቀየር ለሚያግዝ የለውጥ ሃሳብና ተግባር ማዋጣት ሲከብዳቸው ነው:: ይህ ካልሆነም የግል ፍላጎትን ታሳቢ አድርገው የሚወዱትን ለመጥቀም፣ የሚጠሉትን ለማጥቃት ነው:: መታወቅ ያለበት ሐቅ ግን መሰል የሙጥኞች፣ የቢሮክራሲን ሽምቀቆ በማጥበቅ ለሥራ ቅልጥፍና እና ውጤታማነት ያላቸው ፋይዳ ከዜሮ ጋር የሚደመር መሆኑን ነው::

ቢሮክራሲ ለእድገትን ለውድቀትም እጅግ ወሳኝ ሚና ያለው እንደመሆኑ በኢትዮጵያ ምድር ሁለንተናዊ ብልፅግናን ለማረጋገጥ ሲታሰብ መሰል ድክመቶችን ማረምና ቢሮክራሲውን በአግባቡ መምራት ማስኬድና መግዛት ትኩረት ከሚሠጣቸው ጉዳዮች መካከል ዋነኛው ማድረግ አማራጭ ሳይሆን የግድ ነው:: ያልተፈታው የቢሮክራሲ ሽምቀቆ መፍታት የሁሉም ቁልፍ መሆኑን ጠንቅቄ መረዳትና ለመፍትሔው መሥራትም የነገ ሳይሆን የዛሬ ተግባር ሊሆን ይገባል::

Bureaucratic red tape ተብሎ የሚወገዘው ቅጥ ያጣ መጓተት የሚወገደው በጥሩ አመራር ነው:: ለዚህ ደግሞ ብቃቱ ያላቸው አመራሮችን ማፍራት የግድ ነው:: ይህን በማድረግም ሥራን ማፋጠን እንዲሁም የባለጉዳዮችን የጊዜ ብክነትን መቀነስም ይኖርብናል::

የቢሮክራሲን ሽምቀቆ ለማላላት ከተቻለም ለመፍታት መንግሥትም ሆነ ፖሊሲዎችን ለማስፈጸም ሥልጣን የተሰጣቸው ተቋማት ውስጣዊ አሠራራቸውን በመፈተሽ ዘመናዊና ከዓለም ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በተወዳዳሪነት ለመራመድ የሚችል የቢሮክራሲ ሥርዓት መዘርጋት ይኖርባቸዋል።

የሃገር ገጽታን ከሚያጨልሙ ችግሮች መካከል አንዱ የሆነው ይህ ጉዳይ ካልታሰበበት አሳሳቢ ነው:: ልፋቶችን በሙሉ በዜሮ ያባዛል:: ይህን ችግር ለስር መሠረቱ ለማስተካከል መንግሥት ቢሮክራሲውን ትራንስፎርም ማድረግ ይኖርበታል:: በተለይ ሕዝብን የሚያስለቅሱ፣ የሚበድሉ፣ የሚመዘብሩ፣ ፍትሕን የሚረግጡ፣ ሲያሻቸውም በመንግሥት መመሪያ ስም እያጭበረበሩ ሲላቸውም የጠሉትን ለመበቀል የወደዱትን ለመጥቀም የሚራወጡ ቢሮክራቶችን አድኖ ከወንበራቸው ማስነሳት አለበት::

አገልግሎት ሰጪ ተቋማትም የአሠራር ሥርዓታቸውን ቀልጣፋ፣ ግልጸኝነት የተሞላበት ማድረግ እንዲሁም ከሙስና እና ከብልሹ አሠራር በፀዳ መልኩ መተግበር ይኖርባቸዋል። ዘመናዊ ቢሮክራሲ ባሕልና ባለሙያዊነትን ማዳበርም አስፈላጊ ነው:: በሀገሪቱ ከሚገኙ ቢሮክራሲን በአግባቡ ማስኬድ ከቻሉ ተቋማት ልምድ መቀመርም ለውጤታማነት ወሳኝ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው:: ከሁሉ በላይ ያልተፈታው የቢሮክራሲ ሽምቀቆ መፍታት የሁለንተናዊ የብልፅግና ቁልፍ መሆኑን ጠንቅቄ መረዳትና ለመትፍሔው መሥራት የነገ ሳይሆን የዛሬ ተግባር መሆን አለበት::

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## እዮስያስ ልበ-ሙሉ ብላቴና ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

እነሆ! ዛሬ ቀኑ ልዩ ነው። ዕለቱን በጉጉት ሲናፍቁ የቆዩ ሕፃናት በትምህርት ቤቱ አጸድ ማልደው ተገኝተዋል። የአካባቢው ነዋሪ፣ ጥሪ የደረሳቸው እንግዶች፣ መምህራንና ሌሎችም ስፍራውን እያደመቁት ነው። በተለይ ትንንሾቹ ልጆች ሌቱ የነጋላቸው አይመስልም። አብዛኞቹ ወፍ ሲንጫጫ ጀምሮ ሲዘጋጁ መቆየታቸው ያስታውቃል።

ዓመቱን ሙሉ ዕውቀት ሲፈስበት የቆየው ይህ ስፍራ ዛሬ በተለየ ዓላማ ተገልጧል። የማንነቱ ምልክት የሆኑ ተማሪዎች የልፋት፣ ድካማቸውን ውጤት ሊያዩ፣ በሽልማት፣ በምስጋና ሊመረቁ ጊዜው ደርሷል። ይህ እውነት የመጀመሪያቸው ለሆነ ሕፃናት ደግሞ ስሜቱ በእጅጉ ይለያል።

በመመረቂያ ልብሳቸው ከወዲያ ወዲህ የሚሉት ሕፃናት የ«ኦርቶተ» አካዳሚ ፍሬዎች ናቸው። በወላጆቻቸውና በእኩያ ባልንጀሮቻቸው ታጅበው ልዩ ደስታን ተጎናጽፈዋል። ለአብዛኞቹ ከወዳጅ ዘመድ የሚበረከትላቸው አበቦችና ስጦታዎች ተዘጋጅተዋል። የትምህርት ሀሁን የጀመሩበት ትምህርት ቤትም ስለ ውጤታቸው ዝም አላለም። እንደ የጥረታቸው የሚገባቸውን ማበረታቻ «እነሆ» ሊላቸው ዝግጁ ነው።

የ«እንኳን ደስ አላችሁ» ህብረ ዝማሬ ደምቆ መሰማት ይዟል። ይህ መዝሙር በትምህርት ዓለም ተጉዞ ከፍጻሜ ለደረሰ ሁሉ ልዩ ስሜትን ያቀብላል። ዛሬን በዚህ ዝማሬ የታጀቡት ሕፃናት ደግሞ ስለነጋቸው በእያንዳንዱ ስንኝ ይሻገራሉ። በሚያልፉበት ጎዳናም የስኬት ድልድያቸውን ይገነባሉ። ይህ ዓይነቱ እውነት እስከ አሁን እልፎችን አጎልብቶ ለፍሬ አድርሷል።

ሰዓቱ እየሮጠ ነው። የክረምቱን ዝናብ አሸንፋ የደመቀችው ፀሐይ ለቀኑ ያገዘች ይመስላል። ተመራቂ ሕፃናት፣ ተሸላሚ ተማሪዎች፣ እንግዶችና የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ቦታቸውን ይዘዋል። የዕለቱ መርሀ ግብር በታለመለት ዕቅድ መካሄዱን ቀጥሏል። የምክክር መድረክ፣ የተማሪዎች ድንቅ ችሎታ፣ የሥነ ጽሑፍና የምርቃቱ ሥነ ሥርዓት እየተከወነ ነው።

በድንኳኑ የፊተኛው ረድፍ ካሉ እንግዶች መሀል ሁሉን ትዕይንት በአንክሮ የሚያስተውል አንድ ትንሽ ልጅ እይታን ይስባል። አለባበሱ ንጹህና ጠንቃቃ፣ በዕድሜውም ደግሞ ገና እምቦቃቅላ ነው። እያንዳንዱን ትዕይንት በአንክሮ እያስተዋለ ይደመማል። በየአጋጣሚው ለመሳቅ አይቸኩልም። እራሱን እየወዘወዘ በሚያስገርመው ይደነቃል፣ በሚያስደንቀው እጁ እስኪግል ያጨበጭባል።

እሱ ካሻው ቦታ ተራምዶ አያልፍም። እንደ ሌሎች ፈጥኖም አይሮጥም። ካለበት እየመጡ የሚያቅፉ፣ የሚስሙት ግን በርካቶች ናቸው። ያገኙት ሁሉ ስሙን እየጠሩ ፍቅራቸውን ይገልጹለታል። አክብሮቱ ደግሞ እንደ አዋቂ ነው። ለእያንዳንዱ የሚሰጠው ምላሽ ልብ ይነካል። ከተቀመጠበት ዊልቸር የአቅሙን ያህል ተንቀሳቅሶ ምስጋናውን ለመግለጽ አይዘገይም።

### ማነው?

እኔ የዚህ ሕፃን ማንነት አልጠፋኝም። ስለእሱ የራሴን ታሪክ ያህል አሳምሬ አውቃለሁ። ሁሌም ቢሆን በውስጤ ውሎ ያድራል። ስለእሱ ዘወትር እያስታወስኩ እተክዛለሁ። የልጅነት አእምሮው፣ ስለሌሎች ያለው ፍቅርና አክብሮት ሁሉ ከእኩዮቹ ይለያል። ይህን ልጅ ሳስብና ሳስታውስ ግን ስለወላጅ እናቱ የተለየ ብርታት መዘንጋት አይቻለኝም። ጥንካሬዋ ሁሌም እንዳስደነቀኝ ነው። ስለዚህ ልጇ የከፈለችው መስዋዕትነት የእናትነት ወርቃማ ምሳሌ ያደርጋታል።

እሷ ማለት ስለልጇ መኖር፣ ሕይወትና እስትንፋስ ናት፣ ስለእሱ መማርና ማወቅ እንደሻማ ቀልጣ ብርሃን የሰጠች ልዩ ሴት። ካሰበችው ለመድረስ ብዙ ደክማ ዝላለች። በልፋቷ መሀል ያየችው ታሪክ መልከ ብዙ ነው። የእሷ መንገዶች መቼም አልጋ በአልጋ አልነበሩም። ያለፈችባቸው የሕይወት ጎዳናዎች ፍጹም እሾሃማና ሻካራማ ናቸው። ልጇን ወልዳ ካቀፈችበት የመጀመሪያዋ ቀን አንስቶ ሕይወቷ በጭንቅ የተሞላ ፈታኝ ነበር።

### ከዓመታት በፊት...

በሶስት ልጆች የተባረከው የጥንዶቹ ጎጆ ዓመታትን በፍቅር ዘልቋል። መተሳሰብ የሞላው ትዳር ለሌሎች መልካም አርአያ ነው። ባልና ሚስቱ በፍቅር ውለው ያድራሉ። አሁን ደግሞ አራተኛው ልጃቸው ሊመጣ በጉጉት እየተጠበቀ ነው። ለቤቱ እንግዳ የሆነው ይህ ሕፃን ለቤተሰቡ መልካም ስጦታ ነው። ሁሉም በስስት፣ በጉጉት ይናፍቁታል።

ወይዘሮ ልኬለሽ ተፈሪ በወር ደሞዝ የምታድር የመንግሥት ሠራተኛ ናት። ዘወትር የባለቤቷን ሰርቶ መግባት፤ የልጆቿን ተምሮ መመለስ ትናፍቃለች። እንደ እናት፣ ለልጆቿ የዋህ፣ እንደሚስት ለባሏ አሳቢ ነች። ሁሌም ቢሆን ቤቷን አጉድላ አታውቅም። በመሥሪያ ቤቷም ትጉህና ጠንካራ መሆኗ ይነገርላታል።

ልኬለሽ እንደማንኛዋም ነፍሰጡር ክትትሏን አቋርጣ አታውቅም። ቀጠሮ ባላት ጊዜ ከሐኪም ፊት ትቀርባለች። የምትባለውን አድምጣ ትዕዛዝ ለመፈጸም አትሰንፍም። እርግዝና ለእሷ አዲስ አይደለም። ሌሎቹን ስትውልድም በዚሁ መንገድ አልፋለች።

አሁን ልኬለሽ የመውለጃ ጊዜዋ ቀርቧል። እንደ አራስ ቤት የሚያስፈልጋትን ማሟላት አለባት። ለአዲሱ እንግዳ፣ ለልጆቿ ወንድም የሚበጀውን ማድረግ ግድ ይላታል። ከጥቂት ጊዜ በኋላ አዲሱን ጨቅላ ትታቀፋለች። ከዚህ ባሻገር ለሚሆነው ደግሞ ነገ መልስ ይኖረዋል።

### ከቀናት በአንዱ ...

ዛሬ ልኬለሽ ከሐኪሟ ዘንድ ቀጠሮ አላት። ቀኑን ሳታዛባ በዕለቱ ተገኝታለች። እንደ ሁልጊዜው የምትባለውን ሰምታ ለመሄድ ራሷን አዘጋጀች። ምርመራዋ ከወትሮው የተለየ ነበር። ምክንያቱ ባይገባትም መደንገጧ አልቀረም።

ከደቂቃዎች በኋላ የሰማችው እውነት ከአቅሟ በላይ ሆነ። ሐኪሙ በእጁ የገባውን የአልትራሳውንድ ውጤት እያስተዋለ ያለማወላወል ዕቅጩን ነገራት። ይህ ከመሆኑ በፊት እናት ልኬለሽ ስለእሷ ሕይወት ቅድሚያ እንደሚሰጥ አባብሎ የነገራትን ሀቅ በወጉ አልሰማችም።

አሁን ጆሮዋ ምን እያቀበላት እንደሆነ አልገባትም። ሐኪሙ ስለእሷ ሕይወት ብቻ ደጋግሞ የሚናገረው ጉዳይ እንቆቅልሽ ሆኖባታል። ለመውለድ አስራ አምስት ቀን ብቻ እንደቀራት ታውቃለች። በሰላም ወልዳ ልጇን ለማቀፍ የነበራት ህልም ዕውን አለመሆኑ እየገባት ነው።

ወይዘሮዋ በሆዷ ያለው ጽንስ ጤናማ አለመሆኑን እንዳወቀች ጤናዋ ተቃወሰ። የደም ግፊቷ ጨምሮ ልቧ ያለቅጥ ፈጠነ። ሐኪሞቹ እንዳሏት ችግሩ የተከሰተው በእርግዝና ወቅት «ፎሊክ አሲድ» የተባለው መድኃኒት በአግባቡ ባለመወሰዱ ነው። በዚህ ሳቢያ በጽንሱ ላይ የጀርባ ላይ ክፍተት አጋጥሟል። ልኬለሽ እየተነገራት ያለው እውነት በእሷም በሌሎችም ላይ አጋጥሟት አያውቅም። እንደምንም ራሷን ለመግዛት ሞከረች።

ሕፃኑ ከተወለደ በኋላ በሕይወት ከቀጠለ በቀዶ ሕክምና እንደሚታገዝ ተነግሯታል። በውስጧ ሁለት ተቃራኒ ስሜቶች ሙግት ገጠሙ። «በሕይወት» ከቀጠለ» የሚለውን ቃል ልትቀበለው ከአቅሟ በላይ ሆነ። ቀዶ ሕክምና ይሉት አማራጭ ደግሞ የቆሰለ ውስጧን ስስ ተስፋ ዘራበት። አሁን ሁሉን ለፈጣሪዋ ትታ የሚሆነውን ልትቀበል ነው። አስጨናቂዎቹን ቀሪ ቀናት አንድ፣ ሁለት... ስትል መቁጠር ያዘች።

### ከአስራ አምስት ቀናት በኋላ...

እነሆ! ጊዜው ደረሰ። የተረገዘው ሊወለድ እናት ልኬለሽ ምጥ ጀመራት። ለእሷ ይህ ጊዜ ፍጹም ልዩ ነበር። ከተለመደው ህመም የዘለለ ጭንቀት፣ እስከ ዛሬ ከምታውቀው ምጥ የተለየ ስቃይ አስተናገደች። «ምን ዓይነት ልጅ እወልድ ይሆን? »በሚል ስጋት መንፈሷ ታወከ። አዲሱ እንግዳ ዓለምን በለቅሶ ሲቀላቀል ዓይኖች ሁሉ በሁለመናው አረፉ። የሐኪሞቹ እውነት በማሳያዎች ተረጋገጠ። ሕፃኑ የተወለደው ከነርቭ ዘንግ ክፍተት ጋር ነበር።

የነርቭ ዘንግ ክፍተት በሳይንሳዊ አጠራሩ «ስፓይና ቢፊዳ» በሚል ይታወቃል። በእርግዝና ወቅት ከሚያጋጥም የፎሊክ አሲድ እጥረት ጋር ተያይዞ በሕፃናት ላይ የሚደርስ ችግር ነው። ለአብዛኞቹ ሕፃናት አካላዊ ጉዳት ምክንያት የሆነው ይህ ህመም ተደጋጋሚ የቀዶ ሕክምና የሚያስፈልገው በመሆኑ ፈተናውን ከባድ ያደርገዋል።

ልኬለሽ ከወለደች በኋላ የአራስነት ወግን አላየችም። መላ ቤተሰቧን ከቤት ትታ ለወራት ከጨቅላው ጋር በሆስፒታል አልጋ ከረመች። ስለ ትንሹ ልጅ ህመሙን ተጋርታ፣ ጭንቀቱን ተካፈለች። በጥረት ልፋቷ ሕይወቱን የታደገችው እናት «በቃ» እስኪትባል እግሮቿ አልራቁም። ዓይኖቿ ከልጇ ዓይኖች አልተነቀሉም።

### እዮስያስ ተወዳጁ ጨቅላ...

«እዮስያስ» ማለት ትርጉሙ «እግዚአብሔር፣ ያግዛል፣ ይደግፋል» እንደማለት ነው። እውነትም እንደ ቃሉ ሆኖ እናት ልኬለሽ በፈጣሪዋ ድጋፍ ትንሹን እዮስያስ ይዛ ከቤቷ ገብታለች። ቤተሰቡን ከተቀላቀለ ወራትን የቆጠረው ሕፃን በእህት ወንድሞቹ ተናፋቂና ተወዳጅ ሆኗል።



ሕፃን እዮስያስ ኃይሉ

ዮሲ እንደማንኛውም ሕፃን ሊሆን የሚቻለው አይደለም። ቀዶ ሕክምናውን ያስተናገደ አካሉ ጥንቃቄን ይሻል። ሕክምናው በዚህ ብቻ አይበቃምና በየጊዜው በሐኪሞች ይጎበኛል። ዕድገቱ በጨመረ አካሉ ባደገ ቁጥር ተያያዥ ችግሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ ለእናት ልኬለሽ ተነግሯታል። ከዚህ ችግር ጋር የሚወለዱ ልጆች ባብዛኛው ከቤተሰብና ከማህበረሰቡ መገለል ያገኛቸዋል። በወጉ ለመንቀሳቀስ፣ ተምሮ ለመለወጥ የሚኖራቸው ዕድልም የጠበበ ነው።

### እናትነት ከቃል በላይ...

ዮሲ ከወገቡ በታች አካሉ አይንቀሳቀስም። የህመሙ ተጽዕኖም ሕፃንነትን የሚሻገር የዳይፐር ተጠቃሚ እንዲሆን ያስገድደዋል። ይህን የተረዳችው እናት ስለልጇ መኖር ራሷን አዘጋጀች። ለዓመታት ትሰራበት የነበረውን ቋሚ ሥራ ለቃ የቤት እመቤት ሆነች። ስለ ትንሹ ልጅ ራሷን ጣለች፣ ከሳች፣ ተጎሳቆለች። ይህ ሁሉ ሲሆን ልጇ እንዳይከፋ፣ እንዳያዝን ፈገግታዋ ከፊቷ ነበር።

አሁን እዮስያስ ዕድሜው እየጨመረ አካሉ እያደገ ነው። ትምህርት ቤት የመግቢያ ዕድሜው ቢደርስም ከመሬት ችሎ አይነሳም፣ ለመራመድ ለመሮጥ አይሞክርም። ዮሲ አስተውሎቱ የዳበረ፣ ግንዛቤው የተለየ ልጅ ነው። እኩዮቹ፣ ከትምህርት ውለው ሲመጡ ስለራሱ ያስባል። የእህት ወንድሞቹን ደብተር ሲያይ እናቱን በጥያቄ ያፋጥጣል።

### ትምህርትን ፍለጋ...

ትንሹ ልጅ ስለትምህርት በትኩረት እያሰበ ነው። የእሱ ከሌሎች ተለይቶ ከቤት መቅረት እየገባው አይደለም። በየጊዜው ለምን ሲል ራሱንና ሌሎችን መጠየቁን ቀጥሏል። እናት ልኬለሽ አሁንም ስለእሱ ዝም አላለችም። የልጇን ፍላጎት ለመሙላት፣ በዕድሜው የትምህርት ዕድል እንዲያገኝ አበከራ መታገሏን ይዛለች።

ዮሲ እንደሌሎች ልጆች ራሱን ችሎ አይሄድም። እሷም እጁን በእጇ ይዛ ምሳ ዕቃውን ቋጥራ ወስዳ አትመልሰውም። እንዲህ መሆኑ ተስፋዋን አላጨለመም። ልጇን አዝላ ትምህርትን ፍለጋ ተጓዘች። ነገሮች ሁሉ እንደታሰቡት አልሆኑም። በር ያንኳኳችባቸው ትምህርት ቤቶች ሁሉ ፊት ነሷት።

እነሱ በእግሩ ሮጦ የሚገባ እንጂ ታዝሎ የሚመጣ ተማሪ አጋጥሟቸው አያውቅም። ዳይፐር የሚጠቀም፣ የሌሎች እገዛን የሚሻ ሕፃንም አይፈልጉም። እናት ልኬለሽ ተስፋ አልቆረጠችም። በየቦታው እያንኳኳች፣ እየጠየቀች፣ በድካም ባዘነች። ጥቂት ቆየት ብሎ አንድ ትምህርት ቤት ሊቀበለው ፈቀደ። የልጇ ፍላጎት ሞላ። በእጅጉ ደስ አላት።

### ‹‹ስላም ቀንዷ አይከብዳትም››

አሁን ልኬለሽ በየቀኑ ልጇን አዝላ ትጓዛለች። የእሷ መንገድ ወደ ዕውቀት ያደርሳል፣ የልጇን ምኞት ይሞላል። አካባቢዋ የእግር መንገድ አለው። ከቤት ትምህርት ቤት ለመድረስ ወጥታ የምትወርደው የድንጋይ ደረጃ ተቆጥሮ አያልቅም። እሱን አልፋ ታክሲ ለመያዝ ደግሞ ብዙ መታገል፣ መጋፋት ይጠብቃታል። የታዘለውን ትልቅ ልጅ የሚያዩ ባለታክሲዎች ከሌሎች እሷን ሊያሳፍሩ አይፈቅዱም። እንዳላየ ዘግተዋት ያልፋሉ።

የልኬለሽና የልጇ እንክርት ከአቅም በላይ ሆኗል። እሷ በየቀኑ አዝላው መዞሩ ቢያደክም እንጂ አላሰለቻትም፣ ስለ እሱ ደስታና ፍላጎት የእናትነት ፍቅሯን እየከፈለች ነው። ውሎ ሲያድር ልኬለሽና ቤተሰቦቿ መከሩ። የነበረቡትን አካባቢ ለቀው ቢሄዱ ለትንሹ እዮስያስ እንደሚበጅ ገባቸው።

### አዲሱ ሰፈር...

አሁን የእነዮስያስ መኖሪያ ተቀይሯል። ከከተማ ወጣ ብለው የገቡበት ሰፈር ውጣወረድ የሌለበት ፀጥተኛ ነው። እንዲህ መሆኑ ትንሹን ልጅ ለማንቀሳቀስ፣ ከትምህርት ቤት አውሎ ለመመለስ ያመቻል። ይህ መልካም አጋጣሚ የዮሲን ፍላጎት አሟላ። በአካባቢው የሚገኝ ትምህርት ቤት ሊያስተምረው ፈቀደ።

ጎበዙ ዮስያስ ዛሬም በእግሩ አይራመድም። ልክ እንደ ትናንቱ ዳይፐርና የሌሎች እገዛን ይፈልጋል። የሁልጊዜው አጋር ውድ እናቱ ዛሬም ከጎኑ ናት። በማለዳው ገላውን አጥባ፣ ዳይፐሩን ቀይራ ለትምህርት ታዘጋጀዋለች። ዮሲ ዛሬ ላይ የዘጠነኛ ዓመት ዕድሜውን እየተሻገረ ነው። አካሉ ጎልብቷል። አስተሳሰቡ ከእኩዮቹ የላቀ ነውና የሚጽፋቸው ግጥሞች ከእሱ የሚጠበቁ አይመስሉም። ሁሌም የሚያየውን አይዘነጋም። ቁም ነገር ሲጫወት፣ የወዳጅ ዘመድ ጤናን ሲጠይቅ ልጅ መሆኑን ያስረሳል።

በአዲሱ ሰፈር ኑሮ ከተጀመረ ወዲህ እዮስያስ ትምህርቱን በወጉ እየተማረ ነው። እገዛ ቢያሻውም በዊልቸሩ ለመንቀሳቀስ ይሞክራል። ከጥቂት ጊዜ ወዲህ መለስ ቀለስ የሚልበት የጤና ችግር ግን አንዳንዴ ከትምህርቱ ያስቀረው ይዟል። መላው ቤተሰብ ጭንቅ ውስጥ ነው። ቤቱን በፍቅር ሙሉ የሚያደርገው ትንሽ ልጅ ውሎው ከሆስፒታል መሆኑ ለሁሉም ሰላም አልሰጠም።

ዮሲ ከዚህ ቀድሞ የነበረው የሕክምና ክትትል አልተቋረጠም። ዘንድሮ ጀርባው ላይ ያደረገው ቀዶ ሕክምና ግን ቁም ቋጥሮ ያሰቃየው ጀምሯል። የልጅነት አካሉ ስቃዩን መቋቋም አልቻለም። ለስምንት ወራት በኢንፌክሽን ቁስል ተሰቃየ። በቀላሉ ወደቤቱ አልተመለሰም። ከሚወደው ትምህርቱ ተቆራረጠ።

እነሆ! ዛሬ ትንሹ እዮስያስ በተማሪዎች የምርቃት ቀን ከፊት ተቀምጦ ዝግጅቱን እየቃኘ ነው። ለወራት ርቆት የቆየው ትምህርት ትውስ ያለው ይመስላል። የኦርቶተ አካዳሚ ፍሬዎች የዕለቱ ድምቀቶች ሆነዋል። አምና ይህን ጊዜ ዮሲ ተሸላሚ ተማሪ ነበር። ዘንድሮ ደግሞ እንደ ተጋባዥ እንግዳ ከፊት ተቀምጧል።

የዕለቱ ዝግጅት በተያዘለት ዕቅድ እየተከወነ ነው። በድንገት ዮሲ የመርሀ ግብሩ አንዱ አካል ሆኖ ወደ መድረኩ ተጋበዘ። ወዲያው ዊልቸሩን የሚሸከሙ፣ እጆች ተረባረቡ። ትንሹ ልጅ በእርጋታ ንግግሩን ጀመረ። ትምህርት ቤቱ የመማር ዕድል ስለሰጠው፣ ጓደኞቹ ፍቅርና አክብሮት ስለለገሱት ከልብ አመሰገነ። ለዕለቱ ያዘጋጀው ግጥም ጆሮ ገብ ነበር።

ስለእሱ የሚናገሩ አንደበቶች ዝም አላሉም። ማንነቱን ሊተርኩ ቃላት አወጡ። ጥንካሬው፣ ጉብዝናው ተወሳ። የእናት ልኬለሽ ብርታትም እንዲሁ። ዮሲ ዛሬም ድጋፍን ይሻል። ዳይፐር ያስፈልገዋል። የትምህርት ቤት ክፍያና ሌሎች ወጪዎች ይጠብቁታል። በስፍራው የነበሩ እንግዶች ስለእሱ ባወቁ ጊዜ በዓይኖቻቸው ዕንባ ሞላ። አብዛኞቹ በትካዜ አንገታቸውን ደፉ።

### ዕንባ ሲታበስ..

ከአፍታ ደቂቃዎች በኋላ አንድ አስገራሚ እውነት ወደ መድረኩ ደረሰ። የኦርቶተ አካዳሚ የቦርድ አባላት ፈጣን ውሳኔን ይዟል። ሕፃን እዮስያስ ኃይሉ የትምህርት ቤቱ ድንቅ ፍሬ ነው። እስከዛሬ በብዙ ችግሮች መሀል ተመላልሷል። ከአሁን በኋላ ግን ይህ ፈተናው አይደገምም።

ለእዮስያስ የትምህርት ክፍያው ነፃ ይሆንለታል። የመማሪያ ቁሳቁስ ይሟላለታል። የዳይፐር ወጪውም ይሸፈንለታል። በጭብጨባ የደመቀው መድረክ በአድናቆትና ክብር ተሞላ። የዮሲ ፊት በፈገግታ ደመቀ፤ የእናት ልኬለሽ አንደበት ለምስጋና ተከፈተ። ልበ ሙሉው ብላቴና ለራሱ ቃል ሲገባ አደመጥኩት። ከዚህ በኋላ ትምህርቱን ያለ አንዳች ችግር እንደሚቀጥል ሲናገር በተለየ ተስፋ ተሞልቶ ነበር።

# የግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ

ሲዳማ ብ/ክ/መንግስት እርሻና ተፈጥሮ ሀብት/ል/ቢሮ፡-

ሎት 1 CALAM-A ፕሮግራም የካኖን ፕርንተር /2545/

ሎት 2 ፖል ባግ ባለ 16 cm እና ባለ 10 cm

ሎት 3 የይዞታ ማረጋገጫ ሰርትፍኬት የሚባዛበት እስፔኪታ ወረቀት በጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል ፡፡

**ስለዚህ በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች ፡-**

1. በዘርፉ የታደሰ የንግድ ፍቃድ ያለው
2. ለአቅራቢነት የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል
3. ተጨማሪ የእሴት ታክስ (VAT)ተመዝጋቢ የሆነ
4. የግብር ከፋይነት ሴርትፍኬትና መለያ ቁጥር ያለው
5. የዘመነ ግብር ስለመክፈላቸው የግብር ከፋይነት ማስረጃ የሚያቀርቡ
6. ተጫራቾች ዝርዝር መግለጫ /እስፔስፊኬሽን / ከጨረታ ሰነዱ ማግኘት ይችላሉ። ለእያንዳንዱ ጨረታ ሰነድ የማይመለስ ሁለት መቶ /200/ ብር ከፍሎ መግዛት አለባቸው።
7. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ 20,000 በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ (CPO) ማስያዝ አለበት።
8. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዳቸው ተክንካልና ፋይናንሻል አርጅናልና ኮፒ እያንዳንደቸው ለየብቻ በስም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግና ጠቅላላውን በአንድ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ ማቅረብ አለባቸው፡፡
9. ጨረታው በአድስ ዘመን ጋዘጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ ለ15 ተከታታይ ቀናት አየር ላይ የሚውል ሲሆን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ላይ ታሽጎ በዚያው ዕለት ከረፋዱ 5፡00 ሰዓት በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ ግዥ ፋ/ን/አስ/ዳይሬክቶሬት ክፍል ቢሮ ቁጥር 56 ተጫራቾች (ሕጋዊ ወክሎቻቸው) በተገኙበት ይከፈታል፡፡
10. መ/ቤቱ የተሸለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
11. በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች ተጨማሪ መረጃ ቢያስፈልጋቸው ግዥ ፋ/ን/አስ/ዳይሬክቶሬት በስልክ ቁጥር 0462212413 በመደወል ማግኘት ይችላሉ፡፡

**የሲዳማ ብ/ክ/መ/ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ**

# የግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ

የሲዳማ ብ/ክ/መንግስት እርሻና ተፈጥሮ ሀብት/ል/ቢሮ ለ2ኛ ደረጃ መሬት ልኬት ስራ የማሳ **መመዝገቢያ ቅፃች -**

1 . የማሳ መረጃ መመዝገቢያ ቅፅ (FRF) ፣

2 . ደረሰኝ እና

3 . ግጭት ፎርም (Dispute form) ቅፆችን በጨረታ አወዳድሮ ለማሳተም ይፈልጋል፡፡

**ስለዚህ በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች፡-**

1. በዘርፉ የታደሰ የንግድ ፍቃድ ያለው
2. ለአቅራቢነት የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል፣
3. ተጨማሪ የእሴት ታክስ (VAT)ተመዝጋቢ የሆነ ፣
4. የግብር ከፋይነት ሴርትፍኬትና መለያ ቁጥር ያለው፣
5. የዘመነ ግብር ስለመክፈላቸው የግብር ከፋይነት ማስረጃ የሚያቀርብ ፣
6. ተጫራቾች ዝርዝር መግለጫ /እስፔስፊኬሽን / ከጨረታ ሰነዱ ማግኘት ይችላሉ፡፡ ለእያንዳንዱ ጨረታ ሰነድ የማይመለስ ሁለት መቶ /200/ ብር ከፍሎ መግዛት አለባቸው።
7. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ 20,000 በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ (CPO) ማስያዝ አለበት ፡፡
8. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዳቸው አርጅናልና ኮፒ እያንዳንደቸው ለየብቻ በስም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግና ጠቅላላውን በአንድ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ ማቅረብ አለባቸው፡፡
9. ጨረታው በአድስ ዘመን ጋዘጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ ለ15 ተከታታይ ቀናት አየር ላይ የሚውል ስሆን በ16ኛው ቀን ከጠዋቱ 6፡00 ሰዓት ላይ ታሽጎ በዚያው ዕለት ከረፋዱ 9፡30 ሰዓት በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ ግዥ ፋ/ን/አስ/ዳይሬክቶሬት ክፍል ቢሮ ቁጥር 56 ተጫራቾች (ሕጋዊ ወክሎቻቸው) በተገኙበት ይከፈታል፡፡
10. መ/ቤቱ የተሸለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
11. በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች ተጨማሪ መረጃ ቢያስፈልጋቸው ግዥ ፋ/ን/አስ/ ዳይሬክቶሬት በስልክ ቁጥር 0462212413 በመደወል ማግኘት ይችላሉ፡፡

**የሲዳማ ብ/ክ/መ/ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ**

# የጨረታ ማስታወቂያ

በኦሮሚያ በአርሲ የሱዴ ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ለተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶች አገልግሎት የሚውሉ 1ኛ፣ የጽሕፈት መሳረሪያዎች 2ኛ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች 3ኛ፡ የቢሮ ፈርኒቸሮች 4ኛ የሰራተኞች የደንብ ልብስ 5ኛ.የጽዳት ዕቃዎች እና 6ኛ የቴክኒክና ሙያ የስልጠና መሳርያዎች በመስኩ የተሰማሩ የንግድ ድርጅቶችን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ በዚሁ መሰረት የሚከተሉትን መስፈርቱን የሚያሟሉ ማንኛውም ተጫራቾች መወዳደር የሚችሉ መሆኑን ይጋብዛል፡-

1. በግብር ከፋይነት ተመዝግቦ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ያስና ተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) የተመዘገበበትን በአቅርቦት የምዝገባ ዝርዝር(List) ማስረጃ የሚያቀርብና በ2016 ዓ.ም የዘመኑን የግብር ግዴታውን የተወጣ የንግድ ፈቃዳቸውንና የምዝገባ ሰርተፊኬታቸውን የዘመኑን ያሳደሱ ማስረጃ አያይዞ ማቅረብ ይጠበቅበታል ።
2. የጨረታውን ሰነድ ብር( 150) አንድ መቶ ሃምሳ ብር በመክፈል ከሱዴ ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 7 በመውሰድ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15/የስራ ቀናት ለዚሁ በተዘጋጀ የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል።
3. የጨረታ ማስከበሪያ ቢድ ቦንድ ብር 20,000(ሃያ ሺ ብር) በሱዱ ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ስም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ኩላ ቅርንጫፍ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000095450702 በመክፈል የከፈሉበትን ሲፒኦ ከጨረታው ሰነድ ጋር በማያያዝ የጨረታውን ሰነድ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በአንድ ወይም በሁለት ፓስታ አድርገው ኦርጂናስ እና ኮፒውን ማቅረብ ይኖርባቸዋል::
4. ጥቃቅንና አነስተኛ ማይክሮ ኢንተርፕራይዝ የሚፈለገውን ሙሉ መስፈርት አሟልተው በጨረታው ከተሳተፉ ይበረታታሉ።
5. አሸናፊው ተጫራች እቃውን በራሱ ማጓጓዣ ሱዴ ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ድረስ ማምጣት (ማቅረብ) ይኖርባቸዋል ።
6. የጨረታው ሳጥን ከታሸገ በኋላ የሚቀርብ ማንኛውም ሰነድ ተቀባይነት የለውም፡፡
7. ጨረታው ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ጀምሮ ለ15 የስራ ተከታታይ ቀናት ቆይቶ በ15ኛው የስራ ቀን 11፡00 ሰዓት ታሽጎ በ16ኛው የስራ ቀን በ3፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻችው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
8. መ/ቤቱ የተሻስ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥሮች፡- 0913474348 /0910742397 መጠየቅ ይችላሉ፡፡**

**በኦሮሚያ ክልል በአርሲ ዞን የሱዴ ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት**

# Invitation to Bid

Global Women Empowerment Development, Ethiopia (GWEDE) is a dynamic, women-led local non-profit organization with registration No. 6339. Rooted in the belief that a better world is achievable for all, GWEDE is driven by a group of self-motivated Pastoral women. We address critical development and humanitarian challenges while fostering community ownership through the empowerment of women, youth, and marginalized groups, employing a faith-based approach.

Our organization is proud to have a majority female board and a platform that provides equal opportunities for diverse women to lead at all levels. Despite our relatively short presence in Ethiopia since 2022, we possess extensive experience in WASH, Peacebuilding/Conflict Resolution, and other vital areas.

To finalize our 2023 G.C. annual budget, GWEDE seeks qualified bidders meeting the following criteria:

1. Authorized professional license
2. Business license renewed for the year 2016 E.C.
3. Proof of paid tax for the year 2015 E.C.
4. Registered VAT/TIN
5. Renewed Audit license from the relevant government authority for the year 2016 E.C.
6. Level B or above classification.

Interested and qualified bidders can submit proposals within seven working days from the date of this notice to the GWEDE Head Office located at Walo Safer (Ethio-China Road), Dire Dawa Tower, 8th Floor. For inquiries, please contact: +251929388439 or +251910777895

**Global Women Empowerment Development, Ethiopia (GWEDE)**


# ስፖርት





# የመጀመሪያው የብር ሜዳሊያ በበሪሁ አረጋዊ ተመዘገበ

ቦጋለ አበበ




በ2024 የፓሪስ ኦሊምፒክ ኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የብር ሜዳሊያ በወንዶች 10ሺ ሜትር ማግኘት ችላለች። ይህም ከ1972 ከምሩፅ ይፍጠር የነሐስ ሜዳሊያ ጀምሮ ኢትዮጵያ በተሳተፈችባቸው ኦሊምፒኮች ሁሉ በ10ሺ ሜትር ከሜዳሊያ ውጪ እንዳትሆን ያስቻለ ነው።

በትናንት ምሽቱ ፍልሚያ ኢትዮጵያውያን ወርቁ ባይቀናቸውም ከውድድሩ መጀመሪያ እስከ መጨረሻ በመተጋገዝ ያሳዩት የቡድን ሥራ ብዙዎችን አስደስቷል። ያም ሆኖ ኢትዮጵያውያኑ አትሌቶች የተሳሳተ የታክቲክ ስሌት የርቀቱን የሦስት ጊዜ የዓለም ቻምፒዮን ዑጋንዳዊውን ጆሽዋ ቺፕቴጌ ማስቆም አልቻለም። በዚህም ቺፕቴጌ 27:01.17 በሆነ ሰዓት 2008 ቤጂንግ ላይ በቀነኒሳ በቀለ የተመዘገበው የኦሊምፒክ ሪከርድ በማሻሻል በ26:43:14 ወርቁን አጥልቋል። ወጣቱ አትሌት በሪሁ አረጋዊ በአስደናቂ ጥረት በ26:43:44 የብር ሜዳሊያውን ወስዷል። ዮሚፍ ቀጄልቻና ያለፈው ኦሊምፒክ የርቀቱ አሸናፊ ሰለሞን ባረጋ ስድስተኛና ሰባተኛ ሆነው ፈጽመዋል። በውድድሩ ያደረጉት ጥረትና ያሳዩት የቡድን ሥራ ግን ትልቅ ዋጋ ነበረው።

በታሪካዊው አትሌት ማሞ ወልዴ የ1968 ሜክሲኮ ኦሊምፒክ በብር ሜዳሊያ የጀመረው የኢትዮጵያውያን አትሌቶች የኦሊምፒክ 10ሺ ሜትር ወንዶች ድል በማርሽ ቀያሪው ምሩፅ ይፍጠር የ1980 ሞስኮ ኦሊምፒክ የወርቅ ሜዳሊያው አንድ ብሎ ጀምሯል። የርቀቱ የወርቅ ሜዳሊያ ክብር በጀግናው አትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴ ከአትላንታ እስከ ሲድኒ፣ በአቦ ሸማኔው ድንቅ አትሌት ቀነኒሳ በቀለ ከአቴንስ እስከ ቤጂንግ እንዲሁም በወጣቱ አትሌት ሰለሞን ባረጋ የቶኪዮ ኦሊምፒክ ገድል ጎልቶ መታየት ችሏል። ዘንድሮ ግን ዳግም የርቀቱ ክብር ከኢትዮጵያውያን አምልጧል።

በርቀቱ ትልቁ የኢትዮጵያ ውጤት አቴንስ 2004ና ቤጂንግ 2008 ቀነኒሳ በቀለና ስለሺ ስህን ተከታትለው በመግባት ወርቅና ብር ያጠለቁበት ነው። በአራት ተከታታይ ኦሊምፒኮች ከ1996- 2008 የወርቅ ሜዳሊያ በማሸነፍ ኢትዮጵያ ቀዳሚ ናት። ስድስት ነሐስ በማግኘትም ቀዳሚ ስትሆን በብር ሜዳሊያም ከፊንላንድ በአንድ ዝቅ ብላ በ3 ሜዳሊያ ተከታይ ነች። በሪሁ አረጋዊ ትናንት ምሽት ያጠለቀው የብር ሜዳሊያ ከማሞ ወልዴና ስለሺ ስህን ጋር ታሪክ እንዲጋራ አድርጎታል።

ቺኮስላቫኪያዊው ኤሚል ዛቶፔክ በተከታታይ ወርቅ በማጥለቅ የመጀመሪያ ነው። ኃይሌ ገብረሥላሴ፣ ቀነኒሳ በቀለና በሞ ፋራህ ይህን ታሪክ ተጋርተዋል። ከኃይሌ ገብረሥላሴ 1996 የአትላንታ ድል ጀምሮም በርቀቱ አንዴ ያሸነፈ አትሌት በቀጣይ ኦሊምፒክ ሌላ ድል ደግሟል። ይህም በቀነኒሳና ሞ ፋራህ ወርቃማ ዘመንም ቀጥሏል። ሰለሞን ባረጋ በዚህ ረገድ ዘንድሮ ሊሳካለት አልቻለም።

ፊንላንድ በ10ሺ ሜትር ታሪክ 7 ወርቅ፣ 4 ብር፣ 4 ነሐስ በማስመዝገብ ቀዳሚ ስትሆን፣ ኢትዮጵያ በ6 ወርቅ፣ 4 ብር፣ 6 ነሐስ ትከተላለች።